በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም

ሚያዝያ/ ግንቦት ፲፱፻፹፰

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፭
$2.75

# ላንዳፍታ



# አጼ ምንሊክ
# ና
# እቴጌ ጣይቱ

የብልህና የቆራጥ
አመራር አርአያዎች፤
የአድዋ ድል ግንባር
ቀደም ተዋናዮች፤
የጥቁር ሕዝቦች
ነፃነት ታጋዮች፤



እግዚአብሔር፡በቸርነቱ፡እ
ስካሁን፡ጠላት፡አጥፍቶ
አገሬ፡አስፍቶ፡አኖረኝ፡
እኒም፡እስካሁን፡በእግ
ዚአብሔር፡ቸርነት፡ገዛ
ሁ፡እንግዲህ፡ግን፡ብሞ
ትም፡ሞት፡የሁሉ፡ነውና፡
ስኔ፡ሞት፡አላዝንም፡ደ
ግሞ፡እግዚአብሔር፡አሳ
ፍሮኝ፡አያውቅምና፡እን
ግዲህም፡ያሳፍረኛል፡
ብዬ፡አልጠረጥረውም፡
አሁንም፡አገር፡የሚያ
ጠፉ፡ሃይማኖት፡የሚለ
ውጥ፡ጠላት፡እግዚአብ
ሔር፡ደጋሰነልኝ፡ባሕ
ር፡አልፎ፡መጥቷል፡እኔ
ም፡ያገሬን፡ከብት፡ማ
ለቅ፡የሰውን፡መድከም፡
አይቼ፡እስካሁን፡ዝም፡
ብለው፡ዲግሞ፡እያለፈ፡
እንደፍልፈል፡መሬት፡
ይቆፍር፡ጀመር፡አሁን፡
ግን፡በእግዚአብሔር፡
ረዳትነት፡አገሬን፡አሳ
ልፌ፡አልሰጠውም፡ያ
ገሬ፡ሰው፡ካሁን፡ቀደም፡
የበደልሁህ፡አይመስለ
ኝም፡አንተም፡እስካሁ
ን፡አሳስቀየምኸኝም፡
አሁንም፡ጉልበት፡ያለህ፡
በጉልበት፡እርዳኝ፡ጉ
ልበትም፡የሌለህ፡ለል
ጅህ፡ለምሽትህ፡ለሃይ
ማኖትህ፡ስትል፡በሓዘ
ን፡እርዳኝ፡ወስልተህ፡
የቀረህ፡ግን፡ኋላ፡ትጠ
ላኛለህ፡አልተውኽም፡
ማርያም፡ን፡ለዚህ፡አ
ማላኝ፡የለኝ፡ም፡ዘመቻ
ዬ፡ም፡በጥቅምት፡ነው፡ና፡
የሸዋ፡ሰው፡እስከ፡ጥቅም
ት፡እኩሌታ፡ድረስ፡ወረይ
ሉ፡ከተተህ፡ሳላኝህ፡



ልብ ወለድ

❖ አዳምና ሔዋን
"ዕጣዬ"

❖ ኑሮ በአሜሪካ
"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!"

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine
(Amharic is the official language of Ethiopia)
April/May 1996
Vol. 4. No.5

"በመስታወት ቤቶች የሚኖር በሌሎች ላይ
የመጀመሪውን ድንጋይ ወርዋሪ ይሆንም!"
ረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና (ገፅ 32)

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE
### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ካሊፎርኒያ ማርት
# በአትላንታ

1996

1996

## CALIFORNIA MART *IN ATLANTA*

**2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD**
**ATLANTA, GA 30324**

**የምግብ ሸቀጣሸቀጥ**
**GROCERIES**

| | |
|---|---|
| እንጀራ | Injera |
| ጤፍ | Teff |
| በርበሬ | Berbere |
| ሽሮ | Shirro |

ወዘተ

**የተለያዩ ሸቀጦች**
**መደብር**
**አራት ዓይነት ንግድ**
**በአንድ ቦታ**

**የመዝናኛ ክፍል**
**GAME ROOM**

| | |
|---|---|
| ካራምቡላ | *Biliard* |
| የጠረጴዛ ኳስ | *Table Tennis* |
| ሙዚቃ | *Music* |

ልዩ ልዩ መዝናኛዎች

ይደውሉልን




ይጎብኙን

**የስጦታ መደብር**
**GIFT SHOP**

| | |
|---|---|
| ስጦታዎች | *Gifts* |
| ጌጣጌጦች | *Jewelery* |

ወዘተ

**4 BUSINESS IN 1**

**ምግብ ቤት**
**RESTAURANT**

ቁርስ ፉል፣ ግንፍልፍል፣

ምሣና እራት ክትፎ፣ ጥብስ፣

ወዘተ

Mail Order Available
Please, call for Arrangements

(404)320-6747
(404)320-9082

CAPPUCCINO

ESPRESSO

ORDER FOOD
TO GO!!

# ማ ው ጫ

# CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከአገር ቤት (ከወርቃየሁ)

5 ሰላምታ ከባህር ማዶ ከይግለጡ ለወርቃየሁ

8 ከአንባብያን

10 እንዲህ ሆነ (ዜና)

12 ጥንቅር - ከዚህም ከዚያም

15 ልብ ወለድ
"ከሥራ መልስ" ከዓለማየሁ

19 የአድዋ ድል 100ኛ ዓመት
አጭር የአድዋ ታሪክ (መርዕድ ዓለማየሁ)
እቴጌ ጣይቱ (ሣራ ታከለ)
"አድዋ የአርበኞች ቀን" (ልሣኑ ስምረት)
"ኢትዮጵያዊነት ሲያኮራ" (ቴዎድሮስ ጥላዬ)

29 "ታሪክ ከዜናዎች ሲፈልቅ" (ሰይፉ መኩሪያ)

32 የውይይት መድረክ
"በመስታወት ቤት የሚኖር . . ." (መረራ ጉዲና)

39 አዳምና ሔዋን
"ዕጣዬ" (አብርኸት)

42 ኑሮ በአሜሪካ
"እንድረስላቸው!" (አንዋር አህመድ)
"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ" (አትናትዮስ)
ከአካባቢያችን




በአትላንታ የአድዋ በዓል



ከንቲባ ቢል ካምብል
ከኢትዮጵያውያን ጋር




ሽፋን አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ + የምኒልክ ኢዋጅ



"ላንዳፍታ" የግል መጽሔት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪ ዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1996

ላንዳፍታ
ሚያዝያ/ግንቦት ፲፱፻፹፰
፬ኛ ዓመት ቁጥር ፲
LANDAFTA
April/May 1996 V. IV- No.4

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editors:**
*Workayehu* (pen name)
*Girma Zegeye*

**Contributors:**
*Setfu Mekuria*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
ET. Beauty Supply
Bati Grocery
L.A., CA
Merkato
Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Emebet Worku
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Addis Cafe
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Houston
Queen Sheba Rest.
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Merkato Market
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax
(404)728-9122
E-MAIL
mgessesse@aol.com

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከረማችሁ። እኛ ደህና ነን። በዓለም ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ትልቅ ምዕራፍ የያዘው የአድዋ ድል መቶኛ ዓመት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው የዓለም ክፍላት በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል። ለአፍሪካ ሕዝቦች በኮሎኒያኒዝም ላይ ድልን ያጎናጸፈ ይህ ታላቅ የድል በዓል በታሪካዊነቱ ብቻ የሚታወስ ሳይሆን በአሁኑ ወቅት ብዙ የአፍሪካ አገሮች ላለባቸው የጎሣና የዘር ክፍፍልና ግጭት የአንድነትን ጥቅም በጉልህ የሚያስተምር መሆኑም ጭምር ነው። የብልሁ ምኒልክና የጣይቱ የአመራርና ሕዝቦችን በፍቅርና በአንድነት መርቶ ጠላትን የማሸነፍ ልምድ የአሁኑም ሆኑ የቀድሞ የኢትዮጵያ መሪዎች ትምህርት ሊሆናቸው በተገባ ነበር። መሪዎቹ ሳይሆኑ ሕዝቡ አንድነቱን ተሃድሶ ያደረገበት በዓል እንደነበረ በየቦታው በተካሄዱ ዝግጅቶች ላይ የታዩት ሁኔታዎች ምስክሮች ናቸው። የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችንም ይህንን ታላቅ በዓል መታሰቢያ በዓል በማስመልከት ልዩ ዝግጅት ይዞ ቀርቧል።

"እነዚህ ልጆች የሚፈልጉት ምንድነው?" በማለት ለጥቂት ዓመታት ግራ ያጋባንን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሹማምንት አነሳስና ዓላማ ፍርጥርጥ አድርገው የፖለቲካ ሣይንስ ምሁር ረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና በጦቢያ መጽሔት ላይ ያቀረቡትን ጽሁፍ በብዙ አንባብያን ጥያቄ አውጥተነዋል። የዚህ መጽሔት አዘጋጅ መረራ ጉዲና በሚቺጋን ያቃረቡትን በሳል ጽሁፍ በቦታው ተገኝቶ የማዳመጥ ዕድል አግኝቷል። ያኔም ሆነ አሁን በጽሁፋቸው የኢትዮጵያ ገዥዎች ዋና ችግራቸውና ድክመታቸው ካለፉት ስህተቶች መማር መሳናቸውን እየጠቆሙ ለኦሮሞም ሕዝብ ሆነ ለተቀረው ኢትዮጵያዊ በአንድነት መኖሩ አማራጭ የሌለው መሆኑን አሳይተዋል።በዚህ አጋጣሚ የጦቢያ መጽሔትን ከልብ እናመሰግናለን። ለወደፊቱም ይህንኑ መድረክ "የውይይት መድረክ" ብለን ሰይምነዋል። "በፍቅር በሰላምና በአንድነት" ሕዝቦችን ሊያኖሩ የሚችሉ፣ ሕዝቦችን የበለጠ የሚያቀራርቡ ጽሁፎችን የምናስተናግድበት መድረክ ይሆናል።

የአንባብያንን ደብዳቤዎች የምናስተናግድበት "ከአንባብያን" የተሰኘ አምድ ጀምረናል። አስተያየቶቻችሁን ላኩልን። በዚህ እትም እንዳለፈው ሁሉ የተለያዩ ጽሁፎቻችንን ይዘን ቀርበናል።

ወርቃየሁ ከአገር ቤት ይግለጡም ከዚህ ከአሜሪካ ደብዳቤ ተለዋውጠዋል። አብረኸትም የኑሮ "ዕጣዋ" ያደረሰባትን የፍቅር ታሪክ ካለፈው የቀጠለውን አቅርባለች። አትናትዮስም ሚስት ለማግኘት ባደረገው ዘመቻ የገጠመውን ታሪክ በተከታታይ አሁንም አቅርቦልናል። እንግዲህ ድግሱ ከኛ ቀርቧል፣ እናንተስ እንላለን።

ላንዳፍታ የምትገኘው በዘንድሮው የኦሎምፒክ ከተማ በአትላንታ ስለሆነ በዚህም ላይ ሰፋ ያለ ዝግጅት ስለሚኖረን ጽሁፎቻችሁን እንጠብቃለን። የሚቀጥለው እትማችን ኦሎምፒክን በተመለከተ ሰፋ ያለ ዝግጅት ይኖረናልና እስፖርት ነክ ጽሁፎችንና ፎቶዎችን ላኩልን።

የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122
E-MAIL- mgessesse@aol.com

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን ሰንብታችኋል? እንኳን ጾመ ልጓሙን ፈቶ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለእየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ። እኛ <ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ራሱ ፆም ነው> ከሚሉት ፈላስፎች በቀር ይህን የሁለት ወር ሁዳዴ ፆም ህዝበ–ክርስቲያን እንጀቱን አስሮ በእግዚአታ፣ በፆምና በልመና ነበርና ያሳለፈው እንደእቅሚቲ ለአንድ ቀንም ቢሆን 'የሽሮ ድስት ውጣ የዶሮ ድስት ግባ' ማለታችን አልቀረም። በሌላው በሌላው ስናየው ደግሞ አዲሱ መንግስት ከገባ ይኸው አምስተኛውን የፋሲካ በዓል አክብረናል። የዘንድሮውም ፋሲካ እንደሌሎቹ ሁሉ በችግር፣ በለቅሶ፣ በሰቆቃ አሳልፈነዋል። ሺዎች ከስራ ተባረዋል፣ ሺዎች ታስረዋል፣ በሺ የሚቆጠሩ ቤቶች ተዘግተዋል። የአገሬን ሰው የዘንድሮ ፋሲካ እንዴት ነው ብትለው ከሚቀጥለው ሳይሻል አይቀርም ነው የሚል። እውነት እኮ ነው ምንም ጥሩ ተስፋ አይታይም። አምናና ካቻምና ችግሩ ያልደረሰበት ዘንድሮ በሩ ተንኳኩቷል። እንዲያም ሆኖ በጣም ጥቂት ለሆኑት ምርጥ ዜጎች ፋሲካ ፋሲካቸው ሆኖላቸዋል። የፓትሪያርኩም አባ ጳውሎስ ቃለ ቡራኬ ለብዙሀኑ ህዝበ–ክርስቲያን ሳይሆን ለእነዚሁ ይሆናል – አባትነታቸውን አባታችን ለሚሏቸው ወገኖች።

የዘንድሮውን የአድዋን 100ኛ አመት "ድል" ባለ ሁኔታ ለ2 ሰዓት በመስቀል አደባባይ አክብረነዋል። ከዚያ መልስ ደግሞ በተከታታይ ቀናት "ድሉ በተገኘበት" በአድዋ አክብረውታል። ፕሮግራሙ በአንድ አይነት ሰዎች በሁለት ቦታዎች ነበር የተከበረው። እስከ ጥዋቱ አራት ሰዓት ድረስ አዲስ አበባ ላይ ከ5 ሰዓት በኋላ ደግሞ መቀሌ–አድዋ ነበር። ሰዎቹ እንደቁመታቸው ነገሮችን ፍጥንና ቅልጥፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን ልብ ያልኩት የዛኔ ነበር። ከምኔው በምኔው አደረሳቸው ጃል! አንዳንዴ ሳስበው ይህ ፖለቲካ የሚሏት ነገር ግራ ግብት ትለኛለች። እስቲ ምን አስጨነቃቸው? ምንስ ለውጥ አመጡ?

'አድዋን ሲያነሱ ምኒልክን አይረሱ" ቢባልም ፕሬዚዳንቱ ጭራሽ ወራሪው፣ ነፍጠኛውና ጨፍጫፊው ምኒልክ እያሉ ሲደሰኩሩብን ሳይ ምነው እንደፎከሩት ጠቅላላውን እዛው አክብረውት በሆነ ኖሮና እኛው በዓሉን በሰላምና በደስታ ባከበርነው ነበር አልኩኝ። በዚያን ሰሞን የአድዋን ድል መቶኛ አመት አከባበር በማስመልከት በታሪክ አጥፊነትና ጠላትነት የቆሙ፣ በአገራቸው ክብርና ኩራት ቅንጣት ደስታ የማይሰማቸው በቀለም ኢትዮጵያውያን የነበሩ ግለሰቦች በቀለም ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ (ፕሮፌሰር ፓንክረስት ...) ምሁራን ጋር በንግግር ሲጋጩ በቴቪ መስኮት ተከታትለናል። አፍረናልም። እነዚያ የውጭ አገር ተወላጆች የሆኑ ምሁራን በኢትዮጵያ ታሪክ ተመስጠው ህይወታቸውን ሙሉ ሲያጠኑትና ሲመረምሩት የነበረው ታሪክ ዛሬ በኢንዲህ አይነቱ አሳፋሪ ዘመን ትውልድ ሲካድ ምንኛ እንዳዘኑ ከአይናቸውና ከአንደበታቸው ይነበባል።

"ኧረ ተው ሰዎች በአይናችሁ እዩበት፣
ከፉ ቀን ሲመጣ ከምታለቅሱበት።"

ብለው የታዘቡን ይመስለኛል።

ስለዚሁ ስለአድዋ በዓል በምናስብበት ሰሞን ም/ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ለኢትዮጵያ ሱማሌዎች በአካቢቢያቸው ተገኝተው 'ብትፈልጉ እዚህ ብትፈልጉ እዚያ ልትኖሩ ትችላላችሁ' የሚል የማንጠላ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ሰንብተዋል። – አጤ ምኒልክ በበኩላቸው ከዛሬ 100 ዓመት በፊት ስለ ኢትዮጵያ ዳር ድንበር በነበራቸው አስተሳሰብ ይህ <የአባቶቼ ዳር ድንበር ነው። ይህን አገር ለመጠበቅ አባቶቼ ሞተውበታል፤ እኔም እንደዛው> ማለታቸው ይጠቀሳል። የጊዜውን ርቀትና የሀሳቡን ልዩነት እናንተው ለዩልኝ። የአሁኑን ዘመን ሰውዬ አባባል አዝማሚያ ግን ምን እንደሆነ ወደፊት የሚታይ ይሆናል። አንድ ተረት አለ – ሰውየው ፀጉሩን ፀጉር አስተካካይ ዘንድ ሄዶ ሲላጭ ተላጪው ላጪውን – <ሸብቻለሁ ወይ> ቢለው <እየላጨሁ ከፊትህ ስጥልልህ ታየው የለ> አለው ይባላል። እና ወደፊት እናያለን።

እስቲ ወደ አዲስ አበባ ሽገር ልውሰዳችሁ አዲስ አበባ በ110 አመት ዕድሜዋ ያላየችው የችግር ማጥ ውስጥ አሁን ገብታለች። በእርግጥ ከማንምና ከምንም በላይ የአዲስ አበባ መውደቅና መነሳት፣ መራብና መጠማት ከነዋሪው 'ሸገሬ' ሌላ ማንስ ምን ሊል ይቻለዋል? የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሲባል ቤት ሰሪና ቤት አከራዮች ብቻ አይደሉም በቅርቡ ከተማዋ የተዋወቀቻቸው የድንኳን እና የመጋዘን (ኮንቴይነር) ነዋሪዎችዋም ናቸው። እነዚህ በየእህል ሰብል ገበያ ድርጅት መጋዘን ውስጥ ገብተው በመኖር ላይ ያሉት ሰዎችን ብንመለከት በሰፊው አዳራሽ ውስጥ አጥር የለም፣ ክልል፣ መደብ አይታይም፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ አልጋ ከአልጋ፣ ምጣድ ከምጣድ ተቀጣጥሎ ተርታውን ይኖራል። ችግር ሰዎችን ያናክሳል ቢባልም የግዴታም ፍቅር መፍጠር እንደሚቻል በዚህ ቤት ይታያል። የግሌ የሚባል ነገር የሌለበትን በታሪክ የተማርነው የጥንታዊውን የጋርዮሽን ስርአት ያስታውሱናል። ከበሽታው እሱው ይሰውራቸው እንጂ ተስቦ ከገባ ከ48 ሰዓት በላይ የሚፈጅበት አይመስልም። ከእነዚሁ እነስ የሚሉት የከተማዋ ጎስቋሎች ደግሞ

የበረንዳ አዳሪዎች ናቸው ከነውሻቸው የቤታቸው ጣሪያ ሰማይ መሆኑን በግዳቸው የተቀበሉት ይመስላሉ። በሌላው መልኩ ለአዲስ አበባ ነዋሪ ተብሎ ያኔ ለ1 ሚሊዮን ህዝብ ተብሎ የተሰሩት መፀዳጃ ቤቶች፣ መንገዶች፣ ትያትርና ሲኒማ ቤቶች፣ ሆስፒታሎች ወዘተ ምንም መሻሻልና ዕድገት ሳያሳዩ ዛሬ ከ4 እጥፍ በላይ የጨመረውን ነዋሪ እንዲያስተናግዱ ተገደዋል። – በቅርናት ሽታ የታጠሩት ሰፈሮች፣ እንደገበጣ መጫወቻ አስር ቦታ የተቆፋፈሩት መንገዶች፣ ያዘመሙ ቤቶች፣ የተፋፈጉ እና እንደማድያት ከትልቁ ህንፃ ስር የተገተሩት አሮጌ ቤቶች አዲስ አበባ እንደስሟ አዲስ ላለመሆኗ የሚቀርቡ መረጃዎች ናቸው። ዝንጀሮ እንኳ በጥዋት ተነስታ ፊትዋን የምታብስበት ውሐ አታጣም ይባላል። የሰው ልጅ ግን ከዝንጀሮ ያነሰ ውሐ ማግኘት ሲያቅተው ምን ይባላል? ኮረንቲ በማይገኝበት፣ ሻማው ቢገኝም ሞተር ሊያንቀሳቅስበት የማይቻልበት ነው። በጨለማ መኖር፣ በጨለማ መዳከር፣ በጨለማ መመራት . . . የከተማው ገዥ ክቡር ፕሬዚዳንት ተፈራ ዋልዋ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባን ባያውቋት አይገርመኝም። ለመሆኑስ ባለፉት 5 አመታት በከተማዋ ውስጥ ተዘዋውረው ኑሮአችንን በመጠኑ እንኳ አይተውት ይሆን? ወይስ ፊታቸውን በትልቁ አዲስ ዘመን ጋዜጣ እየሸፈኑ ይሆን ከቢሮአቸው የሚወጡትና የሚገቡት? ሳስበው በ1879 የተቆረቆረችው የአዲስ አበባ ከተማ የ1890 ከተማ እንኳ አልመሰለችም። ጭራሽ ወደታች እያቆለቆለች ነው።

ውድ ይግለጡ ለመሆኑ እንዴት ነህ? ዛሬ ደግሞ ከየትኛው ነህ ሳትለኝ አትቀርም። ምን ላድርግ ብለህ ነው። እኛ እንደዚህ ነን ካላልን አልሆነልንም። አንተ አሜሪካን እንዲህ አደገች፣ እንዲህ ሆነች፣ ተመነደገች እያልክ ትመፃደቅብኛለህ። እኔ ደግሞ የአገሬን ገበና ብዕሬ አልሸፍን ብላ መጥፎ መጥፎውን ብቻ (ምን ጥሩ አለ ባትለኝ) ታጋልጥ ገብታለች። <ቂም ይዞ ፀሎት የለም ባይሆን ቂም ይዞ ዲፕሎማሲ እንጂ> ታዲያ ዲፕሎማሲውን ለባለመብቶች መተው አይሻልም? አይመስልህም?

በቸር እንሰንብት!
ያንተው ወርቃየሁ ነኝ።

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከይግለጡ ለወርቃየሁ

የአገር ልጅ ወርቃየሁ እንኳን ብቅ ያልክ። የጠፋ የማይገኝበት፣ ከቤቱ በሰላም የወጣ ከማይመለስበት አገር እየኖርክ ድምፅህ ቢጠፋ፣ ብዕርህ ስሞታውን ቢያቆም ጊዜ በጣም ሰግቼ ነበር። ለካስ ደፈጣ ይዘህ፣ እኛንም ለመለካት ብለህ እንጂ ጤናህ የተጠበቀ ለመሆኑ ብዕርህ ይመሰክራል።

ምነው ምን ነክቶህ ብዬ አልወቅስህም። ደግሞ በዚህ ተቀይመህ ጭራሽ ብትጠፋስ። ዘንድሮ የአገሬ ሰው በትንሽ ነገር ሆድ ይብሰው ጀምሮአል። እንደገና ተጠናክረህ ብቅ ማለትህን ወድጄዋለሁ። የጀመሩትን አለመጨረስ የሽንፈት ወይም የእጅ መስጠት ምልክት ነውና ያቺው የተለመደች የነፍጠኞች ፉከራህን እየፎከርክ "ዘራፍ አይደፈሬ!" ብትል ይሻልሃል።

እስቲ ምን በወጣህ በጠገበ ሆዴ እነተርክሃለሁ። ሆድ ተሸክሞ ሆድ መሙያ ላጣ ሰው ጭቅጭቅ ሆድ ቁርጠት ማስከተሉን አለመገንዘቤ ጥሩም አልሰራሁ።

ወርቃየሁ መልዕክትህን በጥሞና ተመለከትኩት። እንደተለመደው በህሊና ተጉዤ ችግራችሁን ችግሬ፣ ሀዘናችሁን ሀዘን ለማድረግ ሞክሬ አልሆነልኝም። የአሜሪካ ጥጋብ ድህነትና ችግርን በሃሳብ የሚያስጎበኝ እንዳይመስልህ። ዓይነ ህሊናችን ታውሮአል። ወሬ መሰለቅ እንጂ በተግባር የህዝባችንን ችግር ማዳመጥ ከተውን ከረምረም ብለናል። ሞኝህን ፈልግ። ጊዜ ለማይለውጠው ባህርይ፣ ከትላንት ለማይማር ደካማ ፍጡር ማን ያዝናል ብለህ? በሩቁ በወንጭፍ መክረናል። እንቢ ካላችሁ ኃላፊ አይደለንም። አሁንም ተዋጉ፣ በስርዓቱ መሪዎች ላይ አምፁ አልን። አልተቀበላችሁም። ታዲያ እኛ ምን ጎድሎብን ለእናንተ እንዘን። ባይሆን ነገር ሲተራመስ ለስልጣን ሽሚያው ዋዜማ ዶሮ ሳይጮኽ ቦሌ ጠብቁን። ሩቅ ያለነው ለዚህ ለዚህማ ማን ብሎን።

ወርቃየሁ – አንዳንዴ እዚህ ያለነውን የሀበሻ ዘሮች በጥሞና ስመረምርና ስመለከት የተመሳሰለና አንድ ዓይነት መልስ ለመስጠት በብርቱ ይቸግረኛል። በውጭው ዓለም በሚኖረው ህዝባችን ላይ ለትርጉም የሚያስቸግር ትዝብት ካሳረፍኩ ትንሽ ከርሜአለሁ።

አንዳንዱ ከአንደበቱ የሚወጣው ያስደነግጥሃል። ሌላው ደግሞ ስለሀገሩ ያለውን አስተያየት ሲሰነዝርና ፍላጎቱን ሲገልጽ በተራ ፍጡርነቱ እንድታዘበው ትገደዳለህ። ሁሉም የየራሱ ፍፁም የሆነ የማይሻርና የማይገሰስ ፍላጎትና ምኞት አለው።

አንዳንዱ የሚያስበው እንደ አህያ ነው። እንዴት? ትለኝ ይሆናል። ምኞቱ ሁሉ ከራስ ጥቅም ጋር የተያያዘ፣ ለሌላው ደንታ ቢስነት የሚታይበት፣ እሱን ከደላው ሌላውን ከቁምነገር የማይቆጥር "ጭራ የለውም እንጂ" ስንት በሽንፍላው የሚያስብ አህያ አለ መሰለህ።

ሠርግ ወይም ለቅሶ አለ ሲሉት ተኳኩሎ ብቅ የሚል፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ወገኑን ከመጤፍ የማይቆጥር ጉብል እንደአሸን የፈላበት ምድር ቢኖር አሜሪካ ነው። ተሽቀርቅሮ ለመታየት፣ ከሌላው በልጦ ለመኩራራት፣ አለ እኔ ሰው ላሳር የሚል፣ ገልጠው ቢያዩት ገለባ የሆነ የአገር ልጅ በየአጋጣሚው ተመልክቶ መታዘቡ አዲስ ነገር አይደለም።

በሌላ ወገን ደግሞ እንደ ቁስላም ዝንጀሮ ራሱን ገለልተኛ አደርጎ የተቀመጠ፣ በደጉም በክፉውም ጊዜ ከማንም የማይገናኝ፣ ካለው ከቤተሰቡ ጋር ከሌለው ደግሞ ብቻውን ሰውን ሁሉ በጅምላ የጠላ፣ ቢጠሩት ብቅ የማይል፣ ተፈልጎ የማይገኝ፣ በአጋጣሚ በጎዳና ላይ የሚታይ አድፋጭ አበሻ ቁጥሩ ቀላል እንዳይመስልህ። ምነው ምን ነካህ እንዳትለው ቀርቦ አያነጋግርህም።

የአበሻ ዘር ኑሮ በአሜሪካ ብዙ አስቂኝ፣ አስደንጋጭ፣ አስደሳች፣ ግራ የሚያጋባና የሚያደናግር ገፅታ ታይበታለህ። ይህን ለምን አልክ እንደምትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ለዚህ መልስ አላጣም። ያውም በቁና።

አንዳንዱ ወደ አሜሪካ ከመጣ ብዙ ጊዜ ወይም ዓመታት ያስቆጥር እንጂ እስካሁን ድረስ በጠባይ፣ በእውቀት፣ በመሰልጠን ቅንጣት ያህል ምንም ለውጥ ሳያሳይ ያችኑ የቤቱን ባህርይ እንደያዘ ተቀምጧል።

ሌላው ደግሞ አሜሪካ በገባ ማግስት ከመልካሙ ነገር ይልቅ መጥፎውን ባህል በመቅሰም በመንገድ ላይ ቋንቋ (Street language ይሉታል) ልብህን የሚያቆስል ቁጥሩ ላቅ ያለ ነው። ከፊሉ የአሜሪካ ህልም (American dream) የሚሉት ጣራ ላይ ለመፈናጠጥ ወይ ተምሮ አልያም በአቋራጭ ገንዘብ ሊገኝ የሚችልበትን አስተውሎና አጥንቶ በአጭር ወይም በረዥም ጊዜ ህልሙ ሞልቶለት፣ ምኞቱ ተሳክቶለት ካሰበበት የደረሰ የአገር ጉብል ቁጥሩ አይብዛ እንጂ አታጣም።

ከአገሩ ከወጣ ጀምሮ ለአፍታ ያህል ከሃሳብ ሳይላቀቅ ሁሌ በሀገርና በዘመድ ናፍቆት፣ ያሰበው ዳር ሳይደርስ ያለ ዕድሜው እንደወሰራ ዶሮ ፂሙና ፀጉሩ ነጭ ያርከፈከፈበት፣ በብስጭት ግንባሩ ላይ ዘጠኝ ጅራታም መስመር የተጋደመበት ወገን በቁና ታፍሳለህ።

አገር ቤት ያሉ ዘመድና ወዳጆቹ የልጃቸውን አሜሪካ መኖር ለሚቀርቧቸው የሚተርኩለት እሱ ግን አገር ቤት ጥሎት ከመጣው ኑሮ ባነሰ ደረጃና ባልገመተው የስራ መስክ ተሰማርቶ ደፋ ቀና የሚል፣ እፍኝ ታህል ሳይሞላለት አገር ቤት ሳለ በቅርብ የሚያውቁትን እየሸሸና እየተደበቀ ለመኖር ብቻ ቀን መምሸቱን መንጋቱን እየቆጠረ የሚኖር ጉብል የአገሬ ልጅ ድምሩ የዋዛ አይምሰልህ።

ፊትህን ወደ ሌላ አቅጣጫ ስታዞር ደግሞ ለየት ያለ የአበሻ ፍጡር ታያለህ። አሜሪካ ብዙ በመቆየቱ ብቻ የሀገሩ ስልጣኔ ሁሉ ከእሱ የተረፈ የሚመስለው፣ በአዲስ መጤ ወገኖቹ ላይ ትዕቢትና ንቀት የሚያሳይ፣ ከንፈሩን ገጥሞ በጉሮሮው የሚናገር፣ ዓይኑን ጥቅሻ አይሉት ማስለምለም በጎሪጥ እያየህ የለበጣ ፈገግታ የሚያሳይህ፣ ከአለባበስ አሳማሪነቱ ሌላ ውስጡ ገብስ የሆነ፣ የቀድሞ ታሪኩን ብቻ እየተረከ ስለክቡርነቱ የሚሰብክህ፣ እሱን ካላደመጥክና በዝምታ ካልሰማኸው ክብሩን የገፈፍክና የአሜሪካ ቆይታውን ያንኳሰስክበት የሚመስለው፣ ከሆዱ ገፋ፣ ከጭንቅላቱ ፀጉሩ እስከማጅራቱ ድረስ የሸሸው "ሠው አይሉት ድንጋይ ኤሊ የመሰለ" ፍጡር ትመለከታለህ። እኔን በእጅጉ የሚቀፈኝ እንዲህ አይነቶቹ ናቸው።

ይህ እንግዲህ በአጭሩ በሰው አገር በተመሳሳይ ህዝቦች ላይ የሚታይ ደካማ ባህርይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ በመቆየታቸው በሰው አገር ያገኙትን ዕውቀትና ልምድ የሚያካፍሉ፣ ለአዲስ መጤ ወገኖቻቸው ዋስ ጠበቃ በመሆን መልካሙን መስመርና ቀናውን ጎዳና የሚጠቁሙ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ የወገናቸውን መሻሻል በብርቱ የሚመኙ፣ ባለማወቅ ብትሳሳት የሚመክሩና የሚያስተካክሉ፣ ችግር ላይ ብትወድቅ ቀድመው የሚደርሱልህ፣ በአነጋገር ረጋ፣ በስነስርዓት የደረጁ አለኝታ ወገኖች የሌሉ እንዳይመስልህ። ልታይ ልታይ አይበሉ እንጂ ሞልተዋል።

የእኛ የባህር ማዶ ኑሮአችን ከአገር ቤቱ በብዙ የተሻለ ይምሰል እንጂ ያጣነውና በቅርብ የማናገኘው ፍቅርና መተሳሰብ፣ ወግና ባህል፣ መረዳዳትና መደጋገፍ በአሜሪካ ኑሮ ላይ ጭራሽ የማታስበው ከሀገሪቱ አፈጣጠር ጀምሮ ያልዳበረና ያልነበረ ልምድ በመሆኑ ብዙዎቻችን የመልካሙ የሀገራችን ባህል ይልቅ የባዕድ አገር ቀፋፊ ልምድ ለመልመድ የምናደርገው ጥረት በእጅጉ ያሳዝነኛል።

በፖለቲካውም መስክ ያለን አመለካከት አንዳንዴ ለቅርብ ተመልካችና ለሩቅ ታዛቢ ይገርማል። በየስብሰባው የወገንን ልብ በሚያነሳሳ፣ መንፈስን በሚቀሰቅስ አንደበት ከፍተኛ የሆነ ንግግር ለታዳሚዎች በማድረግ በስተመጨረሻ የገንዘብ

እርዳታ የሚለምን፣ አገር ተከፋፈለ፣ ወገን ተጨቆነ፣ ባህልና ወግ ጠፋ፣ ኢትዮጵያዊነት ተሻረ "ወገን ዝም አትበል" የሚል ቅስቀሳ ሲያሰማ ያየኸው ሰው ለወቅቱ የሚያስፈልገውን መፍትሄ ብትጠይቀው የትጥቅ ትግል መፍትሄ መሆኑን ይነግርሃል። ግን "ማን ቀድሞ ይሙት፣ የትኛው መጀመሪያ ይዝመት" ብትለው መልስ የለውም ወይም "አንተ መንገዱን አሳየን፣ ግንባር ቀደም ሁንና እንከተልሀ" ብትለው "ቀልዳችሁን አቁሙ" ነው የሚልህ። የእሱ ዘመቻ ከአሜሪካ ትልልቅ ከተሞች አያልፍም።

ለሀገር በመቆርቆርና ህይወትን መስዋዕት በማድረግ መካከል ያለውን ልዩነት የተገነዘበ አይመስልህም። የእሱ ምሳሌዎችና የንግግሩ ማዳመቅ የሚሆኑት ግን "የቋራው ቴዎድሮስ፣ የትግሬው ዮሐንስ የሰሜኑ ዘርዓይ ድረስና አሉላ አባነጋ፣ የጣሊያኑ በረኸኛ አብዲሣ አጋ፣" ለአገራቸው ነፃነት ሲሉ መስዋዕት የሆኑት አቡነ ጴጥሮስ ምንጊዜም ምሳሌዎቹ ናቸው። እነሱ የፈፀሙትን ገድል ለመስራት ግን ወኔው የከዳው "አባ ተርሣሣ" በየስብሰባው አዳራሽ የጆሮህን ታንቡር በጩኸት ያደነቁረዋል።

ይህን ባየህበት አይንህ ደግሞ ለወገናቸው ፍፁም ተቆርቋሪ የሆኑ፣ ለሀገራቸው መስዋዕት ለመሆን በጭራሽ የማይመለሱ፣ ከልብ የመነጨ የሀገር ፍቅርና የመንፈስ ጥንካሬ ያላቸው፣ ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ በሃገሪቱ ላይ የወደቀውን ችግር ለውጭ ዜጎች፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች፣ በውጭው ዓለም በስደት ላይ ለሚኖረው ወገናቸው የሚያስጠነቅቁ፣ በግል ወጭያቸው ከሀገር አገር በመዞር ለችግራችን የጋራ መፍትሄ ለመፈለግና ሌላውን ለማስተባበር ደፋ ቀና የሚሉ ውድ ዜጎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

ወርቃየሁ የእኛ የባህር ማዶ ኑሮ ብዙ ገፅታ ስላለው እስቲ የተለያዩ ርዕሶችን በመዳሰስ እንደገና እመለሳለሁ። መልዕክቴን ያጠናቀቅሁ እንዳይመስልህ። በጥቂቱም አልነካሁት። ብዙ፣ ብዙ፣ ገና ብዙ የሚቀረኝ አለ።

ለሁሉም የአንተ ብዕር ካልነጠፈ እኔም ለመልስ ምቱ አልቦዝንምና እንጠፋፋ። እስከዚያው በቸር ያቆየን።

ይግለጡ ነኝ
ከቺካጎ /ከነፋሻዋ ከተማ/


**Allstate**
You're in good hands.

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404) 299-7287 □ FAX: (404) 299-6266

AUTO
HOME OWNER'S
RENTER'S
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO



THEODROS
HAILEGIORGIS
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indemnity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

You're in good hands.

# ከ አ ን ባ ቢ ያ ን

## « ፍቅር ሕያው ሲሆን ሀብት ግን ጠፊ ነው!!»

ፅንቁነሽ (ከሳንዲያጐ)

እንደምን ከረማችሁ የላንዳፍታ አዘጋጆች። ዝግጅታችሁ፣ ጥረታችሁ ሁሉ አስደንቆኛል። እደጉ ተመንደጉ፣ በርቱ ኃይሉንና ብርታቱን ቸሩ አምላካችን ያድላችሁ።

እንግዲህ መቼም በውጪ አገር በስደት እንደምንኖር ሁሉ የሀገራችንን የየዕለቱ ጋዜጣ፣ መፅሔቶችን ባናገኝም በእናንተ ጥረትና ዝግጅት የምትቀርበዋን ላንዳፍታ እየኮመኮምናት ነው። አንዳንዴ መጽሔትዋን እያነበብን ሲለን ፈገግ፣ አንዳንዴ ደግሞ በትዝታ ያለምንም የትራንስፖርት ወጪ በአይነህሊና አገር ቤት ደርሶ መመለስ። ኧረ ስንቱ! ታዲያ ለዚህ ሁሉ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ወርቃየሁና ይግለጡ የሚፅፏቸው ፅሑፎች ናቸው።

ወርቃየሁ ይሔ ለባለስልጣናት የሚፈነዳው ፈንጂ አንተ ጋ እንዳይደርስ በፀሎቴ እስብሃለሁ። ሌላው ውሐው፣ መብራቱ፣ በወረፋ ከሆነ የአንተም ፅሑፍ በወረፋ እንዳትለን አደራህን። ላንዳፍታዎች – ባለፈው መፅሔታችሁ ላይ "የእናንተ ትብብር ሬሳ እስከመላክ ድረስ ነው" ብሎ ከአገር ቤት የተናገረው ሰውዬን ፅሁፍ በሳቅ ያለፋችሁት ስንቶቻችሁ ናችሁ? ነገሩን በማጤንስ ትክክለኛ አነጋገር በመሆኑ ዘር ይውጣልህ ያላችሁስ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እስቲ በስደት ዓለም ያለን ሁሉ ነገሩን እናጢነው ባይሆን መልስ ለመስጠት እንድንችል መልሳችን ሬሳ ብቻ እስከመላክ ሳይሆን የምንወዳት ኢትዮጵያ አገራችንን እስከመገንባት ነው የምንለው መቼ ይሆን?

ላንዳፍታዎች – ፍቅርና ጋብቻ በአሜሪካ (ከዮሐንስ ገ/ህይወት) የተፃፈውን ፅሁፍ ተደስቼበታለሁ። እንዳንተው ሁሉ እውነት የሚናገሩ የአገር ልጆች ቢኖሩን የወንዱንም የሴትዋንም ችግር በይፋ አውጥተህ አስረድተሃል። እኔም በአሜሪካ ላይ ያየሁት ነገር ቢኖር እውነተኛ ፍቅር መታጣቱ ነው ሴቷ፣ ወንዱ፣ ለትዳት ሲጠይቃት የመጀመሪያው ጥያቄዋ ከመጣህ ስንት ጊዜህ ነው፣ ስራህ ምንድነው? ቤት አለህ? መኪናስ? የባንክ አካውንቱስ? አሁን ደግሞ የመጣው በሽታ ዘርህ ምንድነው? ኧረ ስንቱ? ወንዱም ሲጠይቅ ተምራለች? ስራ አላት? ገንዘብ አላት? ወዘተ እውነተኛ ፍቅር ሳይሆን የጥቅም ገበያ በለው። ይህን ነው ያየሁት ዮሐንስ ይህቺ ጠቃሚ ፅሁፍህን ስለምናፍቃት በርታ እግዚአብሔር ያበርታህ። እውነተኛ ፍቅር የምትገኘው ከየት ይሆን?

እውነተኛ ፍቅር የሚገኘው (Boyfriend or Girlfriend) ተብሎ በንፁህ ፍቅር የተጀመረ፣ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ የሚባለውን እሱም ስለእስዋ ጥሩ ሲመኝ፣ እስዋም ስለእሱ ህይወት ስታስብ አብሮ ሰርቶ ኑሮን በብልሃት ሲያልፉ እንጂ ሀብት ፈልጎ መግባቱ አያዋጣም። ንፁህ ፍቅርም አይገኝም። የአገሬ ልጆች በዚህ አስቡበት ፍቅር ህያው ሲሆን ሀብትና ንብረት ግን ጠፊ ነው። ላንዳፍታዎች በሉ ቸር ይግጠመን።

■■■■■■■■■■■■■■■■

## እንደእኔ ታዝባችኋል?

ካሣሁን ነኝ ከቺካጐ

ይገርመኛል የእነኚህ አሜሪካን ጋዜጠኞች ነገር። ትንሿን ነገር ትልቅ አድርገው ያቀርቡና የአንድ ሰሞን ትልቅ ዜና ያደርጉታል። አንዳንዴ ሳስበው አሜሪካንን የሚያስተዳድረው ነጩ ቤተመንግስት (white house) ሳይሆን ጋዜጠኞች ናቸው እላለሁ። እነ ፒተር ጄኒንግስ፣ ቴድ ካፐልና የመሳሰሉት ምን ያህል በአሜሪካ ባለሥልጣናት እንደሚከበሩ (እንደሚፈሩ ብል ይሻል ይሆን) ታውቃላችሁ። ይህ ሁሉ ሆኖ ታዲያ አንዳንድ ብዙውን (ተራውን) ሰው የማይመለከቱ ዜናዎች ከመጠን በላይ ተጋነው ይቀርቡና ጆሮአችንን ሲያሰለቹ ይከርማሉ።

ለምሳሌ፣ የዳያና ከባሏ ልዑል ቻርልስ መለያየት የኒውስ ዊክን ሽፋን ይዞ ሲወጣ፣ . . . አንድ ባልና ሚስት አብረው ኖሩ፣ አልተግባቡም ተፋቱ፣ ታዲያ ምን ይጠበስ? አምና ደግሞ እዛ ወደናንተ አካባቢ ፍሎሪዳ መሰለኝ አንዲ በቅናት ነው መሰለኝ የባሏን እንትን ቆርጣ ጣለችለት ተብሎ ጉድ ሲባል ከረመ። በዚያ ሰሞን ዓመት ሙሉ ሲያደነቁረን የከረመው የኦጄ ሲምፕሰን ጉዳይ፣ . . . እንዳንድ ትልቅ ብሔራዊ ጉዳይ ነበር ይታይ የነበረው። ስንት የዓለም ጉዳይ እያለ፣ ስንት ብዙ ሰው የሚመለከት ጉዳይ እያለ እንዲህ ባለ ተራ ወሬ የሰውን አዕምሮ ለምን እንደሚያደነዝዙት አይገባኝም።

ሰው ወሬ ስለሚወድ ነው ወይስ ጋዜጠኞቹ ሌላ የሚወራ አጥተው? የዚህ አሜሪካ ፕሬስ ጉዳይ ሲገርመኝ ይኖራል። እናንተንስ?

■■■■■■■■■■■■■■■■

## በቫሌንታይን ቀን
## ብቻዬን ተከራምቼ አመሸኋት!

(የሺመቤት ነኝ ከሳንዲያጐ)

ሰላም ላንዳፍታዎች እንደምን ከርማችኋል። ለመሆኑ አዲስ ደንበኛ ትቀበላላችሁ? ለማንኛውም እውነተኛ ታሪክ ነውና እንደሚጣፍጥ አድርጋችሁ አቅርቡት። እኔ ግን ተሰጥዖ ስለሌለኝ ሀሳቤን ሁሉ በአንድ ቦታ አስፍሬዋለሁኝ። ስሙን ፈረንጆች Valentines Day (የፍቅረኞች ቀን) ይሉታል። ያደላቸው። እኔ ግን ለራሴ ይህችን ቀን እንደሌሎቹ ተራ ቀን እንኳን ማሳለፍ አልቻልኩም ነበር። በዚህ የተነሳ ቀኑን Black Day (የጨለማ ቀን) በማለት ለራሴ ሰየምኩት። ለምን? ቀኑ Feb. 14 Valentine day ነው። ሰው ሁሉ Post Card, Flower (አበባ)፣ ፅጌረዳ፣ ቀለበት፣ ባሉን የመሳሰሉትን ይዞ ሽርጉድ ይላል። እኔ ግን ከት/ቤት በጊዜ ተመልሼ ቤት ነኝ። ለማጥናት ፈልጌ ደበረኝ። TV ስከፍት valentine day በመሆኑ የታደሉት በTV ስጦታ ሲሰጣጡ፣ surprise እያሉ የሴት ወይንም የወንድ ጓደኞቻቸውን ሲያስደስቱ የመሳሰለውን ያሳይ ጀመር። ተናድጄ TVውን አጠፋሁኝ። አይገርማችሁም ስራ እንኳን እንዳልሄድ ዛሬ እረፍት ነኝ። እስቲ ለማንኛውም ብዬ ከመፅሐፉ መደርደሪያ ላይ እጄ ያነሳውን መፅሐፍ ይዤ መኪናዬን እየነዳሁኝ ወደ ፓርክ ሄድኩኝ። ከቀኑ 12 ሰዓት ስለነበር ፀሀዩ ሃይለኛ ነበር። እኔም ጥላ ቦታ ፈልጌ መኪናዬ ፓርክ አደረግሁኝና ከመኪናው ሳልወጣ ለስላሳ ሙዚቃ ከፍቼ የያዝኳትን መጽሕፍ በማንበብ ለ2 ሰዓት ያህል ቆየሁኝ። እንደአጋጣሚ ሆኖ መፅሐፉ የሚጥም ነበር "Special Treatment" ይላል፤ ደራሲውም Penny Jordan ነው። ትንሽ ድካም ስለተሰማኝ እስቲ በእግሬ ዞር ዞር ልበልም ብል በፓርኩ ውስጥ እኔ ብቻ ነኝ ብቻዬን የምዞረው። ትንሽ አሰብ አደርግሁኝ፤ ተናድጄ ወደመኪናዬ ተመለስኩኝ፤ ይሻለኛል ብዬ movie ለመግባት ብሄድ እዚያም ሰው ሁሉ ጥንድ ጥንድ ነው። ከእኔ በስተቀር። አገሬ ኢትዮጵያ ቢሆን እንደዚህ የሚደብሩ ቀናት ሲያጋጥመኝ ቤተክርስቲያን በመሄድ ጸሎት ማድረግ፣ ትምህርት መስማት የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች የሚያቀርቡትን መዝሙር መስማት፣ ኧረ ስንቱ! ወይ አገሬ! በስንቱ ትናፍቂኛለሽ። I miss my country very much! አሜሪካ ተበልቶ ተጠጥቶ ይታደራል። ሆድ ቢጠግብ መንፈስ ካልተደሰተ ምን ዋጋ አለው። እውነተኛ የፍቅር ጓደኛ የሌለበት፣ ሰው ሁሉ እንደእኔ ተቸግሮ ይሆን? ለዚህ መቼም ከፍተኛ ፀሎት ያስፈልገዋል። ለነገሩማ እኔም አሜሪካ ከመጣሁ ጥቂት አመታትም ቢሆኑ እዚህ ከመጡ ለቆዩት ወንድሞቼና እህቶቼ አስባለሁኝ። ከሁሉም ይልቅ ግን ራስን መጀመሪያ መጠየቅ እኔስ ማነኝ? በሉ የእናንተን ብታካፍሉኝ ደስ ይለኛል። ቸር ይግጠመን።

## "እባካችሁ አንብቡኝ"

(ትዕግሥት ሁሴን ከሪያድ)

ሃሎ! መቼም በመጀመሪያ የሰላምታ ደብዳቤዬን ከባህር ማዶ ለማሻገር ብዕሬን አንስቼ ከወረቀት ሳገናኛት መቼም እናንተ ውድ የአገሬ ልጆች በአይን ያገኘሁዋቸው እየመሰለኝ ነው። በመጀመሪያ ራሴን ላስተዋውቃችሁ ትዕግስት ሁሴን እባላለሁ የምኖረው በሳውዲት አረቢያ በሪያድ ከተማ ነው። ይህቺን መፅሔት በአጋጣሚ በ1995 ወደ አሜሪካ ለሰመር ጉብኝት ከአሰሪዬ ጋር ሎሳንጀለስ ከተማ Bevery Hills የሚባል አካባቢ ለትንሽ ጊዜ ብቅ ብዬ ነበር። ታዲያ አንድ አበሻ አግኝቼ የአገራችንን ወሬ የሚያወሱ መጽሔቶች ካሉሽ እስቲ ጀባ በይኝ ስላት ላንዳፍታ የምትል በጣም የምትጥም አንብቢያት የማልጠግባት መጽሔት አውጥታ ሰጠችኝ። በጣም ደስ ስላለኝ ለመገናኘት ብፈልግም ብዙም ሳንቆይ አገሩን ለቀን ወጣን ነገር ግን መፅሔቷን ይዤ መጥቼ ስለነበር እስኪ በደብዳቤ ካገኘሁዋቸው ብዬ ፃፍኩኝ።

እና ላንዳፍታዎች እንደምናችሁ እስቲ ምነው ወደ አሜሪካ አውሮፓ ብቻ ሳይሆን ወደ ሚድል ኢስት ጎራ በሉ። ይኸን ስላችሁ እኛ በአረቡ አገር ያለን ውድ የአገራችሁ ልጆች በጣም ነው የአገር ልጅ ሽታ እንደ ውሃ የሚጠማን። በተለይ ይህ ፖለቲካ የሚባል ነገር በጣም ነው የበጠበጠን። ለምሳሌ እኛ ባለንበት በሪያድ ከተማ ኤርትራ፣ አበሻ እየተባባለ ግራ ነው የገባን። እኛ የምናውቀው ኢትዮጵያ አንድ መሆኗን ነበር። አንድ ባህል፣ አንድ ቋንቋ ይዘን ዛሬ በሰው አገር አይንህ ላፈር ስንባባል ምን ትሉታላችሁ? እስቲ ይኸን ሕዝብ አንድ መላ በሉት። ወደ ዋናው ቁምነገር ልግባና ይቺን መጽሔታችሁን በጣም ወድጃታለሁ፤ በምን አይነት መንገድ ነው የማገኘው ማለትም ስርጭታችሁ ከሚድል ኢስት ውጭ ነው? እባካችሁ መልሱን ስጡኝ። በተረፈ ምላሹን በጉጉትና በናፍቆት የምንጠብቀው ውድ የአገራችሁ ልጅ በሶስተኛው እስር ቤት በሳውዲት አረቢያ በሪያድ ከተማ የምገኝ እህታችሁ ነኝ። ትዕግሥት ሁሴን።

ከአዘጋጁ ትዕግሥት በአድራሻሽ ያለፉትን እትሞች በብዛት ልከንልሻል

## ውድ አንባብያን

በቀረቡ ጽሁፎች ላይም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ያላችሁን አስተያየቶችም ሆኑ ጥያቄዎች ላኩልን። በዚህ ከ"አንባብያን" በተሰኘ አምድ እናስተናግዳችኋለን።

# እንዲህ ሆነ

## የቀድሞ የደርግ ባለስልጣናት ጉዳይ መታየት ጀመረ

በቀድሞ የአገሪቱ መሪ ከነበሩት ኮ/ል መንግስቱና ወደ 69 የሚደርሱ አጋሮቻቸው 'ዘር በማጥፋት' የተመሰረተባቸው የክስ ወንጀል ለተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ ቆይቶ በቅርቡ መታየት ጀምሯል።

የእንግሊዙ የዜና አውታር ባደረገው ቃለ ምልልስ ኮ/ል መንግስቱ 'ቀደም ሲል እኔን ሲወጉ ከነበሩት ኃይሎች ጋር ፊት ለፊት ቆሜ መዳኘቱ ለእኔ አሳፋሪ ነው። እኛ የእርበኝነት ግዳጅ ተወጥተናል።" በማለት በአዲስ አበባ የተቋቋመውን ፍ/ቤት እንደማይቀበሉትና በየትኛውም ዓለም ላለው ፍርድ ቤት አመኔታ የለኝም በማለት ቁርጥ ያለ ውሳኔያቸውን አክለው ገልፀዋል።

የፍ/ቤቱን ውሎ ይከታተል የነበረው ዘጋቢ የባለስልጣናቱ ጉዳይ ከፍተኛ የህዝብ ትኩረት በመሳቡ የችሎቱ ግቢ በሰው ብዛት የተጨናነቀ መሆኑን ገልፆ ችሎቱ በጋዜጠኞች ላይ የነበረውን አቋም ሲገልፅ የግልና የመንግስት ጋዜጦች፣ የቪድዮ፣ የቲቪ፣ የካሜራ ሰዎች በችሎት ውስጥ ያለውን የምስክር እማኝነትንም ሆነ ዳኞች ምን እንደተናገሩ ጠቅሶ መዘገብ እንዳልተፈቀደና ጋዜጠኞች ስለአጠቃላይ የፍ/ቤቱ ሁኔታ እንጂ ጥልቅ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ማብራሪያ እንዳይሰጡ የህግ አንቀፅ ተጠቅሶ ማስጠንቀቂያ የተላለፈ መሆኑም አሳውቋል።

## ግብፅ ከሱዳን ጋር እየተወዳጀች ነው

አ/አበባ ውስጥ በግብፁ መሪ ሆስኒ ሙባረክ ላይ በተቃጣው የግድያ ሙከራ የተነሳ በኢትዮጵያና በግብፅ መንግስታት አማካኝነት ተነጣጥሮ የነበረው ውንጀላ በተመድ የፀጥታ ምክር ቤት ሲብላላ ቆይቶ በተመድ በኩል በተሰነዘረው የማዕቀብ ጉዳይ ላይ የሱዳን 'ቁስለኛ' የሆነችው ግብፅ በሱዳን ላይ የፖለቲካ መሳሪያ ማዕቀብ እንጂ የኢኮኖሚ ጫና እንዳይደረግባት በምክትል የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯ አማካኝነት አቋሟን በማስረዳቷ የካርቱምን መንግስት ማስፈንደቁ የተመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል ኢትዮጵያ በሱዳን ላይ በጦር መሳሪያ ሽያጭና በትራንስፖርት ኢኮኖሚ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ለተመድ ጥያቄ ማቅረቧ ሲገለፅ የሁኔታዎች እንደዚህ መሆን ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ታላቅ የራስ ምታት እየሆነባቸው መምጣቱ ተገልጿል።

## አቡኑ በየጊዜው የሚነሷቸው ፎቶግራፎች ዓለማዊነትን የሚያንፀባርቁ ናቸው ተባለ።

ባለፈው መጋቢት 3 ቀን 1988 ዓ.ም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ክብርና ዝናን እንኳሶና አሳንሶ የመለኮትን ባህሪ በማፋለሱ "ፀረ ማርያም" ተሰኝቶ በሰላማዊ ሰልፍ የተወገዘው በፓትርያርኩ ትዕዛዝ ተፃፈ የተባለው መፅሀፍ <የእንግሊዝኛው እትሙ> አንዳንድ ገፆች እየተቀደዱ ከመፅሀፉ በመውጣት ላይ እንደሚገኝና መፅሀፉ ከገበያ ተገልሎ የውስጥ ስራዎች እየተካሄዱበት መሆኑ ተገልጿል።

የሰላማዊ ሰልፉ ዋና ዓላማ ይህ ቢሆንም በተጓዳኝ ፓትሪርያኩ የሚያሰሩትና ለጊዜው ወደ 35 ሚሊዮን ወደማለቂያው ደግሞ ወደ 40 ሚሊዮን ብር ይፈጃል የተባለው <Patriarch Palace> ጉዳይ ለመቃወምም ነበር። ተቃዋሚዎቹ ሰልፈኞች እንደሚሉት ስንት በየገጠሩ ያሉና ብዙ ቅርሳ ቅርሶችን በውስጣቸው የያዙ አብያተክርስቲያናት በገንዘብ ችግር ምክንያት ተዘግተው፣ ጣሪያቸው በማፍሰሱ ቅርሶቹ ከጥቅም ውጪ እየሆኑ ባለበት ወቅትና እንዲሁም ከዚሁ ከአዲስ አበባችን ሳንወጣ አጠገባቸው ያለው የቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን አርጅቶ ጣሪያው ውሐ በማፍሰስ ባለበት ጊዜ እሳቸው ለዚህ ቅድሚያ መስጠታቸውን በእጅጉ አውግዘዋል።

በተያያዘ ዜናም በርካታ የቤተክርስቲያኑ የአንድ ጎሳ አባላት በተለያዩ ጊዜና ቦታ የተነሱት አለማዊ ፎቶግራፎቻቸው ሲታዩ ጭራሽኑ ለቤተክህነት አመራርም ሆነ ለአባትነት ያበቋቸዋል የሚባለውን ጥርጣሬ ውስጥ የሚከተው ሲሆን እነዚሁ ፎቶግራፎች በአንዳንድ የግል ጋዜጣዎች በተከታታይ እትም ከድሮዎቹ ከእነአቡነተክለሃይማኖትና ከመሳሰሉት ጋር በንፅፅር ለትዝብት እየወጡ ነው።

## ትግሪኛ ቋንቋ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መመዘኛ መሆኑ አድሏዊ ነው ተባለ።

የትግሪኛ በብሔራዊ ፈተና ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መመዘኛ ሆኖ በመቅረቡ የክልሉ ተናጋሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በቀላሉ ለመግባት ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያኖች የተሻለ ዕድል እንዲኖራቸው መደረጉ አድሏዊ አሰራረ መሆኑን በርካታ ተፈታኞች ገለጡ።

ይህንኑ በተመለከተ የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ፅ/ቤት ዲሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መግለጫ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ትግሪኛ ለብሔራዊ ፈተናነት እንዲቀርብ ከት/ሚር ስለተፃፍልን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በትምህርትነት መሰጠቱን እያረጋገጥን በታዘዝነው መሰረት ፈተና አዘጋጅተናል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ በትግራይ ክልል ከሌሎች የተሻለ የልማት እንቅስቃሴ መደረጉ አንሶ እንደገና ከሌሎች አካባቢ የተሻለ የትምህርት ዕድል ለነበረው አካባቢ ተጨማሪ ዕድል መሰጠቱ አድሏዊ ነው ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ይተቻሉ።

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ጀመሩ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ማኔጅመንት ለሰራተኛው ይሰጥ የነበረውን ነፃ የአየር ትኬት ኮታ መቀነሱና ነባር ባለሙያዎቹን መዋቅር አፋቀፈችሁም በሚል ሰበብ ዕድሜያቸው ለጡረታ ሳይደርስ በገዛ ፈቃዳቸው በጡረታ እንዲገለሉ በማድረጉ በሰራተኞች ዘንድ ተቃውሞ ያስነሳበት መሆኑ ተገለጠ። የድርጅቱ ማኔጅሙንት የነፃ ትኬትን አስመልክቶ በአዲስ መልክና በፖሊሲ ደረጃ አስጠናሁ ብሎ ይፋ ያደረገውን ይህንኑ ደንብ በተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚገኙ የአየር መንገዱ ሰራተኞች የአቤቱታ ነጥባቸውን በፊርማቸው በማረጋገጥ ተቃውሞአቸውን በሰራተኛው ማህበር በኩል ያቀረቡ መሆኑ ታውቋል።

አየር መንገዱ ለረጅም አመታት ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ ያስተማራቸውንና ድርጅቱንም ለዚህ ከፍተኛ ደረጃ ያበቁትን ነባርና እውቅ ባለሙያዎቹን በየምክንያቱ እያባረረ ባለበት በአሁኑ ወቅት አዳዲስ ሰራተኞች ለማሰልጠን በየቀኑ የቅጥር ማስታወቂያ ማውጣቱና ምልመላ እያካሄደ መገኘቱ ብዙዎችን አስገርሟል።

የተመሰረተበትን 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዮ በዚህ ወር ለማክበር ከፍተኛ ገንዘብ መድቦና ዝግጅት በማድረግ ላይ ቢሆንም እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሱትን ባለውለታዎቹን መንከባከብና መሸለም ሲገባው ሽልማታቸው የመብት ገፈፋና መባረር መሆኑ ብዙዎችን እያነጋገረ ነው። በሌላ በኩል ለብዙ አመታት ቋሚ ደንበኞቹ የሆኑት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሰራተኞች የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚያደርስባቸው የተለያዩ መጉላላቶች ደንበኝነታቸውን ለማቋረጥ ከሚገደዱበት ደረጃ መድረሳቸውን ለአየር መንገዱ ማኔጅመንት በተደጋጋሚ በጽሁፍ ያስታወቁ ቢሆንም ምንም እርምጃ ባለመወሰዱ በሌሎች አየር መንገዶች እንዲገለገሉ የድርጅታቸውን ፈቃድ እንደሚጠይቁ አስጠንቅቀዋል።

# ኤድስ በፀበል ተመታ ተባለ!

## በበሽታው ምክንያት ያጣቸውን ቪዛ አገኘች

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ተአምር በመዲናችን ሆስፒታል በተፈፀመ ማግስት አንዲት በእምነቷ የፀናች፣ የማለእክትንና የሰማዕታትን ተራዳኢነት ያመነች ወጣት ከተቀራኛት የኤድስ ቫይረስ በሽታ በፀሎት መዳኗ ታወቀ። ይህች በወረዳ 2 ቀበሌ 13 ነዋሪ የሆነችው ወ/ት ፀሐይነሽ ይመር በሐምሌ ወር 1987 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ውጭ ለስራ ለመውጣት የሀገር ውስጥ ዝግጅት ስታደርግ በህክምና የኤድስ ቫይረስ እንዳለባት ይነገራታል። ይህን የተረዳችው ወጣት 'እኔ ከኃጢያት ለመዳን ፈጣሪዬን ምህረት መጠየቅ ስላለብኝ ንስሃ መግባት አለብኝ' በማለትና ሁለት እህቶቿን ደግሞ በፆምና በፀሎት ትረዱኛላችሁ ብላ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ትሄዳለች። ከዚሁ ቤተክርስቲያን በሰው አማካኝነት የነፍስ አባት ትይዝና ኃጢያቷን በሙሉ ለቄሱ ተናዛ ንስሐ በመግባት ያዘዟትን የተለያዩ ሱባኤዎች ሁሉ በመፈፀም ቄሱ ይበቃሻል ባሏት ጊዜ እንደገና ለምርመራ ደሟን ክሊኒክ ሄዳ ትሰጣለች። ከትንሽ ቀናት በኋላ ከበሽታው ነፃ የመሆኗ መረጃ በፖስታ ታሽጎ በማግኘቷ በኤድስ ቫይረስ ምክንያት አቋርጣው የነበረውን የውጪ ጉዞዋን በእግዚአብሔር እርዳታ በመቀጠል ወደአሰበችው አገር ለመሄድ መቻሏን ልጅቱ በተለያዩ ቤተክርስቲያናት በአካል እየተገኘች ምስክርነቷን የሰጠች መሆኑ ተረጋግጧል።

# ጥንቅር ከዚህም ከዚያም

(በሀገር ውስጥ ከታተሙ የግል ጋዜጦች የተጠናቀረ)

* የአዋሳ ከተማ ህዝብና ፖሊስ እጅና ጓንት ሆኑ ሲል ኢ.ዜ.አ ያሰራጨውን ዜና ምን ትለዋለህ?

ስንዱ - ከመርካቶ

● ከሰሞኑ ደግሞ ጓንቱን ያጠለቅኩላቸው እኔ ነኝ እንደሚለን አይጠራጠሩ።

* * *

* ከፕሬዚዳንት አልበሽር በስተጀርባ ሱዳንን የሚመሯት (አልቱራቢ ናቸው) ያላቸኋት ትኔ እስካሁን አልገባኝም።

ታፈሰ - ከመናኸሪያ

● ከፕሬዚዳንት ነጋሶ በስተጀርባ ኢትዮጵያን የሚያሽከረክሯት ጠ/ሚ/ሩ ናቸው ያልን መስሎዎት ዘባርቀው ዘብጥያ ቢወርዱ እኔ የለሁበትም።

* * *

* ሰሞኑን የኤርትራ ኢንትሬዎች ባዶአቸውን እየገቡ እየጫኑ የመውጣታቸው ምስጢር ምን ይሆን?

አልማዝ - ከ6 ኪሎ

● በዝግ ስብሰባ የተደነገገ የወዳጅ አገር 'ሊሴ ፓሴ' (የመውጫ ፈቃድ) ይሆን?

* * *

* ፕሬዚዳንት ክሊንተን ግብፅ ደርሰው ምነው እኛ አገር ጎራ ሳይሉ ቀሩ?

መለሰ - ከመርካቶ

● እነ እንቶኔን እጅ ማሳም ለምደው እንዴት ብለው ይመጣሉ ብለው ነው።

* * *

* ሮበርት ሙጋቤ ዚምባብዌን ዳግም ለ6 ዓመታት እንዲመሩ መመረጣቸው ምንን ያመለክታል?

ከቤ - ከቄራ

● የኢሕአዴግና የኮ/ል መንግሥቱ መነፋፈቅ ዕድሜውን ማራዘሙን ይሆን?

* * *

* መከላከያ ሚ/ሩ ኦጋዴን ውስጥ አክራሪዎች መኖራቸውን እያመኑ ተዋጊዎቹን "ተራ ሽፍቶች" ያሉበት ሁኔታ ግልፅ አልሆነልኝም።

መሀሪ - ከኮልፌ

● ከጥንቱ የበረሃ ውሎአቸው ጋር ሲያመዛዝኑት ልባቸውን ስላላረካቸው ይሆን?

* * *

* ዶ/ር አብዱል መጂድ ምነው ድምፃቸው ጠፋ?

ሻሾ - ከቀበና

● ቀስ ብለው ደግሞ 'በቅንነሳው ማዕበል ሊጠረጉ ነው' እንዳይሉኝ ሰጋሁ።

* 'የዓለም የውሐ ቀን' የሚል ፖስተር ሰሞኑን ተለጥፎ ያየሁ መሰለኝ?

ዘውዱ - ከካዛንቺስ

● የአባይ ወንዝ ሽያጭ አንደኛ ዓመት ክብረ በዓልን ለማሰብ ነው እንድልም ከሆነ "አፌን በሊዝ ብያለሁ"።

* * *

* ምነው ይኼን ሰሞን የብረት ድስት ማጠቢያ ሽቦ ዋጋው ናረ?

ታደሰ - ከመርካቶ

● የኢዮቢልዩ ቤተመንግስት አጥር ግንብ በሽቦ ብሩሽ መፈተግ ስለጀመረ ይሆናላ!

* * *

* ድላችን ሐውልት መታጠሩን ምን ትለዋለህ?

እያልነህ- ከጌጃ

● እርሳቸውን ቢያጡ ምስላቸውን ማገታቸው ይሆናላ!

* * *

* የቀድሞው መሪ "የእኛ ህዝብ ወርቅ ሲያነጥፉለት ፋንድያ ነው ይላል!" ያሉት አሁን አሁን ሳስብው እውነት ነው ጃል።

ተክሌ - ከኡራኤል

● የአሁኖቹ ደግሞ "የእኛ ህዝብ ማር እየበላ ዳቦ የሚጠይቅ ነው" ሳይሉን ይቀራሉ?

* * *

* ለመሆኑ እናንተ ጋዜጠኞች ሚስት አላችሁ?

አበሬሽ- ከገብርኤል

● የዘብጥያው ነገር አላስተቃቀፈንም እንጂ ለላህን ምልልሱማ ኮንትራት የፈረሙት ምስኪኖች መቸ ይጠፋሉ ብለው ነው።

* * *

* የካቲት 12 ሆስፒታል ውስጥ በመብራት ኃይል እጥረት የተነሳ በሻማ ቀዶ ጥገና መደረጉን ምን ትለዋለህ?

ጠለላ- ከመካኒሳ

● ከአምስት ዓመቱ የኢህዴግ መርሐ ግብር አንዱ ይሄ ይሆን እንዴ?

* * *

* የቤተ መንግስት እንግዳ መቀበያ እንዴት ያምራል እባክህ?

ታምሩ - ከቦሌ

● "እታ በእታ" ሆኖ እንዴት አያምር ብለው ነው ጌታው።

* ኤርትራ በቃ የአውሮፕላን ጠላፊዎች መናኸሪያ ሆና ቀረች አይደል?
አካሉ - ከእስጢፋኖስ
● ምን የጠላፊዎች ብቻ የገንጣዮችም ጭምር እንጂ!
* * *

* እናንተ ውሽታሞች "ኑሮ ተወደደ!" ስትሉ ሽክም ቲማቲም ታቅፈን ወደ ቤታችን መግባት ጀመርን አይደል?
አለሚቱ-ከወሎ ሰፈር
● የቲማቲምን ጣዕም ከእኔና ከእርስዎ ይልቅ መሪዎቻችን ያውቁታል።
* * *

* አንዳንድ ሰዎች በመላዕክት ተራዳኢነትና በፀበል ከኤድስ የተፈወሱትን ወጣት ዜና አጠራጣሪ ነው ይላሉ።
ዮሐንስ - ከፒያሳ
● እንዲች ዓይነቷ አሉባልታ የፈለቀችው መላዕክትን በስራችን ገቡ እያሉ ፀጉራቸውን ከሚነጩት ከነዶ/ር ይሆን?
* * *

* 'የከተማ አውቶቢስ ተጨመረ' እየተባለ ዛሬም ህዝቡ በሰልፍ ይተረማመሳል። ይህን ምን ትለዋለህ?
አዲሱ - ከኮተቤ
● 'የከተማው አንበሳ እየበላ ከሳ' ሲባል የት ነበሩ?
* * *

* መንግስታችን ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ ሬሳ በማውጣቱ ላይ ማተኮሩ ለምን ይመስላችኋል?
ተፈራ - ከ6 ኪሎ
● ፕሬዚዳንታችን የታሪክ ዶክተር ስለሆኑ የአርኪዎሎጂ ጥናት እያደረጉ ነው እንድልዎ ነው?
* * *

* አቤት ይኼ አዲሱ የማስታወቂያ ሚ/ር ፎቶ ማማሩን አይታችሁልኛል?
መስፍን - ከአራዳ
● ታዲያ ምን ያድርጋል? ተዋንያኑና ፎቶ በነጠላ ላይ ከረባት የማሰር ያህል ናቸው።
* * *

* የግብፅን ወደ ሱዳን መንሸራተት ሰማህ?
ንጉሴ - ከካዛንቺስ
● የአራት ኪሎ ሰዎቻችን ኦክሲጅናቸውን አጥልቀው እያራገቡ ጨረቃ ላይ ቀሩ በለኛ!
* * *

* እነዚህ የአቡነ-ጴጥሮስ ጋዜጠኞች የቀድሞ ባለስልጣናትን (እንተ) የሚሉት አይገርምህም?
እመቤት- ከላምበረት
● የበሉበትን ወጪት ሰብረው የዘመኑን ከበሮ ቢደልቁ ምን ይደንቃል?
* * *

* የኢትዮጵያ አየር አብራሪዎችን ማስመረቅ አበዛሳ?
መስፍን - ከደብረዘይት
● እኔ የምፈራው የቀሩት ሚጎችም ተከስክሰው እንዳያልቁ ነው
* * *

* ሰሞኑን ስብሰባ ላይ ቡትሮስ ጋሊ ያልተገኙት ለምንድነው?
አለሙ - ከመድኃኒያለም
● የሲራጅና የአውሎ ነፋስ መምጫው አይታወቅም ብለው ሰግተው ይሆን?
* * *

* ፋና፣ እፎይታ፣ ሜጋ፣ ... የሚባሉት ስሞች ለምንድነው የሚደብሯችሁ?
ኤልያስ -
● ከኋላቸው ካላሽ ስላለ እንድልዎ ከሆነ የፈለጉት ቢቀርብዎትስ?
* * *

* የሜርኩሪ ዋጋ ስንት እንደገባ ብትነግረኝ ውለታህን እከፍላለሁ።
ሜሪ - ከፒያሳ
● ከወደ መከላከያ አካባቢ አጠያይቀን ሰሞኑን ልንነግርሽ እንሞክራለን።
* * *

* አንድ ጋዜጣ ላይ የወጣው የፓትሪያርካችን ፎቶ ቁርጥ ፊደል ካስትሮን ነው የመሰለኝ።
ዘውዱ - ከቦሌ
● ጥቂት ቆይተው ደግሞ 'በቦሊቭያ ለካስትሮ የበረሃ ጓደኛ ነበሩ' እንዳይሉና ኃጢአት እንዳይገቡ ፈራሁሎት።
* * *

---

## ከዚሁ ከአሜሪካ

* ምነው የተቃዋሚ ኃይሎች ድምጻቸው ጠፋ?
ዘውዱ - ከዲሲ
● ኸረ አሉ። ደፈጣ ይዘው ይሆን አልታይ ያሉት?
* * *

---

# ሀናና ብንያም ሱቅ
# H & B SHOP

ጤፍ ዱቄት
በሶ
እልበት
ቡና
በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅመም በያይነቱ

በተጨማሪ
የቪዲዮ ካሴቶች
የቴፕ ካሴቶች
የተለያዩ መጽሔቶችና
መጽሐፍት

የተለያዩ የአገር ባህል
ልብሶችም እንሸጣለን።

**ወለላ ወርቁ**
**WOLELA WORKU**

## የምግብ ክፍላችን
## ጥብስ፣
## ክትፎና
## ጐረድ ጐረድ
## ዘወትር ያቀርባል።
## ጎብኙን

ቆንጆ ጤፍ እንጀራም እንሸጣለን
በተጨማሪ ለሠርግ፣ ለቀለበት፣
ለክርስትናና ለመሳሰሉት ዝግጅቶች
በትዕዛዝ እንጀራ እናዘጋጃለን።

LEMO SERVICE
ለሠርግና ለልዩ ዝግጅት
የሌመዚን አገልግሎትም
እንሰጣለን።
1-800-679-1816
Pager- 738-7783
(770)481-2306

431 North Indian Creek Rd Suite E
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)296-2766

ልብወለድ

# ከሥራ ስመለስ

## ከዓለማየሁ

ከስራዬ የወጣሁት ትንሽ ዘግየት ብዬ ይመስለኛል ወደ አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ። ከምሰራበት ከሰሜን ማዘጋጃ ቤት አካባቢ ቁልቁል ወደ ጊዮርጊስ እየነዳሁ ሳለ ሃሣቤ ምን ላይ እንደነበረ ትዝ አይለኝም። ጊዮርጊስ አውቶቢስ ፌርማታው ጋ ልደርስ ስል ከሩቁ አንድ ነገር ላይ ዓይኔ አረፈ። አውቶቡስ የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች ስላልነበሩም ይሁን ሌላ እሷ ደመቅ ብላ ታየችኝ። ቆንጆ፣ የደስ ደስ ያላት፣ ቦርሳዋን በትከሻዋ ያንጠለጠለች ዕድሜዋ በግምት ወደ 25ቱ የሚደርስ ወጣት ናት። እሷ ወዳለችበት መኪናዬን ጠጋ አድርጌ ክላክስ አደረግሁ። ጎንበስ ብላ ስታየኝ ፈገግታ ሰጠሁዋት። እሷም ፈገግ አለች። አለፍ ብዬ ከወደ ፌርማታው ማብቂያ ጋ መኪናዬን አቆምኩና ጠበቅሁዋት። መጣች። መኪናዬ ውስጥ እንዳለሁ ተንጠራርቼ የፊቱን በር ከፈትኩላት። ገባች። ደስ የሚል ሽቶ ተቀብታለች። ፈገግ አለች።

"ጤና ይስጥልኝ ታሪኩ እባላለሁ" አልኳትና እጄን ዘረጋሁ ልጨብጣት።

ጨበጠችኝ። "ታዲያስ!" አለችኝ። ከዚያም የምኒልክን ሐውልት በስተግራ ትቼ ቁልቁል ወደ ፒያሳ ወረድኩ።

"ጊዮርጊስ አካባቢ ነው ሥራሽ?" አልኳት ወሬ ለመጀመር ምክንያት ስፈልግ ነበር።

"አዎን ማዘጋጃ ቤት ነው የምሰራው።" አለችኝ

"ስምሽን እኮ አልነገርሽኝም" አልኳት

"እምሳለ እባላለሁ" አለች

"ታዲያ የማዘጋጃ ቤት ሥራ እንዴት ነው? አልኳት።

"ምን የመንግሥት ሥራ ታውቀዋለህ ዕድገት የለው፣ እንዲያው ውሐ ቅዳ ውሐ መልስ ነው" አለችኝ። ስለእኔ ሥራ ለምን እንዳልጠየቀችኝ ገረመኝ።

"ቡና ቢጤ ብንጠጣ ምን ይመስልሻል? . ይቅርታ የት እንደማደርስሽ እንኳ አልጠየቅሁሽ፣ የእኔ ነገር!" አልኳት

"ቡና ለመጠጣት ጊዜ እንኳ ይኖረኛል ብለህ ነው። ለማንኛውም አልቆይም። ሰፈሬ ወደ ድሮ አውሮፕላን ማረፊያ ነው።" አለችኝ

ስትጠብቅ የነበረው 3 ቁጥር አውቶቡስ እንደሆነ ገባኝ።

"ፍላሚንጎ ወይስ ፒኮክ?" አልኳት። ከመኪና ሳንወጣ ብዙ ማውራት እንችላለን ብዬ በማሰብ።

"ፒኮክ ትንሽ ይርቃል" አለች።

ቁልቁል በቸርቺል ጎዳና ጉዞዬን ቀጠልኩ። ወደ ፍላሚንጎ።

"የት ነው የምትሰራው?" አለችኝ

"ውሃ ክፍል መሃንዲስ ነኝ" አልኳት

"ያው የእኛ ግርፍ ነሃ! ስራህን ትወደዋለህ?" አለች

ምን ዓይነት ጥያቄ ነው አልኩ በሆዴ።

"መውደድ መለኪያው ምን ይሆን?" አልኳት። ጨዋታውን ለማራዘም ፈልጌ ነው። ፈገግታዬን አከልኩበት።

"መውደድ ምን መለኪያ አለው። መውደድ መውደድ ነው። አይደል እንዴ?" አለች። መለስ ብዬ አየሁዋት። ውበቷ የበለጠ ጎላ ብሎ ታየኝ። ጠይም አሣ መሳይ ናት። በስስ ከንፈሮቿ የተሸፈኑትን ጥርሶቿን ፈገግ ለማለት ብቅ ስታደርጋቸው ልብ ትነሳለች። እንዳው ድንግጥ የሚያደርግ አንድ ነገር አላት። ሰውነቷን በደምብ ይዛዋለች። ለአፍታ ውበቷ በውስጤ የፈጠረውን ስሜት አስታምም ገባሁ።

"ሥራን ለደሞዝ ሲሉ መውደድ አለ። ለገንዘቡ። እንደዚያ ከሆነ አልወደውም የስራውን ባህርይ ካልሽ ግን ፈልጌ ትምህርት የቀሰምኩበት ሙያ ስለሆነ እወደዋለሁ።" አልኳት። ስለሙያዬና ስለትምህርቴ ሳወራ ደስ ይለኛል። በተለይ ለእንደዚች ዓይነቷ የውበት ቁንጮ።

"ምነው ደህና ደሞዝ አይከፍሉም እንዴ?" አለችና ሳቅ አለች።

የምን ሂሳብ መተሳሰብ ነው አልኩ በሆዴ። "ለሙያዬና ለሥራዬ የሚያንስ ነው እንጂ ደሞዜስ ደህና ነው።" አልኳት ጨዋታው ብዙ መቀጠሉ ደስ አላለኝም። ስለደሞዝና ሥራ ማውራቱ በመጀመሪያ ቀን የፍቅር ጨዋታ ላይ ቦታ የለውም ብዬ የማምን ነኝ። መስቀል አደባባይን አልፈን ወደ ቦሌ መንገድ አቀናን። ፍላሚንጎም ደረስን። ከወደጥጉ ባዶ ቦታ አግኝቼ አቆምኩ። አሳላፊው ታዘዘን።

"አንድ ቀዝቃዛ ጊዮርጊስ" አልኩት

"ለእኔ አንድ ጭማቂ" አለች

"ምነው ቢራ አትሞክሪም" አልኳት

"ሴትን በቢራ አስክሮ advantage የመምታት ዓመል አለህ እንዴ?" አለችኝ።

"ኧረ እኔ እቴ" አልኳት

"ታዲያ ቢራ ጠጪ ያልከኝ ለምንድነው?" አለችኝ

ጥያቄዋ ግራ ገባኝ። "አአይ! አለ አይደል እንዳው ምናልባት ቢራ ከወንዶች ጋር መጠጣት ከማይፈልጉ ሴቶች አንዷ ትሆኚ እንደሆነ ለማደፋፈር ብዬ ነው።" አልኳት።

ፊቷን ወደ እኔ ዞር አድርጋ ትክ ብላ አየችኝ።

"ቢራ ከጠጣሁ አትችለኝም" አለች።

"ምንድነው የማልችልሽ" አልኳት።

"ሁሉንም ነገር!" አለችና ፈገግ አለች። ከዚያም በመሽኮርመም ዓይነት ሳቀችና ቀና ብላ በቆረጣ አየችኝ።
መልዕክቷ ገብቶኛል። ጥርጣሬ ገባኝ። ሴተኛ አዳሪ ትሆን? . . . ብትሆንስ . . . hit and run ነው ምን አስፈራኝ . . . ደፈር አልኩ።

"የሚያቅተኝ ነገር ያለ አይመስለኝም" አልኳት

"እአይ! አንተ . . . በል ቢራ ቀይር በለው" አለችና እንደማሽካካት አለች።

ሰውነቴን ይነዝረኝ ጀመር። ከላከስ አድርጌ ጠራሁትና አሳላፊው ሲመጣ ሁለቱንም ቢራ እንዲያደርገው ነገርኩትና
መለስ አልኩ ወደ እሷ።

"ኋላ አልነገረችኝም እንዳትል? . . ."

"ግዴለሽም፤ በእኔ ይሁንብሽ" አልኩና ጎበዝ መሆኔን ለማሳወቅ በአንድ እጄ የመኪናውን መሪ ይዤ ከወደ ደረቴ ተንጠራራሁ። ሌላኛውን እጄን ወደእሷ ትከሻ ወስጄ አንገቷን ያዝ አደረግሁ። ነካ ሳደርጋት ዘላ ተጠመጠመችብኝ። ያልጠበቅሁት ነገር ነበር። አንገቴን፣ አገጩን በከንፈሮቿ ዳሰስ ዳሰስ አድርጋ ከንፈሮቼን እንደተራበ ጅብ ጎረሰቻቸው። ሁኔታዋ ቢያስደነግጠኝም ወንድነቴን ለማስመስከር ቃል የገባሁ በመሆኔ እንደፈለገችው ሆንኩላት። የመኪናው ማርሽ፣ የእጅ ፍሬንና መሪው መሐል ተደንቅረው ባያስቸግሯት ኖሮ ዘላ በወጣችብኝ ነበር። የፎከረችበትን ቢራ ደግሞ ስትጠጣ ምን ዓይነት ትሆን? ብዬ ማሰቤ አልቀረም። አሳሳሟ፣ አተነፋፈሷ በኃይል ነበር። በክፉ ልተረጉምባት መንፈሴ አልገፋፋኝም። ፍቅር ሰጥታ የምትቀበል መሆኗን፣ ስሜትን የማትደብቅ "ተግደርዳሪ ጦም አዳሪ" እንዳልሆነች አድርጌ በደግነት እንዳያት ነው መንፈሴ የገፋፋኝ ። በእጇ በትንፋሿና በከንፈሮቿ የምትሰራቸው ነገሮች ሰውነቴን እያዛሉት፣ እያሟሙት ሄዱ።

አሳላፊው ቢራችንን አምጥቶ የመኪናየን መስታወት ባያንኳኳ ኖሮ ቀጥሎ የሚሆነውን መገመት አያዳግትም። ቢራውን እንደወሰድን ቶሎ ቶሎ ጠጣን። በሁለት ትንፋሽ ጭልጥ አድርጋ ጠጥታ ስትጨርስ ደነገጥኩ። እኔም ከማን አንሼ ጭልጥ አደረግሁና የመኪናዬን ከላከስ ነፋሁ። አሳላፊው እንደመጣ ሂሳቡን ከጉርሻ ጋር ሰጠሁት። ጠርሙሶቹን መለስኩለትና የመኪናዬን ሞተር አስነሳሁ። ፍላጎቷ እንዲሁም ግልፅነቷ ስለገባኝ "የት ይሻለናል?" አልኳት።

"የምታውቀው ጥሩ ቦታ ካለ" አለችኝ።
ሾላ ገጠር መናፈሻ ሩቅ መስሎ ታየኝ። ወደ ነፋስ ስልክ ዳግ ሆቴል በረርኩ። እንደደረስኩ የሆቴል ክፍል ጠየቅሁና ከፍዬ ተያይዘን ገባን። ገብተን የበሩን ቁልፍ እንደዘጋሁ ዘላ ተጠመጠመችብኝ። ከዚያ የሆነውን ለመናገር ቃላት ያጥረኛል። ልብሳችንን አወላልቀን ተያይዘን ከአልጋው ላይ ዘፍ አልን።በሕይወቴ አይቼው የማላውቀው ደስታ ሰውነቴን ወረረው። እንደመኸገር ከሰውነቴ ተጣብቃ ያሳየችኝን የፍቅር ጨዋታ፣ የሰውነቷ ልስላሴና ጣፋጭነት፣ የትንፋሿ ቃና፣ . . . ሰውነቴን አሟሟው። ሳናቋርጥ ለአንድ ሰዓት ባደረግነው ጨዋታ የድካም ስሜት አልተሰማትም። እኔ ደክሞኝ አልጋ ላይ ተዘርሬ ሳለሁ ተነስታ ቁጭ አለች።

"ደከመህ እንዴ?" አለችኝ። ለዛ ባለው ወሲባዊ አባባል።

"እ! . . . ትንሽ!" አልኳትና ፈገግ ብዬ አየሁዋት።

"አትችለኝም አላልኩህም?" አለችና ፈገግ ብላ እተኛሁበት እቅፍ አድርጋ ሳመችኝ።

"በል ተነስ ቤቴ አድርሰኝ" አለችኝ።

ተነስቼ እየለባበስኩ ሳለሁ እንዴት ነው ደስ አልኩህ?" አለችኝ።

"በጣም እንጂ" ብዬ እቅፍ አድርጌ ሳምኳት።

"ሌላ ጊዜ እንገናኛለና?" አለችኝ።

"መጠርጠሩስ፤ እንዳትጠፊ ግን . . . " አልኳት።

"እኔም ደስ ብለሽኛል። ስልኬን እሰጥሃለሁ። ስራ ቦታ አትደውልልኝ። የቤቴን ስልክ እሰጥሃለሁ" አለችኝ።
የቤቷን ስልክ ቁጥር ሰጠችኝ። እቤቷ ድሮ አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ አደረስኳት።

"እቤት ግባ እንዳልልህ እናቴ አለች። ሌላ ጊዜ አስተዋውቄህ ትገባለህ። በል ቻው።" አለችኝ።
መኪናውን ስትከፍት ከባድ ብርድ ተሰማን። የለበሰችው ስስ ልብስ ነበረና ቆይ ይበርድሻል ጃኬት አለኝ መኪና ውስጥ እሱን ልበሺ ብዬ ከመኪናዬ ወጥቼ ከኋላው ኮፈን አውጥቼ ሰጠሁዋት። የቤቴን መንገድ ያዘች። ቤቷን ከፍታ ስትገባ መኪናዬን አስነስቼ ጠረንዋንና ትዝታዋን ይዤ ወደ ቤቴ ነጎድኩ። ማንም ሴት ከዚህ በፊት ሰጥታኝ የማታውቀውን ደስታ ነው እምሳለ የሰጠችኝ። በሚቀጥለው ቀን መደወል አልፈለግሁም። በጣም የጓጓሁላት መሆኔን ያሳውቃትና እንድትኮራብኝ ያደርጋታል ብዬ አለፍኩት። በሶስተኛው ቀን ምናልባት ከስራ ስትወጣ አገኛት ይሆናል ብዬ ጊዮርጊስ አውቶቡስ ፌርማታ አካባቢ ብቃኛት አላየሁዋትም። ቀድማ እቤት ሄዳ ይሆናል በማለት እየከፈንኩ እቤቴ ደረስኩና ስልኩን አነሳሁ። የሰጠቺኝን ማስታወሻ ከኪሴ አወጣሁና ደወልኩ። ከሁለት ጥሪ በኋላ ስልኩ ተነሳ።

"አሎ!" ዝግ ያለ ለስላሳ ድምፅ፤ የእሷ ግን አይደለም።

"አሎ! ጤና ይስጥልኝ። እባክዎን እምሳለን ያቀርቡልኛል?" አልኩኝ። እናቷ መሆን አለባቸው ብዬ ጠረጠርኩ።

"እቤት!" አሉ እንደገና

"እምሳለን ነበር እባክዎን" አልኳቸው።

"እምሳለን?" አሉ። የመገረምና የማላዘን ዓይነት ነበር እጠያየቃቸው

"እዎ እምሳለን!" አልኩኝ ለስለስ ብዬ። "ትቀልድብኛለህ ወይስ ምንድነው?" አሉ ሲቃ በተናነቀው ድምፅ

"እንዴት መቀለድ?" አልኳቸው ትህትና ባለው ቃና።

"ማን ልበል፣ እንዲያው ለነገሩ?" አሉኝ። ትንሽ ፈራ አልኩ። ምናልባት እናቷን ደፍሬ ልጅዎን ያቅርቡልኝ ማለቴ እንደድፍረት ተቆጥሮብኝ ይሆን ብዬም አሰብኩ።

"ታሪኩ እባላለሁ"

"ታሪኩ?" አሉ፤ ማንነቴን የማረጋገጥ ጥያቄ ነበረ

"እዎ ታሪኩ እባላለሁ። ከትላንት በስቲያ ተገናኝተን ቤቴ ደውል ብላ ነበር የስልኩን ቁጥር የሰጠችኝ።

"ከትላንት በስቲያ?" አሉ በመገረም

"እዎ ከትላንት በስቲያ" አልኳቸው

"ልጄ ምናለ ባትቀልድብኝ። ከትላንት በስቲያ የት አግኝተሃት ነው የሰጠችህ?" አሉና ጠየቁኝ።

"ማዘጋጃ ቤት፣ መሥሪያ ቤቷ" አልኳቸው።

ለጥቂት ሰኮንዶች ዝም አሉ። በኋላ ዝግ ያለ የለቅሶ ዓይነት ድምፅ የሰማሁ መሰለኝ።

"እሎ፣ አሉ። ምነው ተሳስቼ ይሆን የደወልኩት፤ የእምሳለ ቤት አይደለም እንዴ?" አልኳቸው ግራ ተጋብቼ።

"ምነው ልጄ ስንት የሚቀለድበት ነገር እያለ ምናለ በዚህ ባትቀልድ። ምን አደረግሁህ?" አሉ በለቅሶ በተናነቀው ድምፅ።

በጣም ግራ ገባኝ። "አልገባኝም እናቴ። እኔ አልቀለድኩም። ምኑ ነው ቀልድ የሆነብዎት?" አልኳቸው።

"እእይ! ደግ አይደለም። ቀልድ ነው እንጅ! እንዴት በሙት ነፍስ ይቀለዳል? . . . አይ ስምንተኛው ሺህ!" አሉ።

"ሙት ነፍስ?" ሴትዮዋ ጤነኛ አይደሉም እንዴ አልኩኝ በሆዴ። "የምን ሙት ነፍስ?" አልኳቸው

"ልጄ በሞተች በ3ኛው ዓመቷ ቤቷ ደውሎ 'ስልኳን ከትላንት በስቲያ ሰጠችኝ' ማለት የሚገባ ነው። ምናለ የዛሬ ልጆች ደጋጉን ነገር ብታደርጉ።"

ግራ ገባኝ። "በሞተች በ3ኛው ዓመት፣ . . . እኔ እኮ የምሎት እምሳለን ነው!" አልኳቸው።

"እኔስ ማንን አልኩ?"

ዝም አልኩ። ምናልባት የሞተ ጓደኛዋን ወይም ሰው ስምና ስልክ ሰጥታኝ ተጫውታብኝ ይሆን ብዬ ጠረጠርኩ።

"ቤታችሁ ድሮ አውሮፕላን ማረፊያ አጠገብ አይደል?"

"እዎ እንዴት አወቅህ?"

"ከትላንት በስቲያ ማምሻው ላይ እኮ እዚያ አድርሻታለሁ።"

"ልጄ እባክህ ተወኝ። የሙት እናት እኮ ነኝ። ምናለ ትንሽ ብታዝንልኝ" አሉ።

"እማማ ይሙቱ አድርሻታለሁ። ጠይም አፍንጫዋ ሰልከክ ያለ ልጅ ናት፤ አይደለችም?"

"ልጄ፤ አፈር በላት እንጂ እሷስ ሰልከክ ያለች ነበረች፤ ዋ . . እኔ" አሉና ለቅሶአቸውን ለቀቁትና ስልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጉት። ግራ ተጋባሁ። እንዴት ሊሆን ይችላል? እእይ! ሸውዳኝ ነው ብዬ በማሰብ እልህ ተናነቀኝ። በተለይ በሞተ ሰው እናት የቀለድሁ ወይም ያሾፍኩ መስዬ መገመቴ ደግሞ የበለጠ አናደደኝ። ስልኩን እስቀምጬ የመኪና ቁልፌን አወጣሁና ከቤት ወጣሁ። በቀጥታ ወደ ድሮ አይሮፕላን ማረፊያ ሰፈር በረርኩ። እልህ እየተናነቀኝ። ከትላንት በስቲያ ካወረድኳት ቤት ጋ ደርሼ ሁሉን ነገር አየሁ። የወረደችበትን፣ የተሳሳምንበትን፣ ከፍታ የገባችውን በር ጭምር። ከዚያም ከመኪና ወጣሁና በቀጥታ ስትገባ ካየሁበት ቤት ግቢ ሄድኩና በሩን አንኳኳሁ። ደግሜ አንኳኳሁ።

"አቤት!" የሚል እንባ የተናነቀው ዝግ ያለ የአሮጊት ድምፅ ሰማሁ።

"እንግዳ ነኝ" አልኩ።

በሩ ተከፈተ። ዓይናቸው በእንባ የተሞላ ዕድሜያቸው ገፋ ያለ መልካቸውና አጠያየማቸው እምሳለን የመሰሉ ሴትዮ ናቸው።

"አቤት" አሉ በድጋሚ አይናቸውን እየጠራረጉ።

"አሁን በስልክ ያነጋገርኮት ታሪኩ ነኝ" አልኳቸው።

"ምነው ልጄ ምን አደረግሁህ? ሲያዩህ የተማርክ ትልቅ ሰው ትመስላለህ" አሉኝ።

"እማማ በእውነት ቀልዴን አይደለም። ይህ የእርስዎ አባባል አሳስቦኝ እኮ ነው የመጣሁት" አልኳቸው።

"ልጄ እየነገርኩህ። ልጄ እምሳለ እኮ ከሞተች ይኸው ያለፈው ወር ሶስት ዓመት አለፋት።"

????? በሩን ከፍተውልኝ ወደ ውስጥ ገቡ።

ሳሎን እንደገባሁ ያየሁት ነገር የበለጠ አስደነገጠኝ። ትልቅ የእምሳለ ፎቶ በቁቢት ጨርቅ ተሸፍኖ ግድግዳው ላይ ተሰቅሏል። ፎቶ ፎቶዋን እያየሁ ወደዚያው ጠጋ አልኩ። ትክ ብዬ ሳየው እሷው ናት። ምንም አያሳስትም።

ድንጋጤ አይባል ሐዘን ሰውነቴን አንድ ነገር ውርር አደረገው። ራሴን እዙሮኝ ልወድቅ ነበር። ሁኔታዬን አይተው እናቷ እጄን ይዘው ወደ መቀመጫ መሩኝ። እየተንደረደርኩ ሄጄ ቁጭ አልኩ።

"ልጄ ታዲያ እሷ ናት?" አሉኝ።

"እ! . . . " ብዬ ከተቀመጥኩበት አሻግሬ ፎቶዋን ማየት ቀጠልኩ።

"እና ከሞተች ሶስት ዓመቷ" አሉና ቁጭ አሉ።

"እማማ . . . አንድ ነገር ልጠይቅዎት" አልኳቸው

"ምን ነበር ልጄ?" አሉኝ።

"ልጅዎ ምን ሆና ነው የሞተችው?" አልኳቸው

"ድንገት ከሥራ ገብታ ማታ ራሴን አለች። ከዚያ መኝታ ቤቷ ገባች። ልጄ ምን ሆንሽ ብዬ ከአንድ ግማሽ ሰዓት በኋላ ወደ መኝታ ክፍሏ ስገባ በድኗን አገኘሁ፤ . . . እህህ! . . ." አሉና በመሀረባቸው የመጣባቸውን እንባ ጠራረጉ።

"የት ነበር የምትሰራው?" አልኳቸው።

"ማዘጋጃ ቤት ነዋ"
"የት ነው የተቀበረችው?" አልኳቸው
"ዮሴፍ" አሉኝ
"እማማ መቃብሯን ሊያሳዩኝ ይችላሉ?" አልኳቸው
"አአይ ልጄ፣ . . . ምን ከፍቶኝ? መቼ?" አሉ።
"አሁኑኑ" አልኳቸው
"አልመሸም?" አሉ
"መኪና ይዣለሁ። እኔ ይህን ነገር ሳላረጋግጥ አላድርም።" አልኳቸው
በድንጋጤ፣ በሀዘን ሰውነቴ ዝልፍልፍ እንዳለ ተያይዘን ወደ ነፋስ ስልክ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን አመራን።

መኪናችንን አቁመን በእግራችን ወደ ውስጥ ገባን። ጊዜው ትንሽ ደንገዝገዝ ብሏል። ትንሽ እንደሄድን ያውልህ ልጄ ብለው ራቅ ካለ ቦታ ሆነው መቃብሯን አሳዩኝና እሳቸው መሬት ላይ ቁጭ ብለው ለቅሶአቸውን ቀጠሉ።

እኔም ወደ መቃብሯ ቀረብ አልኩ። ፎቶዋን አየሁ። ፈገግታዋ እንዳለ ነው። ከፎቶግራፏ ስር
"እምሳሉ ጣሰው"
1941-1965 ይላል።

ቀና ብዬ ከመቃብሩ ላይ ያየሁትን ነገር ብነግራችሁ አታምኑም። ተጣጥፎ በስርዓት የተቀመጠው ከትላንት በስቲያ ብርድ ይመታሻል ብዬ የሰጠሁዋት ጃኬቴ ነበር። እሱን ሳይ አጥወለወለኝና ኡኡ! እያልኩ እየጮኽኩ ከመቃብሩ ላይ ስወድቅ . . . ከእንቅልፌ ብንን አልኩ።

ሰውነቴ ላብ በላብ ሆኗል። የውስጥ ልብሴም ተበላሽቷል። እየተንገዳገድኩ ተነስቼ ወደ ሽንት ቤት ሄድኩ።


## የሚከተሉትን መጽሐፍትና ፎቶግራፎች ለማግዛት እዘዙን

### "ባህልና ሥልጣኔ"

- ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነት ልጆቻችሁ ማወቅ ያለባቸውን ያብራራል።
- ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ፍሬ ነገሩን ያስረዳል።
- የሥልጣኔ ፍቺውን ያወጋል።
- ሥራ ጥያቄ ሲኬድ ወይም ለቃለመጠይቅ ስንቀርብ ማለት ያለብንና የሌለብንን ያስረዳል።
- ኢትዮጵያውያን ቀጠሮ የማክበርን ነገር ያሳስባል።
- ያቀማመጣችንና የእጅ አጨባበጣችን ሁኔታ ግምት ውስጥ የሚከት መሆኑን ያትታል።
- ሴት ወዳጅህን ስታወጣ በቅድሚያ ማወቅ ያለብህን ያሳስባል።
- ለአዲስ መጪዎች ምክር ይሰጣል።

ዋጋው $15.00 ብቻ

በተጨማሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀ ኃ ሥ ከልዩ ልዩ አገር መሪዎች ጋር ሆነው የተነሱትን ፎቶ በአማረ ሁኔታ አዘጋጅተናል።
ዋጋው $32.00
ንጉሠ ነገሥቱ ያደረጉዋቸውን ንግግሮች ከነፎቶግራፎቹ ዋጋው $42.00

የመላኪያውን ወጪ እኛ እንችላለን።

በሚቀጥለው አድራሻ ጻፉልን፣ ደውሉልን።

Ethiopian Cultural T.V.
P.O.Box 1414, Denver, CO 80201
Phone (303)377-7556
FAX: (303)377-8220

# የአድዋ ድል 100ኛ ዓመት በከፍተኛ ድምቀት ተከበረ !!

የኢትዮጵያ ሕዝብ በገናናው መሪዎቹ በአፄ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ እየተመራ በአንድነት በእብሪተኛው የጣልያን ጦር ላይ ያደረገው ድል መቶኛ ዓመት መታሰቢያ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ በታላቅ ድምቀት መከበሩ ታውቋል። የጥቁር ሕዝቦች በኮሎኒያሊስቶች ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አሸናፊነት በመጀመሪያ ያበሰረውና በመላው አፍሪካና በሌሎችም ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ በምሳሌነትና በኩራት የሚታየው ይኸው ታላቅ በዓል የተከበረባቸው ቦታዎች ኢትዮጵያውያን በብዛት በሚገኙባቸው የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ከተሞች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በዋሺንግተን ዲሲ፣ በሎስአንጀለስ በፊላዴልፊያ በአትላንታና በሌሎችም ከተሞች ታላላቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ተደርገው በበዓሉ ላይ ንግግሮች፣ ግጥሞችና የተለያዩ ፕሮግራሞች ቀርበዋል። በሚቺጋን እስቴት (ኢስት ላንሲንግ) ሁለት ቀን የፈጀ ታላቅ በዓልና ትምህርታዊ ጉባኤ ተካሂዷል። ዝርዝር ሁኔታው ባይደርሰንም በብዙ ከተሞች በዓሎች መዘጋጀታቸውንም ለማወቅ ችለናል።

የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን በተገኘበትና በተሳታፈበት አትላንታ ከተማ ቁጥሩ ወደ አምስት መቶ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን በበዓሉ ተገኝተዋል። በበጎ ፈቃድ በመነሳሳት የተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያን ያቋቋሙት የአድዋ በዓል ዝግጅት ኮሚቴ ከበዓሉ ቀን ቀደም ብሎ የአድዋ በዓል ጦርነት ታሪክና የበዓሉን ታላቅነት በተመለከተ በአትላንታ አካባቢ ለሚገኙ የዜና ወኪሎች ጋዜጣዊ መግለጫ የላከ ሲሆን በዋናው በዓል ዕለት ምሽት ወደ ኢትዮጵያ በሚተላለፈው የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ መግለጫ ሰጥቷል። በዓሉ የተካሄደው የካቲት 24 ቀን 1988 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ሲሆን በዚሁ በዓል ላይ የአድዋ ጦርነትን ታሪክ አነሳስ፣ አጨራረስና ውጤቱን በተመለከተ ሰፋና በሰል ያለ ትምህርት የሰጡት የታሪክና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ዶክተር ንጉሤ አየለ ናቸው። ዶክተር ንጉሤ ጠለቅ ያለ ምርምር ያደረጉበትን የአድዋ ጦርነት ገጽታ በበዓሉ ለተሰበሰበው ወደ አምስት መቶ ለሚጠጋ ሕዝብ ከማቅረባቸውም በላይ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ሰጥተዋል። ከዚህ በተረፈ አንድ ጥቁር አሜሪካዊ ምሁር የዩኒቨርስቲ መምህር የአድዋን ታላቅነት፣ ካበሰሩ በኋላ ኢትዮጵያ በዓለም የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ የነበራትንና ያላትን ሚና የአዳማጪን ስሜት ባስደሰተ ሁኔታ አቅርበዋል። አቶ ዐቢይ ና ወ/ ሣራ ታከለና አቶ ኃይሌ አገናፍር ስለጦርነቱ ታሪክ ዘገባ አቅርበዋል። አቶ ጌታቸው አድማሱም ልብ የሚነካ ግጥም አሰምተዋል። በዓሉ የተጀመረው ወጣት እሌኒ አስናቀ የአጼ ምኒልክን አዋጅ ካነበበች በኋላ ነበር። ሕዝባዊ ስብሰባውን በሥርዓትና በቅልጥፍና የመሩት የኮሚቴው ሊቀመንበር አቶ ፍቅሩ አየለ ናቸው። በዚሁ ዕለት በኮሚቴው የተዘጋጁ የአድዋን ታሪክ በተመለከተ የተሰባሰቡ ፎቶግራፎችና የኢትዮጵያ ባህላዊ ዕቃዎች ለኤግዚቢሽን ቀርበዋል።

## የአድዋ ድል 100ኛ ዓመት በአትላንታ ሲከበር



# አጭር የዓድዋ ጦርነት ታሪክ

ከመርዕድ ዓለማየሁ (አትላንታ ጆርጂያ)



የአድዋ ጦርነት የተካሄደው በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ነበር። የተካሄደበትም ቦታ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግሬ ክፍለ ሀገር በአድዋ ዓ.ም. ነበር። ለዚህም ጦርነት የአገራችን ኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ብልሁ አፄ ምንሊክና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ዝግጅቱን የጀመሩት በ1886 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ነበር።

ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረርና በቁጥጥሯ ስር ለማድረግ ሀሳብም ፕላንም እንዳላት ለአውሮፓም አገሮች ይሁን ለአፍሪካ ብሎም ለኢትዮጵያ ምስጢር አልነበረም። የሚያስገርመው ነገር ግን ዋናው የአድዋ ጦርነት መንስዔ የሆነው በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል በተደረገው የመተባበርና የመረዳዳት ውል ምክንያት መሆኑ ነው። ይህም ዝናን ያተረፈ ውል "የውጫሌ ውል" ተብሎ ይጠራል። የተፈረመውም በግንቦት ወር በ18 ዓመተ ምህረት ነበር። ይህ ውል በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ (የኢትዮጵያው) እና በጣሊያንኛ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ነበር። በሁለቱም ቋንቋዎች የውሉ ዓይነትና ፅንሰ ሀሳብ በአንድ ዓይነት እንዲቀነባበር ነበር የታሰበው። ነገር ግን ትንሽም እንኳ ሳይቆይ ይህ በትክክል አለመሰራቱንና ጥንቱንም ጣሊያን ኢትዮጵያን በስሯ ለማድረግ ታስቦ ስለነበረ በውሉ ውስጥ በአንቀፅ 17 (አስራ ሰባት) ላይ ከፍተኛ ውዝግብ ተነሳ። ይህ ከላይ የተጠቀሰው አንቀፅ ዋናው ፅንሰ ሀሳብ በጣሊያንኛው ኢትዮጵያን በሚመለከት የውጪ ጉዳይ ነገር ሁሉ በጣሊያን በኩል ብቻ እንጂ እንደማንኛውም ነፃ አገር የፈለገችውን ማድረግእንደማትችልየሚያረጋግጥሲሆንየአማርኛው ትርጓሜ ደግሞ ኢትዮጵያን ነፃ የሆነች፣ ራሷ ለራሷ የቆመችና የማንም ጥገኛ አገር አለመሆኗን የሚያሳይ ነበር። ይህንንም ውዝግብ በሰላም ለመፍታት አፄ ምኒሊክ በተደጋጋሚ ለተለያዩ የአውሮፓና የእስያ ሀገር መሪዎች ደብዳቤ ፅፈዋል። ጣሊያኖች በበኩላቸው ውሉ ከተፈረመ በኋላ ወደኋላ ተመልሰን የምናስተካክለው ነገር የለንም ብለው አሻፈረኝ አሉ።

በዚህ ጊዜ ነበር አፄ ምኒሊክ፣ እቴጌ ጣይቱ፣ ራሶች፣ ደጃዝማቾች፣ ፊታውራሪዎችና በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ ያለው በአንድ ላይ ለጦርነት መዘጋጀት የጀመረው። ይህ ጦርነት በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

1) የአምባላጌው ጦርነት
2) የመቀሌው ጦርነት
3) የአድዋው ጦርነት

## 1. የአምባላጌው ጦርነት

በነሐሴ ወር 188? አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ እስከ 100,000 (መቶ ሺህ) የሚጠጋ ጦር ሰብስበው ለመጀመሪያው ጦርነት ከመሀል አገር ወደ አምባላጌ ጉዞ ጀመሩ። ይህንንም ጦርነት ራስ መኮንን፣ ራስ ወሌና ራስ መንገሻ እንዲመሩ አፄ ምኒሊም ትዕዛዝ አስተላለፉ ጣሊያኖችም በበኩላቸው በማጆር ቶሶሊ መሪነት የኢትዮጵያን ጦር ለመደምሰስ አምባላጌ ላይ ይጠባበቁ ነበር።

ጦርነቱም በ ዓ.ም ተጀመረ። ጣሊያኖችም ሆኑ የአውሮፓ አገሮች እንዳሰቡት ሳይሆን ስድስት ሰዓት የሚወስድ ከፍተኛ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ ኢትዮጵያ የአምባላጌውን ጦርነት አሸነፈች። ማጆር ቶሶሊም ተገደለ። የጣሊያን ጦር ያለውንና የተረፈውን ሰብስቦ ወደ መቀሌ ሸሸ። የጣሊያንም መሸነፍ ዜናው በመላ ዓለም ተሰማ በሮማ መንገዶች ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች የሚወራው ይኸው ሆነ። የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር (ክሪስፒ) ከፍተኛ የፖለቲካ ውጥረት ውስጥ ወደቀ። በአንድ በኩል እንዴትና ለምን ይህ ሊሆን እንደቻለ? በሌላ በኩል ጦርነቱን የሚቃወሙና የአገራቸውን ኮሎኒያል ፖሊስ የሚጠሉ ተማሪዎች "ጦርነቱ ይቁም" "የጣሊያን ወታደሮች ከኢትዮጵያ ይውጡ" "ቪቫ ምኒልክ" እያሉ ጩኸታቸውን ያሰሙበት ጊዜ ነበር።

ጣሊያንም በጦርነቱም ሆነ በፖለቲካ ከፍተኛ ክስረት ደረሰባት። በኢትዮጵያ በኩል አፄ ምኒሊክ ጣሊያኖችን አሸንፈው አምባላጌን በማስለቀቃቸው ከፍተኛ የሞራል ተሀድሶ ተሰማቸው። ድሉንም ከእቴጌ ጣይቱ ጋርና ከሕዝባቸው ጋር በደስታ ተቀበሉት። ምንም እንኳ ኢትዮጵያ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ቢደርስባትም ለሁለተኛው ዙር ጦርነት ወደ መቀሌ ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

## 2. የመቀሌው ጦርነት

ጦርነት ያስከረቸው ጣሊያኖች ለሁለተኛው ጦርነት ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርጉ ነበር የከረሙት። ሸሽተው መቀሌ ከገቡ በኋላ ወደር የማይገኝለትና በቀላሉ ሊመታ የማይችል ምሽግ ሰርተው ይጠባበቁ ነበር። የጣሊያን ጦር መሪም ማጆር ጋሊያኖ ነበር። አፄ ምንሊክ ለአጠቃላይ ዝግጅት ራስ መኮንንን የበላይ ተቆጣጣሪ አደረጉ። በዚሁም መሰረት ራስ መኮንን ነገሩን በሰላም ለመጨረስ በተደጋጋሚ ለማጆር ጋሊያኖ ጽፈዋል። ከፃፉት መሀከል "አምባላጌ ውስጥ የክርስቲያን ደም በከንቱ ፈሷል። አሁንም እንዳይደገም ለምን በሰላም አንጨርሰውም" የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ "ለአፄ ምንሊክ ስም ስትል አገራችንን ልቀቅ አለበለዚያ ግን ጦርነት ለማካሄድ እንገደዳለን" ብለዋል።

ማጆር ጋሊያኖ በበኩሉ የመለሰው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያን እንደማይለቅ፣ የበላይ ትዕዛዝ እንዳለበትና እንዲያውም ይባስ ብሎ ስላለው የመሣሪያና የጦር ኃያልነት ነበር ያስመለከተው። እንደ እውነቱ ከሆነ የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ማጆር ጋሊያኖ ሰላምን ሳይሆን የሚፈልጉት አባላጌ ላይ የደረሰባቸውን ሀፍረት መቀሌ ላይ ለመበቀል ነበር። የሰላም ድርድሩ ፍሬ አልባ ስለሆነ በጥር ወር 1888 ዓ.ም በራስ መኮንን መሪነት የመቀሌውና ሁለተኛው ጦርነት በጠዋት ተጀመረ። የኢትዮጵያ ጀግና ወታደሮች የአገራቸውን ክብር ለማስጠበቅ ሞት ሳይፈሩ ጣሊያንን ምሽግ ሰብሮ ለመግባት ቀኑን ሙሉ ሲዋጉ ዋሉ። ምሽጉን ግን ፈልቅቆ ለመግባት በጣም አስቸጋሪና ፈፅሞ የማይቻል ነበር።

በኢትዮጵያም በኩል ብዙ ሰው አለቀ። ራስ መኮንን ቀላል ጉዳት ደረሰባቸው። በመጨረሻ ይህንን ችግር የተመለከቱት እቴጌ ጣይቱ ሁኔታውንና ቦታውን በደንብ ካጠኑ በኋላ ጦርነቱ እንዴት ቢካሄድ እንደሚሻል አስደናቂና ብልህ ሀሳብ አቀረቡ። ሀሳቡም የጣሊያንን ጦር የውሐ ማከማቻና መጠቀሚያን መዝጋት ነበር። ይህም ሀሳብ በዚያን ጊዜ አሉ የተባሉ አዋቂ የጦር አበጋዞችን አስደንቆና አስገርሞም ነበር። እቴጌ ጣይቱም ይህንን በሥራ ለማዋል የአፄ ምንሊክን ፈቃድ ካገኙ በኋላ የራሳቸውን ጠባቂ ወታደሮች ለዚህ ቀራጥ ሥራ አሰማሩ። ይህም የጦር ዘዴ ጣሊያኖችን በእምብርክክ አሲኪዶ የማጆር ጋሊያኖን ጦር ከካምፖቻቸው አንድ በአንድ እንዲመጡና እጅ እንዲሰጡ አደረጋቸው። ዕድሜና ጤና ለእቴጌ ጣይቱ እየተመኘ የኢትዮጵያ ተዋጊ የኢትዮጵያን ባንዲራ ጣሊያኖች መሽገው የነበሩበት ቦታ ላይ አውለበለበው። እቴጌ ጣይቱ ሰው ሰራሽ ድርቅ ጣሊያን ወታደሮች ላይ ፈጥረው ድልን ተቀዳጁ። በዚህን ጊዜ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ወታደሮች ጣሊያኖችን ማጥፋትና መጨረስ ሊችሉ ታጋሹና ጀግናው አፄ ምኒልክ ከ10 (አስር) መኮንኖች በስተቀር እነዚያን በውሀ ጥም ሊሞቱ የደረሱና የደከሙ ምርኮኞችን በሙሉ ለቀዋል። ይህንንም ያደረጉበት የሰላም እጃቸውን ለመዘርጋትና ነገሩን በሰላም ለመጨረስ ነበር። አፄ ምኒልክ እነዚህንም 10 የጣሊያን መኮንኖች የያዙት በሰላም ድርድሩ ጣሊያኖችን እንዲስማሙ ለማድረግ ነበር። ነገር ግን ጣሊያኖች ለሶስተኛ ጊዜ ሰላምን የሚፈልጉ መስለው ለጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ።

## 3. የአድዋው ጦርነት

የአድዋ ጦርነት ለሶስተኛና ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገው ነበር። ጣሊያኖች ሁለት ጊዜ መሸነፋቸው ዕብሪታቸውን ስላላበረደው በጄኔራል ባራቴሪ እየተመሩ 17,000 (አስራ ሰባት ሺህ) ወታደሮች ይዘው ለመጨረሻው ጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ። በኢትዮጵያ በኩል አፄ ምንሊክ ጦራቸውን ወደ አድዋ እንዲሰፍር አደረጉ። ለአንድ ወር ያህል አሁንም ሰላም ፈላጊ መሆናቸውን ለማሳወቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ጣሊያኖች ግን ሰላም ለመፈለግ በማስመሰል ለጦርነቱ ጊዜ ለማግኘት ነው እንጂ ሌላ ሀሳብ አልነበራቸውም።

በዚሁም መሰረት ጄኔራል ባራቴሪ በ(DATE) ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከፈተ። የኢጣሊያ ጦር ሁለት ጊዜ የማያወላውል ሽንፈት ስለደረሰበት ከፍተኛ የሞራል ድክመት ያሳይ ነበር። በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ ሞራሉም ጥንካሬውም ጀግንነቱም ይበልጥ እየየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም ነበር። ጦርነቱም ቀኑን ሙሉ ተካሂዶ እስከ እኩለ ሌሊት ቀጠሉ። በመጨረሻም እምዬ ምኒልክ ለአንዴም ለሁለቴም ለሶስቴና ለመጨረሻ ጊዜ ዕብሪተኛውን የጣሊያን ኃይል ደመሰሱት። በዓለም ታሪክ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ ወታደሮች በመሣሪያ ኃያልነቱ የታወቀውን የአውሮፓ ጦረኛ አንበረከኩት። አፄ ምንሊክም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች የብልህ፣ የታጋሽ፣ የአርቆ አሳቢ፣ የኩራትና የጀግንነት ምልክት ሆነዋል።

ጣሊያንም ሌላ ውርደት ሳይመጣበት በመጨረሻ የኢትዮጵያን ነፃነት በማወቅ፣ በመገንዘብና በመቀበል በ ዓ.ም. ውል ፈረመች።

ስለዚህ እኛም ኢትዮጵያውያኖች ይህንን ቀን በደስታ፣ በኩራት፣ ራስን በማወቅና በአንድነት ለዘላለም እናከብረዋለን።

የአገራቸው ታሪክ ከየሚያኮራቸው ኢትዮጵያውያኖች በአትላንታ

# እቴጌ ጣይቱ

( ማራ ታከለ ከአትላንታ)



እኔ የማቀርብላችሁ በአድዋ ጊዜ ሕዝቡን አስተባብረውና መርተው ድል ካጎናፀፉን አያሌ ሰዎች መካከል አንዷና ዋናዋ የሆኑትን የእቴጌ ጣይቱ ብጡልን ታሪክ ነው። ልጠቅሰው የፈለግኩትም ለጦርነቱ መጀመርና ከተጀመረ በኋላ የሰሩትን ዋና ዋና ሚናዎች ነው። እነሱም፣

1) በመጀመሪያ የውጫሌ ውል በአማርኛ እንዲተረጎም ማድረጋቸው ነበር። አስተርጓሚውም ተጠርቶ ሲያስተረጉም ሳለ ኢጣሊያዊው ኢትዮጵያዊውን አስተርጓሚ እንደገሰፀው ከፊቱ በመረዳት አንተ የእኛን ሰው ልትቆጣ መብት የለህም ብለው ኢጣሊያዊውን አሳፍረውታል። ከዚህም በኋላ ነው ያ ሸር ያዘለው የውጫሌ ውል 17ኛው አንቀፅ ምንነቱ የታወቀው፣

2) እቴጌ ጣይቱ ሁልጊዜ መመሪያቸው ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያኖች ሲሆን ጣሊያኖች ግን ኢጣሊያ ለኢትዮጵያ በውጭ አገር ለሚሆነው ሁሉ ሞግዚት ትሆናለች ነበር። በዚህ ነገር ላይ አፄ ምንሊክ የጦር ባልደረቦቻቸውን ሰብስበው ሲወያዩ፣ እቴጌ ጣይቱ ራቅ ብለው ተቀምጠው ጥጥ እየፈተሉ ሲያዳምጡ፣ ከጦር መሪዎቹ ውስጥ አንዱ ትልቅ ወንድማቸው ራስ ወሌ ብጡል ስለነበሩ ወደእሳቸው እንዝርታቸውን ወረወሩባቸው። ይህን ያደረጉትም ከመዋጋት እንደራደር እንዳይመርጡና መዋጋት ከፈራህ እንደሴት ወይዘሮዎች ጥጥህን ፍተል ለማለት ነበር። ይህን የተባለውም ወንድም በዘመኑ ወግ ጀግና ወንዶች ከጦርነት ሜዳ ውለው ድንበራቸውን ማስከበር፣ ከወራሪ ጠላት ግዛታቸውን መከላከልና በበለጠ ግዛታቸውን ማስፋት ስለነበር መዋጋት አለብን ብለው ከአፄውና ከጦር ጓደኞቻቸው ጋር ወሰኑ። ከዚህም ቀን ጀምሮ ዝግጅቱ ቀጠለና ጉዞው በጥቅምት ወር በእኛ አቆጣጠር 1888 ባፈረንጆች 1895 ተጀመረ።

እቴጌ ጣይቱ ከባለቤታቸው ከአፄ ምኒሊክ ጋር ወደ ጦርነት ሜዳ ሲሄዱ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ቢሆንም ከድሮ ባሎቻቸው ጋር ግን ከብዙ ጦርነቶች የተካፈሉና ብዙ የጦርነት ልምዶችን የሰበሰቡ እንደነበሩ ታሪክ ይጠቅሰዋል። ምንም እንኳ እቴጌይቱ እድሜአቸው የገፋ ቢሆንም መጪው ትውልድ ይጨነቅበት፣ ለየትኛው ዕድሜዬ ሳይሉ፣ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያኖች በሚለው መርሆአቸው ፀንተው የሚደርሰውን እልቂት፣ ረጅሙን ጉዞ፣ መራብ መጠማትን፣ መታረዝንና ሌሎችንም እንዳሉ ቢያቁም ይህን ሁሉ ተቁዋቁመው ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያኖች ለማስረከብ ቆርጠው ተነሱ።

2) እቴጌይቱ ራሳቸው የሚመሩዋቸውና የሚያስተዳድሩዋቸው 5 ሺህ በጣም የሰለጠኑና የታጠቁ ወታደሮች ነበሩአቸው። በጊዜው የነበሩት የውጭ አገር ፀሐፊዎች እንዳስቀመጡት የንግስቲቱ ወታደሮች ከንጉሱ ወታደሮች የተለዩና የላቁ፣ ትዕዛዝ አክባሪዎች እንደነበሩ ፅፈውት ይገኛል።

ከዛም በመቀጠል እቴጌይቱን እንደሌሎች የኢትዮጵያ ሴቶች የንቃተ ህሊናቸው በጣም የላቀ፣ ጠንካራ መሪ፣ እጅግ በጣም ቁንጅናቸው ማራኪ በጠቅላላው አነጋገር ደግሞ ታላቅ ሴትዮ እንደነበሩ ፅፈውት ይገኛል።

3) በጦርነቱ ጊዜ ሁሉም በየደረጃቸው ኃላፊነቱን ተከፋፍለውት ነበር። የእቴጌይቱ ኃላፊነት የነበረው የመሪዎችን ልብስ፣ የክብር እቃዎች፣ የስጦታ እቃዎችን፣ እንዲሁም ለንጉስና ለመኳንንቶቹ መዝናኛ መጠጦችንና መጠጫዎችን ማጋጋዝ ነበር። በተጨማሪም ከ20,000-30,000 የሚሆኑ ሴቶችን ስንቅና ውሃ ለወታደሩ ተሸክመው እንዲከተሉ፣ ቁስለኞችን እንዲንከባከቡ ማሰማራትና መምራት ነበር። ለዚህም ተግባር ይተባበሩዋቸው የነበሩ የሁለት ሴቶች ስም ተጠቅሶአል። እነሱም ወ/ሮ ዘውዲቱ ምንሻክና ወ/ሮ አዛለች ነበሩ። ይህን ያዩ ፀሐፊዎች እንዳስቀመጡትም ሴቶቹ ከባድ ሸክም በወገባቸው ተሸክመው የተቀዳደደ ልብስ ለብሰው እየዘፈኑና እየሳቁ ሲጓዙ ሠርግ ወይም ደስታ ቦታ ያሉ ይመስላሉ።

4) በጥቅምት ወር ከአዲስ አበባ ጉዞ የጀመረው ወታደር በጥር ወር መቀሌ ደረሰ። መቀሌ ላይም ጠንካራ ምሽግ የያዘ የጠላት ጦር ነበር። ይህን ጦር ለመምታት በራስ መኮንን የሚመራው ተዋጊ ክፍል ጦርነት ጀመረ። ቦታው አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ በራስ መኮንን ላይ የመቁሰልና በ500 ወታደሮች ላይ የሞት አደጋ ደረሰ። በዚህ ጊዜ እቴጌይቱ አዲስ ሃሳብ አፈለቁ። መፍትሄውም ይሄው ብቻ ሆነ። ዘዴውም ከምሽጉ ውስጥ ያሉት የጣሊያን ወታደሮች ውሃ የሚቀዱበትን ምንጭ በራሳቸው ወታደሮች

ማስከበብና የጠላትን ጦር ውሃ መከልከል ነበር። ይህን ከወሰኑ በኋላም የሚቀጥለውን ንግግር ለወታደሮቻቸው አደረጉ።

"እናንት ወታደሮች ከምሽግ ገብታችሁ የጨበጣ ውጊያ ለማድረግ የምትፎከሩ ሁሉ፤ የጠላት ቁጥር ከእናንተ ያላነሰ መሆኑን እወቁ፤ በሩ አንድ ብቻ ነው። እኔ እገባ እኔ እገባ ስትሉ እርስ በእርሳችሁ ትተላለቁና ጠላት ከሚያደርሰው ጥቃት የበለጠ ይሆናል። ከዚህ ከምሽጉ ገብታችሁ ለመሞት ከቆረጣችሁ ከዛም ውሃው ካለበት ሜዳ ሄዳችሁ ለመሞት አትፈሩም፤ ለዚህ አላማ ፈቃደኛ ለሆናችሁ ሁሉ ተስካራችሁን አወጣለሁ። ልጆቻችሁን አሳድጋለሁ። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን፤" ብለው ንግግራቸውን ደመደሙ።

ይህን ንግግር የሰሙት ወታደሮችም ከምሽጉ ገብተው የጨበጣ ውጊያ ከማድረግ ይልቅ ውሃውን መከበብና መጠበቅ ወደር የሌለው ስራ መሆኑን ተረድተው ውሃውን ከበው ለ2 ሳምንት ተቀመጡ። በዚህም የተነሳ የጠላት ወታደር ውሃ የማግኘት እድሉ እየመነመነ ሲመጣና በተለይም በበርሜል ያስቀመጡት ውሃ ወደ አረንጓዴ ሲለወጥ ሲያዩ፣ በረዎች፣ ፈረሶች በቅሎዎቻቸውና ሌሎችም እንስሳዎቻቸው በውሃ እጦት ምክንያት ሲያልቁ፣ የጦር መኮንኖች ሳይታጠቡ ሳምንታት ሲያልፋቸው፣ በምጥ ላይ ያሉ የባንዳ ሚስቶች ውሃ ሲጠይቁ የሚሰጥ ሲታጣ፣ በጠላት ጦር ላይ ትልቅ ሽብር ተፈጠረ። ተስፋ መቁረጥም መጣ፤ ወኔውም ወደቀ። ይህ እንደሆነ ሮማ ሲሰማ የሮማው ንጉስ መጠቃቱን ሲያውቅ ልቀቁ የሚል መልዕክት ላከ፣ ሲነበብም የመቀሌ ምሽግ ለአብሲና ንጉስ ይሁን የሚል ነበር። የጦር መሪውም እያለቀሰ አስረክቦ ለቀቀ። የኢትዮጵያ ባንዲራም በቦታው ላይ ተውለበለበ።

5) ጠላት ነገሩን ለማለስለስ ሲል ሌላ ድርድር እንደተለመደው ለማድረግ መልእክተኛ ወደ ንጉስ ላከ። በየካቲት 2ኛ ሳምንት ላይ መልዕክቱን ይዞ ከአፄ ምንሊክ ዘንድ የደረሰው ሰው ሻለቃ ሳልሳ የተባለ ነበር። እቴጌ ጣይቱ የዚህን ሰው ሁኔታ አይተው ለቀረባቸው ሰዎች ያ ሰው የመጣው እርቅ በመፈለግ አይመስለኝም። እኛን ለመሰለል ነው ብለው ተናገሩ። የጠረጠሩትም እውነት ሆነና ሰውየው ያመጣው መልዕክት፣ የውጫሌን ውል ለማደስና ከኢጣሊያ የተነጠቀውን የኢትዮጵያ ግዛትም ለኢጣሊያ ለማስመለስ ነበር። ይህንን እቴጌ ሲሰሙ በመደነቅና በመገረም ወደ ሰማይ ቀና ብለው እያዩና እንባቸውን እያፈሰሱ፣

"አንተ የእስራኤል አምላክ ይህን ግፍ ተመልከተው፤ በመድፋቸውና በጠበመንጃቸው ተመክተው እንደልባቸው ይናገራሉ። ያላወቁት ቢኖር ኃይል የእግዚብሔር መሆኑን ነው፤ እኛ ግን በመድሃኒያለም እርዳታ ነው የምንመካው፤ አንፈራም!" አሉ።

ከዚህም በኋላ እቴጌ ጣይቱ ወታደሮቻቸውን አሰማርተው፤ ሴቶቹንም አደራጅተው ጉዞአቸውን ወደ አድዋ ቀጠሉ። አድዋ ላይ ጦርነቱ ተጀምሮ ጥይት እንደዝናብ በሚወርድበት ጊዜም በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው እግዚአብሔርን ይለምኑ ነበር። ከበቅሎአቸውም ወርደው በግራቸው እየገሰገሱ በዚህ ቀውጢ ሰአት ወታደሮች ወደኋላ ሲሸሹ በቆራጥነት እየጮሁ፣ ጠንክሩ፣ ድሉ የእኛ ነው ተዋጉ ሲሏቸው አምርረው መዋጋት ቀጠሉ። ይኼኔም ነው የጠላትን ጦር መሃል ለመሃል ገብተው የበታተኑት። ይህም ዜና ሲሰማ በመላው አለም ጋዜጣዎች የመጀመሪያ ገፅ ላይ የእቴጌ ጣይቱ ፎቶግራፍ ነበር። የኢትዮጵያ የጦር መሪ ንግስት በማለት በአለም ከታወቁት ሴቶች ከነክሊኦፓትራ፣ ጆን ኦፍ አርክና ከካተሪን ዘግሬት ጋር አውዳድረዋቸዋል።

ወደ መደምደሚያ ልምጣና እቴጌ ጣይቱ እንደ ወንዶች ታጥቀው ወታደሮችን በመቀለድ፣ በማሳቅ ስራቸውን እንዳይረሱ በመጎትጎት፣ መነኩሴዎችን የሚሸሸውን እንዲገዝቱ በመምከር፣ የቆሰሉትን በመንከባከብ፣ ውሐ እያጠጡ፣ ጥይት እያቀበሉ፣ ሌላም ሌላም አያሌ ስራዎችን በመስራት ይህን ዛሬ የምናከብረውን ድል አጎናፅፈዋል። በአጭር አነጋገር ለዚህ ድል መሳካት አስተዋጽኦ ካደረጉት ውስጥ አንዷ ናቸው።

እንግዲህ አያቶቻችንና እናቶቻችን ይህን የመሰለ ታሪክ በመስራት ስኖሪታ፣ ማበጋሪታ፣ ከመባል አየለች፣ አበበች፣ ቢፍቱ፣ ደራርቱ፣ መሪማ፣ ፋጡማ የሚል ስምና ኢትዮጵያዊት የሚባል መለዮ እንዲኖረን አድርገዋል። እኛስ የአሁኑ ትውልዶች ሴቶችና እናቶች ምንድነው ለልጆቻችን የምናወርሰው? ከአሁኑ በአስቸኳይ ካላሰብንበትና ተባብረን ካልሰራን ልጆቻችን ኢትዮጵያዊትና ኢትዮጵያዊ መባላቸው እየከሰመ ነው፤ ያከትማልም።



የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ሣራ ታከለ

## ለአድዋ ያልሆነ ግጥም ከትውልድ ትውልድ ይረገም!!

# አድዋ የአርበኞች ልደት!!

ከልሳኑ ስምረት
(ሴንት ሉዊስ ሚዙሪ)

እናት ዓለም አድባር አድዋ የአጋዝያን መሰብሰቢያ
የገድለ ሰማዕታት ምሽግ የትውልድ ሁሉ መጠሪያ
ሰንደቅ ዓላማ ሆነሽ የነጭ ቃፊር ማስፈራሪያ
ያንበሳ ለምድ አድርገሽ የጀግኖች መጎናፀፊያ፤
የቀስተ ደመና ችቦ ኅብረቀለም ማሰረጊያ
አረንጓዴ ብጫ ቀዩን የነጭ በነጭ ማስጠለፊያ
የወሰን ሐረገወይን የጥበብሽ ሁሉ ዙሪያ
ድንበርሽን መከወኛ ሰውነትሽን ማስከበሪያ።
ዋ አድዋ!

ኬንያታን ያስታማርሽባት መጣፍሽ ታጣጥሎ
ንክሩማን የኮራብሽ ገፅሽ ሁሉ ተገንጥሎ
ወመዘክርን ያሳመረው መደርደሪያሽ ተመንጎሎ
የፀረ–ፋሺሽት ብርጋዊነትሽ
በድቅድቅ ፅልመት ተከልሎ፤
ጥቁር እስራኤላዊ ልብሽ በዘረኛ ቀስት ተነድሎ
ደምሽ ከደማቸው ላይሆን ሕዋስሽ ተገልሎ
ለሚጠና ተላላፊ ርዳታሽ ሁሉ ተጥሎ
በወጪት ሰባሪነታቸው በጎ ተግባርሽ ተገድሎ
የአርበኞች የስደት ነፍስሽ በአራጣ መክሊት መግሎ።
ዋ አድዋ!

ምንሊክ የመከረብሽ ሰገነትሽ ተገርስሶ
ብሔራዊነቱ ጠፍቶ ዝናው ሁሉ ተደርምሶ
ጫማ ሳይለብስ ገዥ ሆኖ ጥቁርነቱ ተደምስሶ
ገበናው ሳይመዘን ሥራው ሁሉ አፈር ለብሶ
ሌላው ፃድቅ እንደሆነ እርሱ ብቻ ተወቅሶ።
ዋ አድዋ!

ቦዘን ሳይሆን ተገን ምሶ
ከርቸሌን አተራምሶ
ጌቶ ባሪዮን ቀስቅሶ
ሥጋሽን ሥጋው ለብሶ
በወገኑ ተጠብሶ
ማልኮለም ያገሳብሽ ማይክሮፎንሽ ተቦርቅሶ።
ዋ አድዋ!

ውጫሌ የተመካሽበት ጀግናሽ ሁሉ ለፍርድ ቀርቦ
ታሪክሽ በውሸት ታጥቦ
እውነትሽ ተደልዞ የሐቅ ፍሬሽ ተንቀርቅቦ
የጥቁር ወኔ ተዓምርሽ በጠማማ ፋስ ተጠርቦ
ፀረ–ኮሎኒያሊስትነትሽ በዘር እሳት ተለብልቦ
ገበየሁን ያናርሽበት ክቡር ዝናሽ ተሰልቦ
የጣይቱ ብጡል አርበኝነት የነብር ጥፍርሽ ደድቦ
እንስት በቁጥሯ ሳስታ መወጪያ በሯ ተገርብቦ
ባልቻ ያስተጋባብሽ ልሳንሽም ተሸብቦ
ያሻፈረኝ አልገዛም ወኔሽ አልቆ ተንጠባጥቦ።
ዋ አድዋ!

እንዲህ እንደዛሬው ሳይሆን የውስጥ ሕሊና ሳይፈተን
እንደምሳሌ ሆኖ ወግ ሲተረክ ልብን ሰልቦ
መጥረቢያ ጫካ ቢሔድ ከብረት ጋር ተደርቦ
ምድረ ዛፍም ተንጫጫ እርስበእርሱ ተተራርቦ
ቅርንጫፉም አጉረምርሞ
እጀታው የእኛ ነው ብሎ፣ እጅግ ሠግቶ በአርምሞ
መጥረቢያውስ መቼ ቀናው
ስንቱን ጥሎ ስንቱን ይግደል።
ተሰባብሮ ተገንጥሎ ወደቀ አድዋ ገደል።
ዋ አድዋ!

ዝመት ክተት መፈክርሽ የትውልድሽ ማንጎራጎሪያ
የጀግኖችን ሥንጥር አጥንት ቀሰም ሰርተሽ መጣጣፊያ
ቆዳቸውንም ገርግደሽ ፊደል አዘል መክተቢያ
ደምን ከደም አደባልቀሽ በራስ ቅላቸው መቀመሚያ
እንደ አዝሙድ መከለሻ እንደእዋዜ ማሳመሪያ
የጥቁር ታሪክ ማብሰሪያ፤
የሠዓሊ ድንቅ ሥራ የቀለማት ሁሉ ማጉሊያ
የብርሃን ርቱዕ ምሶሶ የጃኖ ጥበብ መሥሪያ
የኢቶጵስ ማስተርፒስ አድዋ የጥቁር ማሊያ
የኩሩ ከፈን ማልበሻ የወገን አዝማድ ማስኮሪያ።
ዋ አድዋ!

ጊዜ ሲርቅ ላትነግሪ ዘመን ጥሎሽ ልትፈሪ
መቅድም ዜማን ላትዘምሪ
ጦርነት ላሰቃየው ለዚህ ሁሉ ጉድ ቀባሪ
ለድሐው የአበሻ ልጅ በትምሳሌሽ ላታበሪ
ፊትሽን ከገፆችሽ ዓይንሽ ፊጦ ላታዞሪ
አርአያ ታሪክ ሆነሽ ኔግሮን ሁሉ ላትመሪ
በጄንጂስካን የግል ዕቅድ ሀብትሽን ላትመነዝሪ
ኃሳብሽን ላትፈፅሚ በካደሽ ዘር ቆጣሪ።

ዋ አድዋ!

አለቅሳለሁ እንዳትይ፣ ጉንጮችሽን ልትቦጭሪ
ተንሰቅስቀሽ ላታባሪ
ነፍስሽ ከድቶሽ ተስቆብሽ ልጆሽን ላትገሪ
አንጓሽ አብጦ ዓይንሽ ሰምጦ
ጅማትሽን ልትወጥሪ
ደምስርሽን ላታረግቢው አጠላልፈሽ ልትገትሪ
የወላድ መሐን ሆነሽ ዘሮችሽን ልታነዝሪ
እንደእንቁ የአሞራ ልጅ ሀገር ለአገር ልትበሪ
በአራት ማዕዘን ልትረጪ ልጆችሽን ልትዞሪ
ሳይመክሩልሽ ሊበተኑ ሳይቆሙልሽ ሊናከሱ
አንቺም ፈርተሽ ላታስፈሪ።

ዋ አድዋ!

ባይላካም የቆመልሽ የቀይ ሽብሩ ዒላማ
የዚያ የቅርብ ትውልድ የእናቴ ልጅ የእነእማማ
ሁሉን አቀፍ ምኞተኛ የገጠሩ የከተማ
አፍላ ነፍሱን የገበረ የእሳተ ገሞራ ማግማ።
ዋ አድዋ!

አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም አድዋ የገድል ጣሪያ
መራር እንቆቆ መድኃኒት የአልገዛም ማሽሪያ
የተገፋ ሕዝብ የምልዐቱ የማጽያን መወደሪያ
ያልበገሬ ብሔራዊ የደመነፍሱ መታወቂያ
የአፍሪቃ የይለፍ ቪዛ የክልል ድንበር መስበሪያ
የፅንፈኞች ማኮማተሪያ የሽረኞች ማንበርከኪያ።
ዋ አድዋ!

ፍጥረትሽን ለሰረዘው ጂን ዘርዛሪ ጮሌ ኮብራ
ልጆችሽን ለሚያጋጨው ለመጭው ውጤት ሳይፈራ
የመርዶ ድምፅ ቀረርቶውን በቅዱስ ቃል ለሚጮኸው
ሆደባሻ ህዝባችንን እንደአክርማ ለሚልጠው
ለአዲስ ስሪት የንግድ ዘፈን ቃና አራራት ለሚሰጠው
አድዋ ልብ አስገዢው ባይሰማ ደግመሽ ንገሪው
ሰንብተሽም ቃል አብራሪ በቁጣሽ ኃይል በእሮሮ
ላልተረዳው ከለልተኛው ለባዕዳን ክፍት ማሰሮ
ለእውቀ አጥፊም ጥላወጊ ለሚነሳው ነገር ፈጥሮ
ዋ አድዋ!

የማንዴላ የዘርዓይ የጴጥሮስ ብቸኛ ግርግም
የነፃነት ሥነ-መለኮት የደጓው ርዕዮተ ዓለም
የክርስቶስ ፔዳጎጂ ድኃን መራጭ ልዩ ማኅተም
የሉቡምባ የኒሬሬ አቡጊዳ የፊደል መቅድም
የምድረ ናሽናሊስቱ የኔግሮ ሖርሞን ቀይ ፍም
ዋ አድዋ!

የጊዜ ቦምብ ሳይፈነዳ የቦስኒያ ስቃይ ብካይ
አሁንም እንዲህ ሳይሆን የዓባይ ወንዝ ሳይጨቀይ
ደም ውኃን ቀይ ከልሶ ውስጠ ልብን ሳያሰቃይ
ተከዜም ጋሽም ተከፍሎ ውኃ ደርቆ ምች ሳይታይ
ገናሌም ሐሩር መቶት የፀር እሳት ሳያደባይ
እንደሩዋንዳ ከጌራ ወንዝ ሬሳ ሳይሆን
የሰው ድልድይ
ባሩድ ጅረቱን ሳያከብድ የመርዝ ዞግ ሳይሆን ስራይ
አድዋ አስተምሪው የአበሻን ልጅ በጧት ፀሐይ።
የይገብር ካላችሁ ይገብር የተሜ መድረክ መሰብሰቢያ
የየዋህ ኢንቴሌጂንስያ
የድርሳኑ መቆለፊያ የኮፌዳው መሰነጊያ
የቀን መንገድ የተጓዘልሽ ምሑርሽ በዝብጥያ
የኢቶጵስ ማስተርፒስ አድዋ የጥቁር ማሊያ
የኩሩ ከፈን ማልበሻ የወገን አዝማድ ማስኮሪያ
ዋ አድዋ!

የሳንዲኖ ሰረገላ በጠፍ ጨረቃ መስገሪያ
የጂናሪሞ የአንገቱ መጠምዘዥያ
የሹል ጥርሱ መለጎሚያ
የካምፓሲኖ ኤነርጂ ናፍጣ ማቀጣጠያ
የቺያስ መራር ሐሞት የድፍርስ ቅርሻት ማጥሪያ
የሪዘርቬሽን ኬላ ሰባሪ የክልላቸው ሁሉ መዝለያ
የበርሊን ግርግዳ በታች ድጅና መሰርሰሪያ
የፓን አፍሪክ መውዜር ሊበን ጠይም ውልውል መሣሪያ
አድዋ ታላቅ ደመላሽ እብሪተኛን ማስነጥሻ
ዕርዳታቸውን ማጋለጫ መዋቅራዊ ኃጢአት መስበሪያ
የኢቶጵስ ማስተርፒስ አድዋ የጥቁር ማስኮሪያ
ዋ አድዋ!

የስዌቶ ሻርናቪል ዘረኛ ነቀዝ ማስከነፊያ
የተፈሪ ኃይለስላሴ የልጅነቱ መፈንደቂያ
የሺመቤት ልጅ ማሠልጠኛ የማይጨው መቦረቂያ
የዲፕሎማሲ ስጋጃ አሜድላ ላይ ማስጠለፊያ
ራስሽን ቀንቶት ላትነሺ በጂሶ እንደተለሰንሽ
አሁንም ኩሉ አርአያ
የኢቶጵስ ማስተር ፒስ አድዋ የጥቁር ማሊያ
የኩሩ ከፈን ማልበሻ የወገን አዝማድ ማስኮሪያ
ዋ አድዋ!


A TO Z
ELECTRONICS
& GIFTS
220V/110 Volt Appliances
*Audio-Video-Toys-Cameras-Phones-Stereos-Luggage-*
*Fax Machines-Watches-Gift Items* - Etc.
ኤ ቱ ዜ ኤሌክትሮኒክስ
We do Digital Vedeo Coversion
From PAL to NTSC & Vice Versa
ከፖል ሴካም ወደ ኤንቲሲና
ከኤንቲሲ ወደ ፖል ሴካም
ቪዲዮ መገልበጥ
ኢትዮጵያ መስራት የሚችሉ
ባለ 220 ቮልት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
በርካሽ ዋጋ
1713 CHURCH ST., SUIT A-1
DECATUR, GA 30033
*Jayendra Patel & Dipa Patel*
Tel/Fax: (404)299-9196

# ኢትዮጵያዊነት ሲያኮራ

ከቴዎድሮስ ጥላዬ – (ከአትላንታ)

የዘንድሮን የአድዋ ድል በዓል አከባበር ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ የድሉ መቶኛ አመት ቢሆንም ከዚያ በበለጠ ግን ኢትዮጵያውያን ለአንድነታቸውና ለነፃነታቸው ያላቸውን ቀናእናዊነት በተግባር በአንድነት ሊያረጋግጡበት የሚገባ ወሳኝ ወቅት ላይ መሆኑ ነው።

አባቶቻችንና እያቶቻችን አገራቸውን ከውጭ ወራሪ ኃይል ለመጠበቅ ቀስቃሽና ጎትጓች ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው ስንቅና መሣሪያ ተጠቅመው "ጥራኝ ዱሩ፣ ዱሩ ቤቴ" ብለው ዘምተው ወደር በማይገኝለት መስዋዕትነት አገራችንን ከነአንድነቷና ነፃነቷ ጠብቀው ለትውልድ አስተላልፈዋል። ዛሬ ከ100 አመት በኋላ በተፈጠረው ትውልድ ላይ ግን ያ የአገር ፍቅርና የነፃነት ናፍቆት ላልቶ አልፎ አልፎ ከስሞ ይታያል። ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችል ይሆናል። ነገር ግን በተለይ የአገር ተረካቢና ገንቢ መሆን በሚገባው ወጣት ትውልድ ላይ የሚታየው የግድየለሽነትና የምንአገባኝ አይነት አስተሳሰብ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው። ይህን አስተያየት ለመሰንዘር የደፈርኩት ያለ ምክንያት አይደለም። በአሁኑ ወቅት በተለይ በስደት አለም የሚገኘው ወጣቱ ትውልድ የመጣበትን አገርና ሕዝብ የረሳ ይመስላል። በእርግጥ አገራችን ከድሆች ተራ የመጨረሻውን ቦታ እየተሰጣት ያለ ቢሆንም ወደድንም ጠላንም ተወልደን አድገን ፊደል የቆጠርንባት አገራችን መሆኗን መዘንጋት የለብንም። ዛሬ ዛሬ እንደሚታየው የአገራቸው ድህነትና የጦርነት ሰለባ መሆን እያሳፈራቸው ማንነታቸውን ክደው በሌላ አገር የተሰየሙ አንዳንድ አልባሌዎች አልጠፉም። በተለይ አሜሪካን አገር "ከየት መጣህ?" የሚለው ጥያቄ አዘውትሮ የሚጠየቅ ስለሆነ የኛዎቹ ስልጡን ተብዬዎች አንዴ ከጃማይካ ነኝ አንዴ ከዚያ ነኝ እያሉ በመዘባረቅ አገራቸውን ሲክዱ ይታያሉ።

ለዚህ ጽሁፌ መነሾ የሆነኝ ዋናው ቁምነገር ከዚሁ ከላይ ከጠቀስኩት ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ስላለው ወደ ጉዳዩ እመለሳለሁ። በዚህ እኔ ባለሁበት የአትላንታ ከተማ የአድዋ ድልን አከባበር አስመልክቶ የደመቀ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። በዕለቱ በግምት ከ400 እስከ 500 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በከፊል በባሕላዊ ልብሳቸው አሸብርቀውና ልጆቻቸውንም አድምቀው የተገኙ ሲሆን በበዓሉ ላይ የተገኙ ጥቁር አሜሪካዊያን እንግዶችም ነበሩ። ምንም እንኳን በአትላንታ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከ7ሺህ እስከ 8ሺህ ቢገምትም በበአሉ ላይ የተገኘው ብዛት ግን ሳያስተዛዝብ አይቀርም። የአዘጋጅ ኮሚቴው አባላት ገንዘባቸውንና ጊዜአቸውን ሰውተው ለበአሉ መሳካት ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል። ለዚህም ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል።

እንዲሁም ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲያውቀው በተለያዩ አካባቢዎች በራሪ ወረቀቶች በመበተን ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ቢሆንም በአብዛኛው የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ተብሎ የታለፈ ይመስላል። ከነአካቴውም የአድዋ ድል በአል የሚባል እንዳለ የረሱም አልጠፉም። ምናልባት ከዚህ ዓይነቱ ወቀሳ በውጪ አገር ተወልደው ያደጉ ወጣቶች ሊድኑ ቢችሉም ወላጆቻቸው ግን የትውልድና የዜግነት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ከተወቃሽነት አያመልጡም። በዚህ አጋጣሚ ልጠቅሰው የምፈልገው ቁም ነገር አለ። ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ለልጆቻቸው የአገራቸውን ቋንቋ ባህልና ወግ ማስተማር ይገባቸዋል። ልጆቻቸው ተወልደው የሚያድጉበትን አገር ቋንቋ በቀላሉ ግን ሊማሩ የሚችሉት እቤታቸው ብቻ ነው። ስለዚህ ይህን እንገብጋቢና ጠቃሚ ጉዳይ ስራዬ ብለው ሊያስቡት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ወደ በዓሉ አከባበር ስነስርዓት ልመለስና ስለተደነቅሁባቸው ጉዳዮች ትንሽ ልበል። በእለቱ በግጥምና በስድ ንባብ የቀረቡት መነባንቦች ጠቃሚ ትምህርት ያዘሉና መንፈስንም የሚያነቃቁ ነበሩ። ከሁሉም የበለጠ የሁሉንም ልብ የነካውና የአንዳንዶቻችንን አይን እንባ ያስቀረረው ከዕለቱ ተጋባዥ እንግዶች ከነበሩት መካከል በአንድ ጥቁር አሜሪካዊ የቀረበው ንግግር ነው። በእውነቱ ለመግለፅ በሚያስቸግር የአድናቆት ስሜት ተውጬ ነበር ያዳመጥኳቸው። ሰውየው ዶክተር ዶናልድ ቬስት (Donald Vest) ይባላሉ። መልካቸውና አቋማቸው የኢትዮጵያዊነት ገፅታን የተላበሰ ቢሆንም ከአንደበታቸው የሚወጣው ንግግር እና በልባቸው የሚፍለቀለቀው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊያን ፍቅር ደግሞ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ያደርጋቸዋል ብል ማጋነን አይሆንም። በበለጠ ደግሞ ከትከሻቸው ላይ ጣል ያደረጉት ባለቀይ ጥለት ነጠላ ለማንነታቸው መታወቂያ ሆኗቸዋል። የአድዋ ድል በኢትዮጵያዊያንና በሌሎች ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ የፈጠረውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ሲያወሱ በተደጋጋሚ "ኢትዮጵያ አገሬ ናት፣ ኢትዮጵያ መንፈሳዊ ቤቴ ናት" ይሉ ነበር። ታዲያ እኒህን ሰው ያዳመጠ ሰው እውን ኢትዮጵያ ምን ያህል ብታኮራቸው ነው? ምንስ ያህል ታሪኳን ጠልቀው ቢያውቁ ነው ብሎ ሊጠይቅ ይገባል። እንዲሁም ይቺን የብዙዎቹ መኩሪያ የነበረችና የሆነች አገር እንዴት እንዳለች ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል በሚለው ጉዳይ ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆነ ሁሉ ሊያስቡበት ይገባል። በተረፈ በቸር ይግጠመን።

ቴዎድሮስ ጥላዬ (አትላንታ)

# ከልብ እናመሰግናለን !!

በኢትዮጵያና በዓለም የጥቁር ሕዝብ ታሪክ ከፍተኛ ቦታ ይዞ የሚታወሰው የአድዋ ድል 100ኛ ዓመት በዓልን እ ኤ አ March 1996 በአትላንታ ከተማ American Legion ተብሎ በሚታወቀው አዳራሽ በከፍተኛ ድምቀት ማክበራችን ይታወሳል።

በዚሁ በዓል በአትላንታና አካባቢዋ ነዋሪ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን እና ታሪኩ ይመከተኛል ብላችሁ ለተገኛችሁ ሁሉ፤ እንዲሁም ለዚሁ በዓል መሳካት የገንዘብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ላደረጋችሁልን ሁሉ የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ በአክብሮት ምስጋናውን ያቀርባል።

በተለይም የአድዋን ድል ታሪክን አስመልክቶ ከኒው ዮርክ ጥሪያችንን ተቀብለው በመምጣት ትምህርታዊ ገለጻ ላደረጉት ለዶክተር ንጉሤ አየለና የድሉን ዓለማቀፋዊነት በማስረዳት ገለጻ ላደረጉልት አፍሪካዊ አሜሪካዊ ዶክተር ዶናልድ ኤስ ቬስት (Dr. Donald S. Vest) ከፍ ያለ የአክብሮት ምስጋና እናቀርባለን።

በአትላንታ የአድዋ ድል 100ኛ በዓል ዝግጅት ኮሚቴ







# ኢትዮወርድ EthioWord

## ግዕዝና የዓለም ፊደላት በኢንተርኔት

የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር ግዕዝ ከሌሎች የዓለም ፊደላት ጋር ኢንተርኔት ላይ እንዲጻፍ፣ እንዲታተምና እንዲነበብ አዲስ የኢትዮኔት ግኝት አቅርቧል ። በተሟሉና ባልተቀጠሉ እንዲሁም በተቀጠሉና በጎደሎ ፊደላት በቀጥታና በተዘዋዋሪ እርስ በእርስና ከሌሎች ቋንቋዎች ጽሑፎችና የመሳሰሉት ጋር ተያይዘው (Multi-lingual hyperlinked documents) ግዕዙ ለኢንተርኔት እንዲጻፍና እንዲነበብ ፈጥረናል ። ምሳሌ፦ ዐረብኛ/Arabic (جثجرخخثثث) ግሪክ/Greek (Σ'Ωϱ,ΰώεϑ) ሕብራይስጥ/Hebrew (דּ״ ת״ ב״) ጃፓን/Japanese (ムラモトメヤメトニ) etc. ከአሁን ወዲያ ግን ግዕዙን በአንድ ዓይነት አጻጻፍና አቀማመጥ ብቻ መጠቀም ስላለብን ግኝታችንን ማንም እንዳይቀዳና አስመስሎ እንዳይሠራ እናስጠነቅቃለን ። ኢትዮወርድንና ግዕዝኤዲትን ያዷቸው ለኢንተርኔት የሚያስፈልጓቸውን (Upgrade) በ$49.00 ቢያሟሉ ጠቃሚ ነው ። የግዕዙ ጽሑፎች የሚከፈቱት ልክ እንደላቲኑና በሰማያዊ ቀለም የተጻፉትንና የተሰመረባቸውን የግዕዝ ፊደላት ቃላት በመጫን ነው ። Now you can include Ethiopic texts and even hyperlink them with some other world alphabet texts in your Internet documents. This is another new innovation from the pioneers. You are limited only by your knowledge of the different languages and alphabets as you surf the multi-lingual **Ethionet** with the same browser. If you have EthioWord or GeezEdit, we encourage you to upgrade for only $49.00 and start surfing the Internet by just clicking on the Geez hypertext documents. Publishing on the Internet in Ethiopic requires Ethionet and some other products. Ethionet package includes EthioWord, GeezEdit, free software and manuals for $279.00. **See this first Ethiopic Internet text in our web page.** Please call for more information about server software, Internet access, building and hosting Ethiopic home pages. (Warning: Do not copy our methods since we will publish lists of any violators and institutions in different media even before we take legal actions.)


### የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር

### Ethiopian Computers and Software

**9781 W. Fremont Pl., Littleton, Colorado 80123, USA**


Tel: 303/972-2186, 202/785-1618 and 301/270-3865

Fax: 303/973-4342 or 202/785-1626

E-mail:*Ethiopian@aol.com* — ዶ/ር አበራ ሞላ ፳/፹፰ (3/96)

*http://home.navisoft.com/ethiopian/index.htm*


# ኢትዮኔት



Back to Ethiopian Home Page ወደኋላ ለመመለስ


Copyright (©) 1985-1996 ABSHA/ECS (Dr. Aberra Molla)

# "ታሪክ ከዜናዎች ሲፈልቅ"

(ከሰይፉ መኩሪያ)

እየተከማቹ የሚያስቸግሩኝ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና ወረቀቶችን አስተካክላለሁ ብዬ የጀመርኩት የፅዳት ዘመቻ እስካሁን አልተገባደደም። የቆዩ ፅሑፎች እንደታጠፉ ተረስተው ቁጭ ያሉ ጋዜጦችና ከላይብረሪ ኮፒ አድርጌ የሰበሰብኳቸው ጽሑፎችን እንደገና ስመለከታቸው ብዙ ትዝታዎችን ቀሰቀሱብኝ። ገለጥ ገለጥ፣ አለፍ አለፍ እያልኩ ከተመለከትኳቸው ጽሑፎች ውስጥ እየገረመኝና በተመስጦ ዓይኔን የጣልኩበት "አፍሪካን ኮንቴምፓራሪ ሬኮርድ" ከተባለው ጥራዝ ላይ ኮፒ አድርጌ ያስቀመጥኩትን ጽሑፍ ላይ ነበር። የጽዳት ዘመቻው ቀርቶ የቁም ንባብ ጀመርኩ። "All history is current events" እንደሚባለው ሁሉ በዘመናቸው ዜናዎች (current events) የነበሩ አሁን ግን ታሪክ ሆነው የቀሩ ድርጊቶችን ማስታወስ "የት ነበርን?" በሚል አንክሮ የተጓዝናቸውን ሂደቶች እንድናስስ ይጠቅመናል።

ኮሊን ሌጉም የተባለው ፀሐፊ የየአንዳንዱን አፍሪቃ አገር ሂደት እየሰበሰበ "ለሬኮርድ" በየዓመቱ ከሚያስቀምጠው ጥራዝ ላይ "ETHIOPIA 1969-1970" የሚል አርእስት አለ። ኮፒ አድርጌ ያስቀመጥኩት ከአስር ዓመታት በፊት ነበር። "አፍሪካን ኮንቴምፓራሪ ሬኮርድ" ከሚባለው ጥራዝ ላይ የተወሰደ ታሪክ ነው።

## ኢትዮጵያ 1969/70

ዲፕሎማሲ፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ በአፍሪቃ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በOAU ውስጣዊ ሥራዎች ተጣድፈዋል። የናይጀሪያው እርስ በእርስ ጦርነት ገና አለቆመም፣ የመካከለኛ ምሥራቅ አረቦችንና እስራኤሌን እያጋጨ አካባቢው ይተረማመሳል፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ማሳያታቸውን እያገፉባት ነው። አበበ ቢቂላ በጠና ታሞ ለንደን ሆስፒታል ውስጥ ተኝቷል፣ ንጉሡ አሜሪካንን እንዲጎበኙ ኦፊሲያል ጥሪ ከፕሬዚዳንት ኒክሰን ደርሷቸዋል። የኤርትራው ጀብሀ (ELF) ድምፁን ከሚሪያ ያሰማል። ስዊዝ ካናል በፖለቲካ ምክንያት እንደተዘጋ ቁጭ ብሏል። የአፍሪቃ ድርጅት ተደጋጋሚ ስብሰባዎችን ያካሂዳል። 1969 ለንጉሡ የሥራ ዓመት እንደሆነላቸው ግልፅ ነበር። በብሔር/ጎሳ ተከፋፍለው ጦርነት ውስጥ የተዘፈቁት የናይጀሪያ ህዝቦች ሁኔታ ንጉሡን ከመጠን በላይ እንዳሳሰባቸው ያካሂዱት የነበረው የዲፕሎማሲ ስራዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም የስዊዝ ካናል መዘጋት ኢትዮጵያ ከImport/Export ታገኘው የነበረው ሀብት ማቆልቆሉም አንዱ አሳሳቢ ጉዳይ ነበር። ከሚሪያ ከተማ ዳማስኮ ሆኖ በሬዲዮ የፕሮፓጋንዳ ስራውን የሚያቀላጥፈው ጀብሀ ይባስ ብሎ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላኖችን እየጠለፈና እየሰበረ የኤርትራን ችግር በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ለማስተዋወቅ ይጣጣራል። ኢትዮጵያ ውስጥ ንጉሡን የሚቀናቀን ኃይል ወይም አንድ መሪ አለ ለማለት ባይቻልም፣ የተማሪዎቹ ረብሻ እየባሰባት እንጂ እየቀለለ አልሄደም። ሆኖም ንጉሡን ይበልጥ ያሳሰባቸው የውጪው ዓለም ግኑኝነት እንደነበረ ያካሂዱት የዲፕሎማሲና የሽምግልና ሥራዎች እነሆ ይጠቁማሉ።

Feb.1969 የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ዩታንታን በቤተመንግሥታቸው ተቀብለው ስለናይጀሪያ ጦርነት ውይይት አካሄዱ።

March የእንግሊዝ ጠ/ሚርን አስጠርተው እንደገና ስለናይጀሪያ ጉዳይ ውይይት አካሄዱ።

April የምሥራቅ አፍሪካን ስሚት ጉባዔ ለመሳተፍ ወደ ሉሳካ ሄዱ

June ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማህበር (ILO) በዓል ላይ ለመገኘት ጄኔቫ ሄዱ።

– እግረ መንገዳቸውን ለንደን ድረስ በመሄድ አበበ ቢቂላን ይጠይቃሉ።

– ከዛ ሲመለሱ ግብፅ በመሄድ ፕሬዚዳንት ናስር ጋር ውይይት ያካሂዳሉ።

– የኒዘርላንድ ንግሥት ጁሲያና እና ልዑል በርንሀርድን በቤተ መንግሥታቸው ያስተናግዳሉ።

– የየመን አረብ ሪፐብሊክ መሪ ፕሬዚዳንት ሠይድ አብዱልራህማንን እንዲሁ ያስተናግዳሉ።

July የተላከላቸውን ጥሪ በመቀበል አሜሪካንን ይጎበኛሉ። ፕሬዚዳንት ኒክሰንን ስለናይጀርያው ጉዳይ ያናግራሉ።

Sept ስድስተኛውን የOAU ስብሰባ ይከፍታሉ። በንግግራቸው ላይ የናይጀርያው ጦርነት መፍትሔ ቶሎ እንዲፈለግለት በጥብቅ ያሳስባሉ።

Nov. የሠላሳ ዘጠነኛውን የዘውድ በዓል ያከብራሉ። በዚህ አጋጣሚ ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ "በሕገ መንግሥታችን መሠረት" አልጋ ወራሹ የዙፋኑ ተከታይ መሪ መሆናቸውን በማያሻማ መንገድ ይገልጣሉ።

## የአገር ውስጥ ፖለቲካ

በአገራችን ውስጥ ምርጫ ማድረግ የተጀመረው በኃይለስላሴ ዘመን ነው። በተለይ በ1969 ዓ/ም ላይ ለመምረጥ ከተመዘገቡት ሰዎች ውስጥ ሰባ በመቶው (5.2 ሚሊዮን ህዝብ) ድምፅ የሰጠበትና አዳዲስ እንደራሴዎች የፓርላማ ወንበሮች ለመሙላት የተካሄደው የ'ምረጡኝ' ዘመቻ ላይ አንድ ሺ ሶስት መቶ ተወዳዳሪዎች በመቅረባቸው በተለይ የአዲስ አበባ መንገዶችና የስልክ እንጨቶች በበራሪ ወረቀቶችና በትላልቅ ፖስተሮች አሸብርቃ ነበር። ምርጫው ተከናውኖ አዲሱ ፓርላማ ስራውን በNovember ላይ የጀመረው ከአባሎቹ ውስጥ አብዛኞቹ (68%) ለሥራው ጀማሪዎች የሆኑትን (የምርጫው አሸናፊዎች) ይዞ ነበር።

ሆኖም የንጉሡን አስተዳደር የሚቃወሙ ሰዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። በሚስጥር እና በአደባባይ ቅዋሚ የሚያሳዩ ኃይሎች ነበሩ። ንጉሡን፣ ንጉሣዊ ቤተሰቦችን፣ የሃይማኖት መሪዎችንና አንዳንድ ሚኒስትሮችን የሚዘልፉ በራሪ ወረቀቶች ይበተኑ ነበር። ከተቃዋሚው ክፍሎች ውስጥ በድፍረቱና ሆ ብሎ ሰልፍ በመውጣቱ ይበልጥ ተደማጭነት ያገኘው የተማሪው ክፍል በMarch ላይ ት/ሚኒስትሩን እንዲሻሩ፣ የአሜሪካው የሰላም ጓድ (Peace Corps) ከኢትዮጵያ እንዲወጣ የሚሉ ነጥቦችን ያዘሉ ጥያቄዎች አቅርበው ነበር። (ሁለቱም ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በጠየቁት መሰረት ፍፃሜ አግኝተዋል)። የተማሪዎቹ ነገር እየበዛ፣ የራስ ምታት እየሆነ በመሄዱ በመንግስት ትዕዛዝ መሰረት ዩንቨርስቲውና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለጊዜው እንዲዘጉ ተደረገ። ወዲያውኑ ሁለት የሶቭየት ጋዜጠኞችና ሶስት የቼኮዝሎቫኪያ ዲፕሎማቶች ተማሪዎቹን ቀስቅሰዋል በሚል ሰበብ ከኢትዮጵያ ይባረራሉ።

የተማሪዎቹ ተቃውሞ እየበዛ ሲሄድ መንግሥትም ጠንከር ባለ መንገድ አፀፋውን መስጠት ጀመረ። በApril 30 ላይ አራት የዩንቨርስቲ ተማሪዎችና አንድ አስተማሪ "ቀንደኛ በጥባጭ" ተብለው እያንዳንዳቸው ላይ የአምስት አመት እስራት ይፈረድባቸዋል። ግን ከ5 ወር በኋላ (Sept.) በንጉሡ መልካም ፈቃድ ምህረት ተደርጎላቸው ይለቀቃሉ። ይህ 'መልካም ፈቃድ' ተማሪውን ሊያስታግስ አልቻለም። ሰልፉ እየበዛ፣ አውቶቡሶችና መኪናዎች በድንጋይ እያደቀቁ፣ ተማሪና ፖሊስ በየመንገዱ እየተፋለሙ መሄዳቸው የተለምዶ ነገር እየሆነ ሄደ። በተለይ ጥላሁን ግዛው የተባለው የተማሪዎች መሪ መንገድ ላይ ከተገደለ በኋላ ተማሪና መንግሥት ሆድና ጀርባ ሆኑ።

ከአገር ቤት ውጪ ፈረንጅ አገር በትምህርት ገበታ ላይ የነበሩት አራት መቶ ስድሣ ተማሪዎችም የአገር ቤቱን ትግል በመደገፍ በአውሮፓና በአሜሪካ ከተሞች ውስጥ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችን ማጥቃት ጀመሩ። ለምሳሌ በMarch ላይ በዋሺንግተን ዲሲ እና በፓሪስ ከተሞች ያሉት የኤምባሲ ቢሮዎች ለተወሰኑ ጊዜያት በተማሪዎች ቁጥጥር ሥር ሆነው ነበር። ቤልግሬድና ሞስኮ ከተማ ውስጥ የሚገኙት ኤምባሲዎች የተደጋገመ የሰልፍ ኢላማ እንደነበሩና በተለይ የሞስኮ ኤምባሲ ከተማሪዎቹ በደረሰበት ጥቃት ሰፋ ያለ ጥገና አስፈልጎት እንደነበረ ይታወሳል።

በአገር ቤትም ሆነ በውጪው ዓለም የኢትዮጵያን ዝና በማደፍረስ ላይ የሚገኘውን የተማሪ ክፍል እንዴት መግታት ይቻላል? በሚለው ነጥብ ላይ መንግሥት አጥጋቢ መልስ ማግኘት አልተቻለውም ነበር። የመንግሥት ባለሥልጣኖች "እንቅጣቸው" በሚሉና "የባሰ ትዝብት ውስጥ ይጥለናል ከቀጣናቸው" በሚሉ ባለሥልጣኖች መከፋፈል ስላመጡ ሁለቱን ወገን የሚያስተናግደው የንጉሡ መንግሥት አመርቂ የሆነ ምላሽ ማፍለቅ ባለመቻሉ የተቃውሞ ሰልፎች እየበዙ ሄዱ። ይህ ሁሉ ሲሆን የአገሪቱ ጦር ኃይሎች በታዛቢነት ሁኔታዎችን ከመመልከትና አንዳንዴም ንጉሡንም ተማሪዎቹንም ከመተቸት በቀር የፖለቲካው ትግል ውስጥ አፍ አውጥተው የተናገሩት ጉዳይ አልነበረም። ሆኖም ታማኝነታቸው ለንጉሡ መሆኑን የሚጠራጠር ክፍል ነበር ማለት ያስቸግራል።

በMarch ላይ ከአገር ቤትና በውጪ ዓለም ተማሪው ያመጣውን ጣጣ ለመግታት በApril ላይ "የህዝብ ምቾትና ደህንነት የሚያስጠብቅ" ደንብ (Public Safety and Welfare Order) ተደነገገ። አዲሱ ደንብ "የደህንነትና የፖሊስ ኃይሎች ማንም ዜጋ በጥርጣሬ ብቻ ቁጥጥር ስር ማዋል ይችላሉ" የሚል ነበር። ይህ ደንብ ግልጥ የሆነ ተቃውሞ አስነስቶ ነበር። "ህገ መንግሥቱን የሚጥስ ደንብ ነው" "ሰብዓዊ መብቶችን የሚረግጥ ነው" በሚሉ መፈክሮች ላይ የተመሰረተ ተቃውሞ በመጀመሪያ የመጣው አገሪቱ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት የውጪ ዜጎች ነበር። በዚህ ቅዋሜ በተለይ በዩንቨርስቲው ውስጥ የአካዳሚክ ዲን ሆነው ይሰሩ የነበሩ አንድ የውጪ ዜጋ ቀንደኛ እንደነበሩ ይታወሳል።

## አውሮፕላን ጠለፋ

ዳማሥኩሥ ከተማ ውስጥ የከተመው ጀብሀ (ELF) በሬዲዮና በወረቀቶች የሚያካሂዳቸውን ቅስቀሳዎች በሰፊው ቀጥሎበታል። ምንም እንኳን በኤርትራ ገጠር ውስጥ እንቅስቃሴ መካሄዱ ቢታወቅም የሚያካሂደውን ትግል ይበልጥ ታዋቂ ያደረገለት በውጪው ዓለም የሚታወቀውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላኖች በመጥለፍና በመሰባበር ነበር። በMarch ወር ፍራንክፈርት ከተማ ውስጥ፣ በJune ወር ካራቺ ውስጥ ሁለት አውሮፕላኖች አንዱ በAugust ሁለተኛው በSeptember አካባቢ ተጠልፈው ወደ ካርቱምና ወደ ኤደን ተገደው ይበራሉ። ከዚህ ለየት በሚል መንገድ በDecember ወር ሁለት ሰዎች አውሮፕላን ሊጠልፉ ሲሉ በጠባቂ ኃይሎች ጥይት እዛው አውሮፕላን ውስጥ ይገደላሉ። የኢት.መንግሥት ሁለቱ ሰዎች የሢሪያ ዜጎች ናቸው የሚል መግለጫ መስጠቱ የሚታወስ ነው።

አሁን ኤርትራን የሚያስተዳድረው ሻቢያ (EPLF) በዛ ወቅት አልነበረም። በኤርትራ ጉዳይ የሚታወቀው "የእስላሞች ድርጅት ነው" ሲባል የነበረው ጀብሀ ብቻ ነበር። ሆኖም ራሱ ጀብሀም ይህን ያህል ደጋፊዎች የነበረው ድርጅት አልነበረም። በ1969 ላይ የደጋፊዎቹ ቁጥር "አንድ ሺ ይሆናሉ" የሚል ግምት ነበር። በእርግጥ የንጉሡን ሥልጣን መቀናቀን የሚችል ኃይልም አልነበረም። ከዚህ በላይ ብዙ ኤርትራውያን የንጉሡ ደጋፊ ነበሩ ባይባልም ኢትዮጵያዊ ሆነው መኖርን የሚፈልጉ ነበሩ።

ኮሊን ሌጉም በጥራዙ ላይ ያስቀመጠው ይህንኑ የሚጠቁም ነው።

"Moreover, the majority of Christian Eritreans ... appear to have come to see more threet from the Moslems than from the Ethiopian Amharas, with who, they share a common religion, culture and history."

እንደተባለውም የኢትዮጵያ አብዮት ፈንድቶ ህብረተሰቡ ትርምስ ውስጥ ከመግባቱ በፊት የኤርትራው ትግል ይህን ያህል ብዙ ተከታዮችን ማፍራት አልቻለም ነበር። የኤርትራው ችግር/ትግል በቁጥርም ሆነ በስፋት እየጨመረ የሄደው ከንጉሡ በኋላ መሆኑ አይካድም።

በውጪውም ዓለም ኢትዮጵያ ጥሩ ግኑኝነት ነበሯት። ምንም እንኳ አምስት ሰዎችን ከአገር ብታባርርም ቅሉ የኮምኒስቱ ዓለም ጋር የነበረው ግኑኝነት አልሻከረም ነበር። የተማሪዎች ቅዋሜ የሶሻሊስት መርሆዎችን መከተሉ እንዲሁም አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምትሰጠው ዕርዳታ ተደማምረው ያስከተሉት የምን ይለኛል (face saving) አቋም እንደነበረ ሶቭየቶች ገምተው ነበር። ከዛ በኋላ በDecember ወር ላይ ቋሚ የሆነ የሶቭየት የኤግዚቢሽን ህንፃ ንጉሡ መርቀው መክፈታቸው ይታወሳል። ከጎረቤት አገሮች ጋር የነበረውም ግኑኝነት "በጣም ጥሩ" ነበር። መለስተኛ የሆኑ ግጭቶች ይታዩ የነበረው ከሶማሊያ ጋር የሚያዋስኑ ቦታዎች ላይ ሲሆን "ሠላማዊ ጉርብትና" እንዲስፋፋ በማለት የሁለቱ አገር መሪዎች በዛች ዓመት ውስጥ አምስት ጉባዔዎችን ሲያካሂዱ፣ ንጉሡ በበኩላቸው "ከሶማሊያ ወታደሮች ጥቃት እየደረሰብን ነው" እያሉ አቤቱታ ያቀርቡ የነበሩትን የኦጋዴንና የሐረር አገር ሽማግሌዎችን ድሬዳዋ ድረስ እየሄዱ አስጠርተው ያነጋግሩ ነበር። በተደረጉት ጥረቶች ሳቢያ ሁለቱ አገሮች መሃል የነበረው ችግር ወደ ጦርነት አላመራም ነበር።

ከኬንያ ጋር "እጅግ በጣም ጥሩ" ግኑኝነት ሲኖር ከሱዳን ጋር ግን ሁኔታው ልዩ ነበር። "ጀብሀን ትደግፋለች" "የደቡብ ሱዳን ጦረኞችን ትደግፋለች" በሚሉ ክሶች አንዱ አገር ሌላውን ቢወነጅልም ወደ ጦርነት አልሄዱም ነበር።

ከላይ የተጠቀሱትን የውስጥና የ[illegible] ግኑኝነትን በአፍሪቃ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ከ[illegible]ች እየተዘዋወሩ ልዩ ልዩ የዲፕሎማሲና የሽምግልና ሚና ይጫወቱ የነበሩት ንጉሥ ኃ/ስላሴ ከሥራቸው ሆኖ በአማካሪነት፣ በባለሟልነትና በአጋፋሪነት የኢትዮጵያ መንግሥትን ሥራ ያከናውኑ የነበሩት ባለሥልጣኖች፣

| | |
|---|---|
| ንጉሠ ነገሥት | አጼ ኃይለሥላሴ |
| ጠ/ሚር | አክሊሉ ሀብተወልድ |
| ውጪ ጉዳይ | ከተማ ይፍሩ |
| ገንዘብ ሚ/ር | ማሞ ታደሠ |
| ንግድ ኢንዱስትሪ ቱሪዝም | ይልማ ደሬሣ |
| ግብርና | አበበ ረታ |
| ፍርድ ሚ/ር | አካለወርቅ ኃብተ ወልድ |
| ጤና ጥበቃ | ገርማቸው ተክለኃዋርያት |
| አገር ግዛት | ዘውዴ ገ/ህይወት |
| መከላከያ | ከበደ ገብሬ |
| የንጉሥ ችሎት | ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ |
| መሬት ስሪት | አበበ ገብሬ |
| ማዕድን | አማኑኤል አብርሃም |
| ማስታወቂያ | ጌታቸው መካሻ |
| ሥራ ሚ/ር | ሣላ ሒኒት |
| ቴሌኮሙኒኬሽን | እንዳልካቸው መኮንን |
| ትምህርት ሚ/ር | ሰይፉ ማህተመስላሴ |
| የጠ/ሚ ሚኒስቴር | ሥዩም ሀረጎት |
| የፕላኒንግ ኮምሽን | በላይ አባይ |
| ጡረታ ሚ/ር | ታደሠ ያዕቆብ |
| የጦር ኃይሎች አዛዥ | አሠፋ እያና |
| የምድር ጦር አዛዥ | ደበበ ኃ/ማርያም ነበሩ። |

ይህንኑ አይነት ተዋቀር የነበረውና በተጠቀሱት መሪዎች ስር አገሪቱን ያስተዳድር የነበረው ይህ መንግሥት ከአራት ዓመቶች በኋላ የፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮት ባስከተለው ለውጥ ምክንያት ድምጥማጡ ጠፍቷል። ንጉሡ በውጪ በኩል አገሪቷ ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት በዲፕሎማሲና በሽምግልና መከላከል ቢችሉም በቤተመንግሥታቺው ዙሪያና በየከተማው መንገዶች ላይ ይቃወሟቸው የነበሩትን ተማሪዎችን ማስታገስ አልቻለም። ከወሰዷቸው ርምጃዎች ውስጥ አንዱ በመገናኛ ብዙሀን በቀጥታ ተማሪዎቹን ማነጋገርና ወላጆችን ቤተመመንግሥታቸው ውስጥ ሰብስበው ማማከር ነበር። ንጉሡ ተማሪዎቹን ከተማጠኑባቸው ነገሮች ውስጥ በጉልህ የሚታወሰው "ለፖለቲካውማ ስታድጉ ትደርሱበት የለምን?" በማለት በቴሌቭዥን ላይ ያቀረቡት ጥያቄ/ግሰፃ ነው። በእርግጥም "All History is current events" የሚለው አነጋገር ክቡር ነው።

-----------------------------------

ሰይፉ መኩሪያ የአትላንታ ነዋሪ ሲሆን የላንዳፍታ መጽሔት ቋሚ ጸሐፊ ናቸው።

# የውይይት መድረክ

## እነዚህ ልጆች የሚፈልጉት ምንድን ነው?

## "በመስተዋት ቤት ውስጥ የሚኖር በሌሎች ላይ የመጀመሪያውን ድንጋይ ወርዋሪ አይሆንም"

## ክፍል 1


ከመራራ ጉዲና (ረዳት ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣


(ከጦቢያ መጽሔት የተወሰደ)

"የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር አቶ መረራ ጉዲና ... ኅብረ ብሔር በሆኑ አገሮች ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመፍጠር መደረግ ያለበትን አስመልክተው በጉባኤው ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅጣጫ በሰፊው በመቃኘት ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ፣ ብሔራዊ ዕርቅ ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ሥልጣን የያዘው መንግሥት የብሔር – ብሔረሰቦችን ጥያቄ ለራሳቸው ድብቅ ዓላማ ማስፈጸሚያ ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት ችግሮችን በመፍጠር ላይ እንዳለ መግለፃቸው ተዘግቧል።
(ኡርጂ ጋዜጣ በሚችጋን ስለተካሄደው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ በመስከረም 3 ቀን 1987 ዓ.ም ካቀረበው ሪፖርት የተወሰደ)

"በየጊዜው በስልጣን ላይ የሚወጡ የኢትዮጵያ ገዥዎች ዋና ችግራቸውና ድክመታቸው ካለፉት ስህተቶች መማር ተስኗቸው በሕዝቦች ላይ ችግሮች እንዲደጋገሙ ማድረጋቸውና ከዚህም የተነሳ ለውድቀትና ለውርደት መዳረጋቸው እንደሆነ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር የሆኑት አቶ መረራ ጉዲና ከትላንት በስቲያ ከአሜሪካን ድምፅ ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ውስጥ ገለጹ።

"አቶ መረራ በዚህ ቃለ ምልልሳቸው ውስጥ ከ1960ዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ ስለሚነሳውና ዛሬም ምላሽ ስላላገኘው የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ለችግሩ ሶስት ገጽታዎች ሰጥተውታል። እነዚህም ሶስት ገጽታዎች <የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ የኮሚኒዝም ቁምጥና ነው የሚለው የትምክህተኞች አቋም፣ የእስካሁኑ የኢትዮጵያ ታሪክ የወሰደው (የወለደው) ከታሪክ የመነጨ ችግር መሆኑን የሚቀጥል፣ እና የራስን ዕድል መወሰን እስከመገንጠል የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ተንተርሶ "መገንጠል" የሚለውን የመንጃ ፈቃድ አድርጎ መጠቀም ናቸው።> ካሉ በኋላ በራሳቸው አመለካከት ግን ትክክለኛ ገጽታው ይህ የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ከእስካሁኑ የኢትዮጵያ ታሪክ የመነጨ ችግርና እውነታ መሆኑን አስምረውበታል።

"ኢሕአዴግ አዲስ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እገነባለሁ በማለት የሚያደርገው ትግል ተጨናግፎበታል ያሉት አቶ መረራ የኢሕአዴግ ጥረት "በተለይም ከምዕራብ ዓለም መንግሥታት ጋር በማበር ስልጣን ላይ ለመቆየት እየተጠቀመበት ያለ መሣሪያ እንጂ ትክክለኛ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አይደለም" ብለዋል። ከዚሁ ጋር አያይዘው አቶ መራራ ሲናገሩ የኢሕአዴግም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ መንግሥታት መሠረታዊ ድክመታቸው ያሉትን ችግሮች ለሕዝብ አቅርበው በሰላማዊ መንገድ የመፍታት የፖለቲካ ፍላጎት ማጣት ነው ካሉ በኋላ ስለተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ድክመት ደግሞ ሲናገሩ <እነዚህ ኃይሎች በሰላማዊ መንገድ ተደራድረው በሚስማሙባቸው ነጥቦች ላይ ተግባብተው ሊስማሙባቸው ያልቻሉትን ነጥቦች ደግሞ ለሕዝብ ለማቅረብ ጥረት አለማድረጋቸው ነው> ብለዋል። "የፖለቲካ ሳይንሱ ምሁር ኢትዮጵያ ውስጥ ሲነሳ የቆየውን የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ምንም ቢሆን ከዚህ በኋላ የዘር ጥያቄ ገጽታን መላበሱ የማይቀር ነው ካሉ በኋላ ይህ ደግሞ በሩዋንዳና በላይቤሪያ የታየው[illegible]ይነት አስከፊ እልቂት እንደሚያስከትል ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል። ሕዝባችንንና አገሪቱን [illegible]ህ ዓይነት አደጋ ለማዳን መንግሥትና ተቃዋሚ ኃይሎች ድክመቶቻቸውን በማስወገድ ጥያቄው በሰላማዊ መንገድ እንዲመለስ የፖለቲካ ፍላጎት (Political will) እንዲያሳዩ ደጋግመው ጠይቀዋል። የአቶ መራራ ጉዲናን ቃለ ምልልስ ሙሉ ቃል ሰወደፊት አጠናቅረን ለማቅረብ እንሞክራለን።" (ኡርጂ ጋዜጣ "አዲሱ የኢትዮጵያ ፖለቲካና አቅጣጫው" የሚል ርዕስ በመስጠት እኔ ለአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ የሰጠሁትን ቃለ ምልልስ በሚመለከት መስከረም 10 ቀን 1987 ዓ.ም እትሙ ከዘገበው የተወሰደ)

የገጠማቸው ችግር ይህ ነው ለማለት ባልችልም የቃለ-ምልልሴን ሙሉ ቃል ለማቅረብ ለሕዝብ ቃል የገቡት የኡርጂ አዘጋጆች እስከዛሬ አላቀረቡም። ባለፈው ዓመት በሚችጋን ላይ ያቀረብኩት ጥናታዊ ጽሑፍና ተከትሎም የሰጠሁት ቃለ-ምልልስ ብዙ ሰዎችን ትኩረት መሳቡ ያናደዳቸውና ያባሳጫቸው የባህር ማዶ አለቆች አዲስ ትዕዛዝ ሰጥተው ሊሆን ይችላል። እንዲያውም "ኡርጂ" እና "ሰይፋ ነበልባል" በተባሉ የግል ጋዜጦች የተለያዩ ጸሐፊዎች በስድ ንባብና በግጥም፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ስፊ ዘምቻ አድርገውብኛል። በእነዚህ ጋዜጦች ስለተባሉ ጉዳዮች ወደፊት የምለውን እላለሁ።

የሚካሄደው ዘመቻ ግን እኔን ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና የተጫወቱትን የኦሮሞ ልጆች ማለትም ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን፣ ራስ አበበ አረጋይን፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን፣ ጄኔራል ጃጋማ ኬሎን ጨምሮ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተገቢ ቦታ የነበራቸውንም ሁሉ ለማጣጣል የታቀደ ይመስላል። በድርጅቶችም በኩልም መኢሶንና ኢሕአፓን ጨምሮ በኢትዮጵያ ምድር የተፈጠሩትና የታወቁት በሙሉ እየተኮነኑ ናቸው። የውግዘቱ ፀበል ከብዙ ዓመታት በፊት ስለኦሮሞ ከፃፉት አባ ባሕርይ ከሚባሉ መነኩሴ እስከእኔ ድረስ ስለኦሮሞ የፃፉትን ሁሉ ደርሷቸዋል። በተለይ እኔን "የዘመናችን ጎበና ነው" ብለውኛል። አንባቢ ከእኔ ጋር እንዲጠይቅ የምፈልገው እንዲያ በኡርጂ ተደንቆ የተዘገበበት ጥናታዊ ጽሁፌና ቃለ ምልልስ (በስፋት የጠቀስኩት ያለ ምክንያት አይደለም) እጅግ አስገራሚ በሆነ ፍጥነት እንዴት "ዋና የዘመናችን ጎበና" ሊያስብለኝ እንደቻለ ነው። የዚህን እንቆቅልሽ ፍቺ እንደጥላሁን ገሠሠ "ሆድ ይፍጀው" ብዬ ላልፈው አልፈልግም። በዚህም ምክንያት ላለፉት ሩብ ምዕተ ዓመታት በኦሮሞ ልጆች መካከል ታምቆ የኖረውን ምስጢር ለህዝባቸው መብትና ክብር ለሚቆጩ፣ ለዚህም ክቡር ሕይወታቸውን እስከዛሬ ለሚሰዉት የኦሮሞ ልጆችና የሁሉም እኩልነት የተከበረባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ለሚታገሉ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የበኩሌን እፈልጋለሁ።

አንባቢ ግን በቅድሚያ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ እንዲልልኝ እፈልጋለሁ። አንድ የፈረንሳይ ሶሻሊስት ደራሲ "አንድ ነገር ስለወዝአደሩ ጽፌ የወዝአደሩ ጠላቶች ጥሩ ነገር ጽ<u>ፍ</u>ል ብለው ካሞገሱኝ፣ ወዝአደሩን የሚጎዳ ምን ነገር ጽፌ ይሆን? ብዬ እጨነቃለሁ። የወዝ አደሩ ጠላቶች መጥፎ ነገር ጽ<u>ፍ</u>ል ብለው ሲነጫነጩብኝ ያኔ ለወዝአደሩ ጥሩ ነገር መስራቴ ስለሚገባኝ በጣም ደስ ይለኛል" ብሎ ነበር። እኔም ስለሕዝባችን ብሔራዊ ክብርና መብት መከበር፣ የሀገሪቱ መሰረታዊ ችግሮች እንዲፈቱ ስለሰጠኋቸው አስተያየቶች የሚነጫነጩትን እኔም ሆንኩ ብዙ የኦሮሞ ልጆች እነማን እንደሆኑ ስለምናውቅ ብዙ የሚያስጨንቀኝ አይደለም። የሚያሳስበኝ ሌላ ነገር ነው።

ከጫጫታዎቻቸው ጋር የሚተላለፉ፣ የኦሮሞን ሰፊ ህዝብም ሆነ የተቀረውን የኢትዮጵያን ህዝብ መሰረታዊ ጥቅሞች የሚጎዱ በርካታ ጎባጣ ሀሳቦች አሉ።

ስለዚህ <u>አንደኛ</u> በኦሮሞ ሕዝብ ስም የሚንቀሳቀሱና በስሙ ብዙ የሚባልለት የኦሮሞ ሕዝብ የችግሩን ምንጭ እንዲያውቁት፣ ለሕዝብ መብት ሲሉ የሚሞቱና በእስር የሚንገላቱ ሁሉ መስዋዕት የሚከፍሉበትን ጉዳይ በቅጡ እንዲገነዘቡ ነገሮችን በግልጽ ማስቀመጥ መርጫለሁ።

<u>ሁለተኛ</u> የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት መንገዱን በመሳቱ በተከፈተው ቀዳዳ ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች ሥቃይና መከራ መቀበል ብቻ ሳይሆን ደማቸው እንደውሃ የፈሰሰበት ምክንያት አለ። ስለአብዮት በጆሮአቸው እንኳ ያልሰሙ፣ የእዬውን ክብርና ሞገስ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሲጠብቁ የነበሩ ወታደሮች በአንድ ጀንበር ከሁሉም በላይ ሐቀኛ አብዮተኞች ነን ብለው፣ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከወጡት ከመኢሶንና ከኢሕአፓ መካከል ለፍርፋሪና በሞቀበት ለመዝፈን በተሰለፉ ጥቂት ግለሰቦች ድጋፍ በዚህ ትውልድ ላይ አሳዛኝ ቴያትር ተሰርቷል። በዚህ ምክንያት ከዚያ የእልቂትና የጨለማ ዘመን ሕይወታችን የተረፈው ቴያትሩ እንደገና ሲደጋገም ስናይ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ከዚያ እያስላሰልን ይዘገንነናል። ይህ አጠቃላይ የሀገሪቱ የፖለቲካ ድራማ በኦሮሞ ልጆች አካባቢ ትናንት ምን መልክ ነበረው? ዛሬስ ምን መልክ ይዟል? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስ በቅድሚያ ግንዛቤ ብናገኝ ሕዝባዊ ዓላማ ባላቸውና እግር ጥሏቸው ፖለቲካ ውስጥ ገብተው ለራሳቸው ስያሜ በመስጠት በሚንደፋደፉ መካከል ያሉትን ልዩነቶች በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል ይመስለኛል። ከችግሩ መነሻ ልጀምር።

ለኦሮሞ ሕዝብ መብት የሚደረገውን ትግል በተመለከተ ሆዳችን እየቆሰለ እስከዛሬ ድረስ ይከፋፍለናል ብለን እስከዛሬ አምቀን የያዝነው በሽታ የተፈጠረው ሰፊ መሰረት የነበረው የሜጫና ቱለማ እንቅስቃሴ ሲጀመር ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚሲዮን ፀሎት ቤቶች የተፈለፈሉና የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ለርካሽና ወራዳ ዓላማቸው ለማዋል የቆረጡ እንግዴ ልጆች መፈጠር ተከተለ። ይህን ሀሳብ ዘርዘር አድርጌ ላብራራ። የሜጫና ቱለማ መስራች መሪዎች የእነ ኮሎኔል ዓለሙ ቂጢሣና የጄኔራል ታደሰ ብሩ መታሰር፣ የመቶ አለቃ ማሞ መዘምር መገደል የሜጫና ቱለማን እንቅስቃሴ ለጊዜውም ቢሆን እንዲገታ አድርጎ ነበር። ይህ ክስተት የፈጠረላቸውን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም ከሚሲዮን ፀሎት ቤቶች የተመረቁ ጥቂት ሰዎች የኦሮሞ ሕዝብ እንቅስቃሴን ከሃይማኖታቸው እንቅስቃሴ ጋር ያቆራኙታል። ይህ ቁርኝት እንዴት የሕዝባችንን ትግል በቀላሉ በማይወጣበት አጣብቂኝ ውስጥ ከተተው? እንቅስቃሴውን ማን መራው? ለዛሬው አጣብቂኝ እንዴት አስተዋጽኦ አደረገ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል።

ይህን ያልተቀደሰ የሚሲዎን ፀሎት ቤትና የኦሮሞ ሕዝብ የመብት ትግል ቁርኝት የመሩት ባሮ ቱምሣና ቤተሰቦቹ ነበሩ። ይህ ግለሰብ ያኔ በዕውን ያልነበረው የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር መሪ አድርጎ ራሱን በመሰየም የኦሮሞ ሕዝብ መሪ ለመሆን ሲያልም እንደቆየ የኢትዮጵያ አብዮት ፈነዳ። ባልጠበቀበት ጊዜ የአብዮቱ መምጣት የኦሮሞ ሕዝብ መሪ የመሆን ህልሙን ስላጨለመበት የተበሳጨው ባሮ ቱምሳ እስከዛሬ ለትውልድ ተላልፎ ያልተዘጋውን በኦሮሞ ልጆች ደም የመነገድ ምዕራፍ አንድ ከፍቷል። ግልጽ ላድርግ።

አብዮቱ እንደፈነዳ ጄኔራል ታደሰ ብሩ ከታሰሩበት ሐረርጌ ክፍለሀገር ተፈትተው አዲስ አበባ ሲገቡ የውሸት ፍቅር በማሳየት ከተጠጉዋቸው "ተራማጆች" አንዱ ባሮ ቱምሣ ነበር። ይህ ሰው በአንድ በኩል የጄኔራል ታደሰ አስተናጋጅና አማካሪ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ ደርግ ሶሻላዝምን ሲያውጅ፣ ሶሻሊስት በመምሰል ደርግ ውስጥ በነበሩ የኦሮሞ መኮንኖች በኩል የደርግን ሹመት ለማግኘት ደጅ መጥናት ጀመረ። ይህ ለሥልጣን የቋመጠ ግለሰብ ቀን ቀን እንደመሬት አዋጅ ያለትን ለማርቀቅ ከተሰለፉት ጋር እየዋለ ማታ ማታ ደግሞ ጄኔራል ታደሰን "የኦሮሞ ሕዝብና ሠራዊት ተነስቷል፣ የሚመራው ሰው ይፈልጋል። ምኒልክ የኦሮሞን መሬት አከፋፍሏል። እንዴት የምኒልክ ልጆች ዳግመኛ በእኛ ላይ ቆመው መሬታችንን ያከፋፍሉ?" እያለ ጄኔራሉን አላስቆም አላስቀምጥ ይል ጀመር። ዛሬም በሕይወት ያሉ አንዳንድ የኦሮሞ ልጆችን ጨምሮ "ካስፈለገ ዳገት መውጣትና መውረድ፣ ሮጠህ ማምለጥ የምትችለው አንተ ሸፍት፣ ሽማግሌውን ከሚታወጀው የመሬት አዋጅ ጋር አታጋፍጣቸው" ብለው ጄኔራል ታደሰ ብሩን ለማዳን አጥብቀው የተከራከሩ ነበሩ፣ ግን አልተሳካላቸውም።

ዛሬም የሚሲዮንን ኬክ ሲገምጡ ያደጉት ልጆች ሌሎችን እያጋፈጡ መነገድ እንጂ ወደ ጥይቱ መጠጋትን አይሞክሩትም። የእነዚህ አጋንንቶች ዋናው ዓላማ ከነሱ በላይ ስም ያለው የኦሮሞ ልጅ እንዳይኖር ነው። ለዚህም ነበር ያኔ ባሮ ቱምሳ ሽማግሌውን መናገሻ አድርሶ ለራሱ ወደለመደው የቅጥፈት ስራ የተመለሰው። ያለዝግጅት፣ ያለድርጅትና ትጥቅ ቀድሞውኑ የትም መድረስ ስለማይቻልና የጄኔራሉን መውጣት ሆን ተብሎ ከመሬት አዋጅ መውጣት ጋር እንዲገናኝ ስለተደረገ በተዘጋጀላቸው ወጥመድ ውስጥ የገቡት ጄኔራል ታደሰ ብሩና ኮሎኔል ኃይሉ ረጋሣ ስማቸውን ከማላውቀው የአካባቢው ሰዎች ጋር በጥቂት ቀኖች ውስጥ ተይዘው "የመሬት አዋጁን ለማደናቀፍ ለመሬታቸው የሸፈቱ ፈውዳሎች" ተብለው ተረሸኑ።

እዚህ ላይ በተለይም የኦሮሞ ተወላጆች ልብ እንዲያደርጉልኝ የሚፈልገው ነጥብ አለ። እነ ጄኔራል ታደሰ ብሩ ሲረሸኑ መለስ ተክሌ የሚባል በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ የትግራይ ልጅ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትና በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ውስጥ ቦምብ ቀብረሃል ተብሎ የተረሸነ በዚህ ጓዳቸው መሞት የተቆጩት እነ ለገሠ ዜናዊ የወደቀ ጓዳቸውን ስም ወስደውና እነመለስ ዜናዊ ሆነው ወደትግራይ በረሃ ሲንቀሳቀሱ የኦሮሞው ጉድ ባሮ ቱምሣ "እነጄኔራል ታደስ ብሩና ኮሎኔል ኃይሉ ረጋሣ ለመሬታቸው የሞቱ ፈውዳሎች ናቸው" ብሎ በማስወራት ከደርግ ጋር ወግኖ በጄኔራሉ ላይ ሞት ከፈረዱባቸው የኦሮሞ ደርግ አባሎች ጋር ኢጭአት የሚባል ድርጅት መስርቶ ከደርግ የስልጣን ፍርፋሪ ፍለጋውን ሲያጠናክር ነበር። ከርካሽ ዝናና ሥልጣን ሌላ ምንም ዓላማ ያልነበረው ባሮ ቱምሣ የትኛውም ወገን ቢያሸንፍ ስልጣን እንዳይቀርበት አቅዶ "ነፃነት" "በክልቻ ኦሮሞ"፣ "ወራቅሣ" ወዘተ ... የሚሉ ከ6 ያላነሱ ልሳኖችን ማስራጨት ይጀምራል። እነዚህ ልሳኖች የሚያራምዱት አቋም እንደ ሰማይና ምድር የሚራራቅ ነበር። "ነፃነት" የኢጭአት ልሳን ሆኖ ይዞ የሚወጣው ጽሑፍ ደርግን ተራማጅ፣ ሶሻሊስት፣ አብዮተኛ ብሎ የሚያቀርብ ሲሆን "በክልቻ ኦሮሞ" እና "ወራቅሣ" ወዘተ ... ደግሞ ይዘዋቸው የሚወጡት ጽሑፎች ደርግን ፋሽስት፣ የነፍጠኞች ጥርቅም የሚሉ ነበሩ። ግለሰቡም በተራማጅነት ካባ ወደሚያገለግልበት ሕዝብ ድርጅት ሲሄድ የማርክሲስት ስብከት፣ ወንድሙ ወደሚመሩት ፀሎት ቤት ሲሄድ የኦሮሞ ህዝብ አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚል ስብከት፣ ወጣ ብሎ ከኦሮሞ ልጆች ጋር ሲገናኝ ደግሞ ያለገዳ የኦሮሞ ሕዝብ ተስፋ የለውም የሚል ስብከት ነበረው። ከዚህም አልፎ ኢሕአፓም እንዳይነካው የግንኙነት መስመር ፈጥሮ ነበር። የዚህ ሰው የፖለቲካ ቁማር ያልገባቸው የኦሮሞ ልጆች ባልገባቸው ነገር ሕይወታቸውን አጥተዋል። አቶ ጉታ ሰርኔሳ ከባሮ ቱምሣ ጋር ፖለቲካ እየሰሩ በኢሕአፓ ተገድለዋል።

በዚሁ ቁማሩ የገፋው ባሮ በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ የደርግ አባሎችን አቅፎና (ከፍተኛ የደርግ ፀጥታ ሹማምንትን ይጨምራል) ሲንቀሳቀስ መኢሶን ብዙ የኦሮሞ ልጆችን መሳቡ ስላስደነገጠው በመኢሶን ውስጥ ባሉት የኦሮሞ ልጆች ላይ "ከነፍጠኛ ልጆች ጋር የሚሰሩ ቀይ ጎበና ናቸው" የሚል አሉባልታ መንዛት ጀመረ። የዚያ አሉባልታ ውጤት እስከዛሬ እያገረሸ የሚገኘው የመጀመሪያው የኦሮሞ ልጆች አደገኛ ክፍፍል ሆነ። ደርግና መንግሥቱ ኃይለማርያም አደገኛ አዝማሚያ እየያዙ ሲሄዱና በመኢሶን ላይ ቀጥታም ሆነ የእጅ አዙር ዘመቻ ሲከፍት ሕይወቱ በደርግ ውስጥ በተገሰገሱት ትምክህተኞች እስከታልፍ ድረስ የሐረርጌ ክፍለሀገር የሕዝብ ድርጅት ኃላፊ የነበረው ጓድ አብዱላሂ ዮሱፍ ምንም ከማድረግ የማይመለሰው ባሮ ቱምሣ የደርግ መሣሪያ እንዳይሆን ከደርግ ጉያ ለማውጣት ያላደረገው ሙከራ አልነበረም። የኦሮሞ ሕዝብ መሪ ለመባል ባለው ሕልም በተለያየ ስም የሚንቀሳቀሱ ከስድስት ያላነሱ የኦሮሞ ቡድኖችን የምመራው እኔ ብቻ ስለሆንኩ ከእኔው ጋር ብቻ ተደራደሩ ለማለት ሞከረ ከማይታመን ተለዋዋጭ የፖለቲካ ቁማርተኛ ጋር መደራደሩ ፋይዳ ስላልነበረው ሙከራው እዚያው ላይ ቆመ።

መኢሶን ከፖለቲካ መድረኩ ሲወጣ ባሮ ቱምሣ ጮቤ ረገጠ። መኢሶን ሲመታም ከደርግ በስተጀርባ ሆኖ እንደእሱ የተንቀሳቀሰ ሰው አልነበረም። የተከተለው ታክቲክም የመኢሶን አባሎች የሚለቁዋቸውን ቦታዎች በራሱ ካድሬዎች መሙላት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮሞ የሆኑ የመኢሶን አባሎችን መመልመል ነበር። ለምሳሌ በሽግግር መንግሥቱ ም/ቤት አንዱ የኦነግ ተወካይ የነበረው ዓለማየሁ ታረቀኝ ያን ጊዜ በባሮ ቱምሳ ከመኢሶን ከተወሰዱት ካድሬዎች አንዱ ነበር።

የኤርትራ ግንባሮች እንቅስቃሴ፣ የሶማሊያ ጦርነት፣ የኢሕአፓ እንቅስቃሴ፣ የሶማሊያ ጦርነት፣ የኢሕአፓ እንቅስቃሴና የመኢሶን መውጣት ደርግን ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መክተቱን ሲያይ ባሮ ቱምሣ ለኦሮሞ ልጆች እጅግ በጣም አደገኛ የሆኑ ሁለት ቁማሮችን መጫወት ጀመረ። ይህም በአንድ በኩል ደርግ በአጋጣሚ ካሸነፈ ለመታረቅ እንዲችል ይመራ የነበረው ኢጭአት ከደርግ ጋር እንዲቆይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ-ደርግ ኃይሎች ካሸነፉ ከድል አድራጊዎች ጋር ለመሆን ከጃራ አባገዳ ጋር ግኑኝነት የማድረግ ታክቲክ ተከተለ። የኋላ ኋላ ልዩነቱ እየከረረ ሲሄድ ጃራ አባገዳ ወደሚንቀሳቀሱበት ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ፈረጠጠ። ይህ ተዓምረኛ ግለሰብ እዚያ እንደደረሰ ብዙም ሳይቆይ "የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ" እንደሚባለው ስራውን ይጀምራል። ይህም ጃራ አባገዳን-ከሥልጣን ለማውረድ ማሴር ነበር።

የዚህ አስቸጋሪ ሰው ስራ ያላማረው ጃራም ቀደም ብሎ አብሮት የነበረውንና ለረጅም ጊዜ አብሮት ይሰራ የነበረውን ባዶ ደቻሣ የሚባል (የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ የነበረ) የጉለሌ ልጅ "ይህ ሰው እየከፋፈለን ነው - ምከረው" ብሎ ይነግረዋል። ባዶ ደቻሣ ትግል የጀመሩት ለሥልጣን ሳይሆን የኦሮሞን ሕዝብ ለማደራጀት መሆኑን፣ ሰው ቤት መጥቶ በሰው ላይ ማሤር ብልግና መሆኑን፣ ውጤቱም አደገኛ ክፍፍልን መፍጠር ሊሆን እንደሚችል ደጋግሞ ቢነግረውም ባሮ ሤራውን ይገፋበታል። በመካከሉም ሶማሊያ አሸንፎ የሚመለሰው የደርግ ሠራዊት ግፊት ተጨምሮበት ተስፋ አስቆራጭ ውጥረት ይፈጠራል።

ይህን የተገነዘበው ባሮ ቱምሣ አዲስ ልብወለድ ሲያልም ያድርና "ሥልጣን ላይ በነበርኩበት ጊዜ ጫካ ስገባ ትሰጡኛላችሁ ያልኩዋቸው የቻይናና የምሥራቅ ጀርመን መንግሥታት ቃል የገቡልኝን ብዙ ገንዘብና የጦር መሣሪያ መጥቶ ይውሰድ ብለው መልእክት ስለላኩብኝ ይህንኑ ለማምጣት ወደ ውጭ ልሂድ" ይላል። ከማንም በላይ የዚህን ሰው ማንነት በትክክል መረዳት የጀመረው ባዶ ደቻሣ ባሮ ሌላ ድራማ ለመስራት ማቀዱን በመገንዘብ በምንም መንገድ ባሮ ቱምሳ ወደ ውጭ መሄድ የለበትም ይላል። የባሮ ወደ ውጭ መሄድ ለስብሰባ ሲቀርብም "የሚባለው እውነት ከሆነ ሌላ ሰው ተወክሎ ይሄዳል እንጂ ባሮ በምንም ተዓምር ወደ ውጭ መሄድ የለበትም" የሚለውን አቋሙን ያጠናክራል። በዚህ ጥያቄ ላይ የባሮ ግልገሎች እነዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ የፖለቲካ ነፍስ አባታቸውን በመደገፋቸው በጣም የተናደደው ባዶ ደቻሣ ስብሰባ ለቆ ይሄድና መሣሪያ ይዞ በመመለስ "በኦሮሞ ልጆች ደምና እንባ እስካሁን ነግደሃልና ለዘላለም ግን ስትነግድ አትኖርም" ብሎ ባሮን ረሽኖ ራሱንም በመግደል የክብር ሞት ሞቷል።

ከዚህ በኋላ ውጥረቱም ክፍፍሉም በከፋበት ጊዜ ወደ ጅቡቲ የተጓዘው ዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ አንድም የፖለቲካ ነፍስ አባቱ በኦሮሞ ልጅ እጅ ትክክለኛ ፍርድ መቀበሉና ርካሽ ሞት መሞቱ ታሪኩን ስለሚያበላሽና በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብ የተሻለ እድል ከገጠመው እነጃራ አባ ገዳ የበላይነት እንዳያገኙ ልክ ባሮ ሲያደርግ እንደነበረው ልብወለድ አሉባልታ ማሰራጨት ይጀምራል። "ባሮን የገደለው ጃራ ነው። እስላሞቹ ሁላችንንም ሊጨርሱን ነበር። እኔም አምልጬ ነው የመጣሁት" ብሎ በአንድ ፀሎት ቤት ላደጉትና ከኢትዮጵያ መንግሥት የዜና ማሰራጫ አውታሮች የተሻለ ወሬ የማሰራጨት ችሎታ ላላቸው ዘመዶቹ ይነግራል። እነሱም ከጅቡቲ እስከ ሱዳን፣ ከሱዳን እስከ አውሮፓና አሜሪካ፣ ከዚያም ወደ ሀገር ቤት ይህንኑ ነጭ ውሸት አውርተው ያስወራሉ። የመጨረሻ ውጤቱም የኦሮሞ ተወላጆች ጃራ በሚመራው "እስላሚክ ኦሮሚያ ነፃ አውጭ ግንባር" እና እነዮሐንስ(ሌንጮ) ለታ በሚመሩት "የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር" ተከለከሉ። በዚህ ምክንያት እስካሁን የኦሮሞ ልጆች ደም እየፈሰሰ መሆኑ ብቻም ሳይሆን ለነገም የሚተርፍና የሃይማኖትም መልክ ሊይዝ የሚችል የኦሮሞ ልጆች ሁለተኛው አደገኛ ክፍፍል የተፈጠረው የኦሮሞ አዛውንቶች በተደጋጋሚ እነጃራንና ኦነግን ለማስታረቅ ሞክረው ያልተሳካላቸውም ጃራ "እነዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ በኦሮሞ ሕዝብ ፊት ወጥተው ዋሽተናል ብለው ካላመኑ እነሱን አምኜ ከእነሱ ጋር አልሰራም" በማለቱ ነበር።

ይህን ሁሉ ያወራሁት ሙት ወቃሽ ለመሆን ፈልጌ አይደለም። ይሁንና በራሱ አምሳል ኮትኩቶ በየሚሲዮን ፀሎት ቤቶች ያሳዳጋቸው ዮሐንሶች ኦነግን በቤተሰብ የጥቅም ሰንሰለት ውስጥ አስገብተው አፍነው በመያዝ ሰዎች በተለይም የኦሮሞ ልጆች የሚታገሉትን፣ የሚሞቱለትን፣ በእስር የሚንገላቱበትን ዓላማ በቅጡ እንዲገነዘቡ ባለኝ ፍላጎት ነው። ትናንት የጀመሩትን የፖለቲካ ቁማር በስፋት በመቀጠል የኦሮሞ ልጆች በማይታረቁበት ቅራኔ ውስጥ ዘላለም እንዲዳክሩና ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በጋራ ለሕዝባቸው እንዳይታገሉ በማድረግ ላይ በመሆናቸው ነው። ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉም መኢሶን ከነበሩ ልጆች አልፎ እነ ጃራን፣ ከነጃራ አልፎ እነ ጄኔራል ዋቆ ጉቱን፣ ከእሳቸውም አልፎ አዲስና የተሻለ ድርጅት እንዳይፈጠር ውስጣችንን ያውቁብናል የሚሏቸውን የኦሮሞ ወጣት ምሁራን ሁሉ ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት በሞተ ጎበና ስም እየኮነኑ የደራ የፖለቲካ ንግዳቸውን ቀጥለዋል።

በተለይ የኦሮሞ ልጆች የችግሮችን ምንጭ ከመሰረቱ እንዲረዱ አይፈልጉም። ይህ የፖለቲካ ንግድ እንዴት እንደነበረና አሁንስ በምን ላይ እንዳለ ስለእኔ ብዙዎች ብዙ ብለዋል። ትችቶቻቸው እኔ ከፃፍኩዋቸው ቁም ነገሮች ጋር ግኑኝነት የሌላቸው የአሉባልታ ክምር በመሆናቸው መልክ ያለው መልስ ለመስጠት ይቸግረኛል። ለማንኛውም ለጊዜው የአንደኛውን ግለሰብ ጽሁፍ በተመለከተ የምለው አለኝ።

በጦቢያ መጽሔት ቅጽ 4 ቁ. 3 የወጣውን የዶ/ር መክብብ ገበየሁን ጽሑፍ አንብቤ እንደጨረስኩ እንዲህ ዓይነቱን የስም ማጥፋት የሚጽፉ ከየት የመጡ መሆናቸውን ለማጥናት ሞከርኩ። ስለእሳቸው ጠይቄ ትዝታዎች ተቀሰቀሱብኝ። ይህች ጉደኛ አገር ብዙ ጉደኛ ልጆችን ስለምታፈራ ትናንት ለጊዜያዊ ጥቅም ብለው የፖለቲካ አቋማቸውን እንደየጊዜው ሁኔታ እየለዋወጡ ብዙ ያተረፉ፣ ለማትረፍም ሲሉ ብዙ የኢትዮጵያን ልጆች ያጠፉና በማጥፋት ላይ ያሉ ትዝ አሉኝ። ከጊዜው ጥቅም አንፃር ዘራቸውን የሚለዋውጡ፣ የጊዜው ሁኔታ ከሚፈልገው አንፃር የአባታቸውን ደብቀው የእናታቸውን፣ የእናታቸውን ደብቀው የአባታቸውን መስመር እየተከተሉ የሚያወናብዱት ታወሱኝ። ቀን ቀን በአደባባይ እንዴት ከአማራ ጋር በአንድ ሀገር ውስጥ እንኖራለን እያሉ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉ፣ ማታ ማታ ደግሞ ከአማራ ሚስቶቻቸው ጋር "ተጋብተን ተዋልደን፣ አብረን በልተን፣ ጠጥተን" እያሉ የሚወሸክቱ እየተፈለፈሉ መሄዳቸው ሳስብ የዚች አገር መከራ ገና መሆኑ ታየኝ። የዶ/ር መክብብን ጽሁፍ በቅን ልቦና ላየው እውነትም ስለ ኦሮሞ ሕዝብ መብት የሚናገር ሊመስል ይችላል። እሳቸውን የሚያውቅ ግን ከላይ ያልኩትን ትያትር ለመደጋገምና ጽሁፋቸውም ንስሐ ገብተው ወደ አዲስ ዓለም ለመግባት፣ በአዲሱ ዓለምም ታማኝነት ለማግኘት የተፃፈ ሰፊ ማመልከቻ መሆኑን ለመረዳት አያስቸግረኝም። ነገሩን የበለጠ ግልጽ ላድርገው። ዶ/ር መክብብ ደረጃው ወደታች የነበረ ቢሆንም የመኢሶን ተከታይ የነበሩ ሰው ናቸው። ዛሬ እሳቸው የኦነግ ሐቀኛ ታጋይ ለመሆን ኢድኅቅን በተለይ መኢሶንን ለአማራ መብት ማስከበር የቆሙ ትምክተኛ ድርጅቶች አድርገው አቅርበዋል። ጅብ በማይታወቅበት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል የሚለውን አባባል ዶ/ር መክብብ ረስተው ከሚኖሩበት ስዊድን ሀገር ከኦሮሞዎች የበለጠ ኦሮሞ መስለው በመቅረብ፣ ከራስ ጎበና ቀጥለው ወለጋን ለማስገበር ከሄዱት ከራስ ደምሰው ጋር የሄደውን የፊታውራሪ ዘለቀን የልጅ ልጅ እንደማናውቅ ሁሉ የኦሮሞ አርበኛ ሆነው ቀርበዋል። አንዳንድ ሰዎች አማራ እናቶቻቸውን ወይም ሚስቶቻቸውን እቤት ደብቀው በአደባባይ ግን ከሁሉም በላይ የኦሮሞ ሕዝብ ተቆርቋሪ ነን ሲሉ እያየን ስንታዘብ እንደቆየን ሁሉ ዛሬ ደግሞ የአማራው ፊታውራሪዊ የልጅ ልጅ ራሳቸውን በኦሮሞ ሐቀኛ ታጋይነት አስለፈው እኔን የኦሮሞን ሕዝብ ከዳ ብለው ይኮንኑኛል። ክሱ እርባና የሌለው ቢሆንም አንባቢ የተሻለ እንዲረዳ የስዊድኑ የኦሮሞ "አርበኛ" ያነሷቸውን አንዳንድ ነጥቦች እንመልከት።

የብሔር ጥያቄን በተመለከተ የነበሩትን አመለካከቶች አታውቃቸውም፣ የፃፍከው ልብወለድ ነው ብለውኛል። ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ታሪክ ከሁለታችንም የተሻለ የሚያውቁ በሕይወት ስላሉ ስለበሩት አመለካከቶች የታዘቡ ካሉ አስተያየት ሊሰጡበት ይችላሉ። በእርግጠኝነት ለመናገር እምፈልገው ግን ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ልብወለድም ሆነ እውነተኛ ታሪክ ለመፃፍ እኔ ከዶክተሩ የተሻለ ተሳትፎ ያለኝ መሆኑን ነው።

ዶ/ር መክብብ በተማሪዎች ንቅናቄ በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ ውይይቱ የነበረው በኦሮሞ ምሁራን መካከል ሳይሆን "በሐበሻና በኦሮሞ ምሁራን" ነበር ብለዋል። ይህኛው ነጥብ ዶክተሩ ለተማሪው ንቅናቄ በእርግጥም እንግዳ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። እኔ በጽሁፌ ነጥቡን ያነሳሁት በኦሮሞ ልጆች መካከል የነበረውን አመለካከት ለማሳየት ነበር። እሳቸው ለማየት የሞከሩበት በአጠቃላይ መልኩ ከሆነ ግን ሁለት ነጥቦችን እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ።

**አንደኛው፡-** በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ ውይይቱ የተካሄደው በሐበሻና በኦሮሞ ምሁራን መካከል ያልነበረ መሆኑን፣

**ሁለተኛው፡-** በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የተሳተፉት የኦሮሞ ተወላጆች በየትኛውም ሚዛን አብዛኛዎቹ መኢሶን ውስጥ የነበሩ እንጅ በዛሬው ኦነግ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ እንዳልነበሩ ነው።

ዶ/ር መክብብ ስለጥቅስ ሕጎች እንደማላውቅ ነግረውኛል። እሳቸው ጥቅስ በብዛት በሚጠቀሙበት በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት በመማራቸው ስለጥቅሶች ከእኔ የተሻለ ዕውቀት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል። እንዳይዘነጋብኝ የምፈልገው ግን ያኔ እርሳቸው ሊገቡበት ያልቻሉት የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ የነበርኩና ዛሬም አስተማሪ መሆኔን ነው። በራሺያው ትምህርት ቤት ወይም አሁን ዶክተሩ በሚገኙበት ስቶክሆልም ዩንቨርስቲ ሚዛን ካልሆነ በስተቀር "የጥቅስ ህጎችን ያልተከተለው" ጽሁፌ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ መስፈርት በጥናታዊ ጽሁፍነት አልፎ የቀረበ ነው። ዶክተር መክብብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወደ ብሔረሰቡ ወርዶ መደራጀት አለበት ይሉናል። ሰዎች በፈለጉት መንገድና ባመኑበት ዓላማ ዙሪያ ቢደራጁ ተቃውሞ የለኝም። ዲሞክራሲያዊ መብታቸውም ነው። መጀመሪያ እንዳልኩት በዚህ አገር አንዱ ትልቁ ችግር የፖለቲካ ዘፈናቸውን ዳንኪራው ወደደመቀበት የሚዘፍኑ እየበዙ መምጣታቸው ነው። ዶ/ር መክብብ በመሰረቱ ለኦነግ ያላቸውን ታማኝነት ለመግለጥ ትናንት የነበሩበትን ድርጅት መኮነን አልነበረባቸውም። ሳይሳደቡ የኦነግ ተከታይ እንዳይሆኑ የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም። በአዲስ አለቆች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት በቀድሞ ጓዶች ላይ የሐሰት ወሬ መንዛት ከእኚህ "ትልቅ ምሁር" አልጠበቅም።ነገ ደግሞ ሌላ ቦታ ዘፈን ደምቆ ወደዚያ መሄድ ሲፈለግ ሌላ ትዝብት ውስጥ

ከመውደቅ ከወዲሁ መጠንቀቅ ይሻላል። ፖለቲካውም የሺዎች ብቻ ሳይሆን የሚሊዮኖች ሕይወትን የሚመለከት ትልቅ ቁም ነገር ስለሆነ ከአዲስ ሙዚቃ ጋር ዳንኪራ እንደመርገጥ ቀላል አይደለም።

የከተሞችን የስም ለውጥ በተመለከተ የአማርኛ ስሞቻቸውን በቅድሚያ ጽፈሃል ተብዬ ተወቅሻለሁ። እኔ ያልኩት ለዶክተሩ የገባቸው አይመስለኝም። "የኦሮሞ ልጅ" በመሆናቸው አማርኛው እንዳልገባቸው ለመምሰል ካልፈለጉ በቀር እኔ በእንግሊዝኛው ጽሑፌ የተጠቀምኩበት ሐረግ Reoromaising the names የሚል ስለነበር በአግባቡ ያስቀምጥኩ ይመስለኛል። ስለከተሞች ስያሜ ያነሳሁትም የችግሩን ውስብስብነት ለማሳየት ነው። እኔ በእናቴም፣ በአባቴም በአያቶቼም ኦሮሞ ስለሆንኩ Identity names የሚል ስለነበር በአግባቡ ያስቀመጥኩ ይመስለኛል። ስለከተሞች ስያሜ ያነሳሁትም የችግሩን ውስብስብነት ለማሳየት ነው። እኔ በእናቴም፣ በአባቴም በአያቶቼም ኦሮሞ ስለሆንኩ Identity crisis የለብኝም። ያለጭንቀት መልእክቴን ለማስተላለፍ ሞከርኩ እንጂ ፀጉር ስንጠቃ ውስጥም አልገባሁም።

በኢትዮጵያ አዲስ መንግሥታት ለመፍጠር የሚከለሉ ወሰኖችንና በየክልሎቹ የሚኖሩ የሌሎች ብሔረሰብ ሰዎችን በተመለከተ "ከጎረቤቶቻችን ጋር እንደራደራለን። የሌሎች ብሔረሰብ ሰዎችም የፈለጉት ይቆያሉ ያልፈለጉት ደግሞ ወደፈለጉት ይሄዳሉ" ይላሉ ዶ/ር መክብብ። ሀገር አፍርሶ በነፃ መሄድ ካለ ዶክተሩ ወደአባታቸው ሀገር ለመሄድ የሚችሉ ስለመሆናቸው ወይም በእናታቸው አገር (በኦሮሞ ክልል) ሀገር ስለመቆየታቸው ምርጫ ችግሩ ሲመጣ የምንነጋርበት ይመስለኛል። በኢትዮጵያ ዓይነቱ ሁኔታ ከእንግዲህ ወሰኖች እንዴት በነፃ መንግሥታት ሊከለሉ እንደሚችሉ የሰጡት አስተያየት ግን ወይ የፖለቲካ የዋህ የሆነ ሰው የሚሰጠው፣ ወይም የፖለቲካ ሀሁ ሳይገባው ሰዎች ለተለያየ ዓላማ የሚጽፉትን ሰምቶ የሚጽፍ ሰው የሚያስተጋባው ጨቅላ ሀሳብ ነው። ሌላው ቢቀር እዚያው በቅርባቸው ያለችውና በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የነበረችው ዩጎዝላቪያ እንዴት እንደተከለለች አያውቁም? ወይስ የሰነዘሩትን ሀሳብ እንደ ከባድ ነገር አላዩትም?

የብሔራዊ እርቅን አስፈላጊነት በተመለከተ "አንተም ተው፣ አንተም ተው" መባል የለበትም ብለውናል። ዶክተሩ ብሔራዊ እርቅን አቃለው ያዩት ይመስለኛል። ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም የህዝብ ደም በከንቱ እንዳይፈስ ከስልጣን ወርደው ብሔራዊ ዕርቅ ይፈጠር ብለው ለጠየቋቸው የዩንቨርስቲ ምሁራን "ፖለቲካ አንተም ተው፣ አንቺም ተው የሚባልበት የባልና የሚስት ጥል አይደለም" ብለው የሰጡት መልስ ትዝ አለኝ። መንግሥቱ የዚምባብዌ ዝግጅታቸውን ጨርሰው ሲያፈዙ እንደነበረ ሁሉ የስዊድኑ ጀግናም ኑሯቸውን ከውጭ አገር አመቻችተው የ"የይዋጣልን" ፖለቲካ ይሰብካሉ።

ዶ/ር መክብብ የኦሮሞ ልጆች እየተገደሉ፣ እየታሰሩ፣ እየተሰደዱ ነው ብለዋል። ለሕዝባቸው መብትና ክብር ሰማዕታት ለሚሆኑት የኦሮሞ ልጆች ትልቅ አክብሮት አለኝ። አንድን ለመብቱ የሚታገል ሕዝብ በማሰርና በመግደል የሚገኝ መፍትሔ እንደሌለ አምናለሁ። እነዚህ የሚገደሉ፣ የሚታሰሩና የሚሳደዱ የኦሮሞ ልጆች መስዋዕትነቱን የሚከፍሉት እትብታቸው በተቀበረበት መሬት ላይ ነው። እንዳይረሳብኝ የምፈልገው ነጥብ ግን የተሰደደ ሁሉ ለሕዝብ መብት አለመሆኑን ነው። ማን ክቡር ሕይወቱን እየሰዋና ማን በሚፈሰው የሕዝባችን ደም በአውሮፓ፣ በካናዳና በአሜሪካ ከተሞች እየነገደ፣ የፈረንጅ ፍርፋሪ እየለቀመ የተምነሸነሸ ኑሮ እንደሚኖር ወደፊት ታሪክ ያወጣዋል።

ሶቭየት ኅብረት ለኢትዮጵያ መንግሥት ረድታ ነበር የሚል ክስም ሰንዝረዋል። የቀድሞውን ሶቭየት ሀብረት ቢከሱ የሚያምርባቸው ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች አሉ። እርሳቸውን አብልታና አስተምራ ከምሁር ተራ ያሰለፈችውን ሶቭየት ሕብረትን መክሰስ የበሉበትን ወጪት ሰባሪነት ይመስለኛል።

ዶ/ር መክብብ በኢትዮጵያ ካሉት ብሔር/ብሔረሰቦች የሶስቱ ትልልቅ ብሔረሰቦች ኤሊቶች ጉዳይ ሲነሳ የኦሮሞ ኤሊቶችም እኩል ከሰሃል ብለው ይወነጅሉኛል። ጽሑፌን በጤናማ አእምሮ ያነበበ ሰው እንደሚገነዘበው ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉት ችግሮች የኢትዮጵያ ኤሊቶች አስተዋጽኦ ባደረጉበት መጠን ለማስቀመጥ ሞክሬአለሁ። የሚዛናዊ አስተሳሰብ ትልቁ መለኪያ ክስተቶችን በተገቢ ሚዛን መለካት መቻል ነው። በእኔ እምነት ኢትዮጵያ እጥረት ያለባት የእንዲህ ዓይነት ምሁራን ነው። እኔ አቅሜ የፈቀደውን ያህል ሁሉንም በሚዛናዊነት ለማየት የሞከርኩ ይመስለኛል።

በጽሁፌ ለሀገሪቷ ችግር መፍትሔ የሚሆን ቁም ነገር እንዳላነሳሁ ተነግሮኛል። በበኩሌ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ላለፉት 150 ዓመታት በአጭሩ በመዳሰስ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንዴት እንደተፈጠረች፣ ከአፈጣጠርዋ ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን፣ በእነዚህም ችግሮች ሳቢያ የደረሰውን ጥፋትና ዛሬ የገባንበትን የፖለቲካ አጣብቂኝ ሀገሪቱና ሕዝቧ እንዴት ሊወጡ እንደሚችሉ የመፍትሔ ሀሳቦችን ለማቅረብ ሞክሬአለሁ። ስለጉዳዩ ተመሳሳይም ሆነ የተለየ አስተሳሰብ ካላቸው የኦሮሞም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ምሁራን ጋር ስወያይበት ነበር። የቀረቡትን መፍትሔዎች አላምንባቸውም ማለት የጨዋ ምሁር ስራ ነው። ዶ/ር መክብብ ለማስቀመጥ በሞከሩበት መንገድ ማስቀመጥ ግን ከጭፍን ጥላቻ የመነጨ ተራ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው።

ዶክተሩ በሚችጋኑ የጥናት ጉባኤ ከመረራ እጥፍ የሚበልጡ የጥናት ጽሁፎች ቀርበዋል ብለዋል። እኔ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና ከመላው ዓለም የመጡ ምሁራን በተሳተፉበት ስብሰባ፣ "ያቀረብኩት ወረቀት ከሁሉም ስለበለጠና አንደኛ ስለወጣ ነው የሰዎችን ትኩረት የሳበው" የሚል

የግብዞች አቋም የለኝም። በሚችጋኑ ስብሰባ እኔም ሆንኩ ሌሎች ያደረጉትን አስተዋጽኦ በተመለከተ ግን በቦታው የነበሩ ቢናገሩ ይሻላል። የኦሮሞን ሕዝብ ታሪክ በሚመለከት የደቡቡን ኦሮሞ ትቼ ወደ ሰሜኑ እንዳዘነበልኩ ተወስዶብኛል። በእኔ እምነት የአንድ ሕዝብ ታሪክ እንደ ቡፌ ግብዣ የፈለጉትን የሚተውት አይደለም። ከሰሜን እስከደቡብ የኦሮሞን ሕዝብ ዕውነታዎች ለማሳየት ሞክሬአለሁ። ይህን በማድረጌ የሰራሁት ስህተት ለእኔ አልታየኝም። ያም ሆነ ይህ በኦሮሞ ሰፊ ሕዝብ ደምና እንባ ካላገደው መረራ ይልቅ ከአቅኝዎች አንዱ የነበሩት የፊታውራሪ ዘለቀ የልጅ ልጅ ለኦሮሞ ሕዝብ መብት ለመሞት የተዘጋጀ የነፃነት ታጋይ የሚሆንበት ምክንያት አይታየኝም። ከሆነም ተግባሩ በሂደት የሚታይ ነው።

ዶ/ር መክብብ ከኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄም ሆነ ከኢትዮጵያ ህዝብ ግኑኝነት የሌላቸው ነገሮች ሲነግሩን ቆይተው ለኢትዮጵያ አንድነት ፍቅር አለኝ ይላሉ። ጽሁፋቸው የሀገርና የሕዝብ ፍቅር ያለውና ሊኖረውም የሚችል ሰው ጽሁፍ ይሁን አይሁን ፍርዱን ለአንባቢ ለመተው እፈልጋለሁ። ለኦሮሞ ሕዝብ አለኝ ስለሚሉት እንግዳ ፍቅር ግን አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ። ዶ/ር መክብብ በጣም ስለሚያፈቅሩት "የኦሮሞ ሕዝብ በባርነት እንዲኖር አልፈልግም" ይላሉ። መቼም የሀሳብ ተቃውሞ ቢሆን ሰው የሚመስለውን ቢጽፍ መልክ ይኖረዋል። እኔ ለምንና እንዴት የፊታውራሪ ዘለቀ ልጅ መክብብ ገበየሁ የኦሮሞ ሕዝብ የነፃነት ታጋይ፣ መረራ ጉዲና ደግሞ ለኦሮሞ ሕዝብ ባርነት የሚታገል ሊሆን እንደሚችል ጨርሶ አይገባኝም። እንዲህ ዓይነቱ እንቆቅልሽ ከ"ጳጳሱ ቄሱ" ዓይነት ነው።

የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ረዳት ፕሮፌሰርና የፖለቲካል ሳይንሱ ዲፓርትሜንት ሊቀመንበር በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዋዜማ ላይ በንቃት ጉድለት ከአብራኩ የወጣው ሕዝብ ባሪያ እንዲሆን ካለ፣ በእርግጥም የኦሮሞ ሕዝብና አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብም ትልቅ አደጋ ላይ ነው ማለት ነው። ስለዚህ የዶ/ር መክብብ ዓይነት ልዩ ችሎታ ያላቸው ምሁራን በብዛት ያስፈልጋሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ምሁራን ከፈረንጅ አገር የሚጽፉት ጽሁፍም ጨርሶ ስለማይበቃ፣ በባሌም ሆነ በቦሌ ዘምተው ለኦሮሞ ቢደርሱለት የነፃነቱን ቀን የሚያፋጥኑ ይመስለኛል። ዶክተሩ በመጨረሻ አንድ ጥያቄ ጠይቀውኛል። በተወሰነም ደረጃ ቢሆን ከጽሁፋቸው ውስጥ ቁምነገር ያለው ይኸው ጥያቄ ነው። መልሴም ግልጽ ነው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ መሰራታዊውና መመለስ ያለበት የፖለቲካ ጥያቄ "የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ መኖር ይችላል ወይስ አይችልም?" የሚለው ነው። የእኔ ግልፅ አቋም "አብሮ መኖር ይችላል፣ መኖሩም ይመረጣል" የሚለው ነው። "አብሮ መኖር የሚችለውም እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን በመመስረት የሁሉም ኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ መብትና ክብር ሲጠበቅ ነው" የሚለውን አስምሬበት ነው። ከእርሳቸው የሚጠበቀው ስራ ለዚሁ ለተቀደሰ ተግባር አስተዋጽኦ ማድረግ ነው ብዬ አምናለሁ።

ለኦሮሞ ሕዝብ "ነፃነት" እንታገላለን የሚሉ ከእነሱ የተለየ ሀሳብ ሲነሳ ጧትና ማታ ሳይከሰሱ ተከሰስን፣ ሳይሳደቡ ተሰደብን የሚሉ ጫጫታ አብዝተዋል። ከላይ እንደገለጽኩት ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄና አገራችን አሁን ስላለችበት ሁኔታ አቋሜን መግለጽ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በስድ ንባብና በግጥም፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ይጽፋሉ። እንደሚመስለኝ ዓላማቸው ተሰሚነት (attention) ፍለጋ ነው። ለዚህ ነው ራስን ሰድቦ ሰድቡን ማለት፣ ራስን ከሶ ተከሰስን ማለትና ፈረንጆቹ እንደሚሉት shadow boxing ዓይነት ነው። ዋና የትግል ስልት መሆኑ ነው።

ዶ/ር መክብብ እኔን እንደጠየቁኝ ሁሉ እርሳቸውና አለቆቻቸው እንዲመልሱት የምፈልገው ጥያቄ አለ። አቶ አሰፋ ጫቦ የሚባሉ ሰው አሜሪካን አገር አግኝቻቸው ጠይቀውኝ መመለስ ያልቻልኩት ጥያቄ ነውና ለእኔም ለእሳቸውም መልሱ ይጠቅመናል። አቶ አሰፋ ጫቦ የጠየቁኝ ጥያቄ "እኔ ብዙ ዓመት ፖለቲካ አብሬያቸው ሰርቻለሁ። ለአስር ዓመታትም አብሬ ታስሬአለሁ። የእነዮሐንስ (ሌንጮ) ቡድን እስከዛሬ በትክክል ምን እንደሚፈልግ ስለማላውቅ አንተ ካወቅክ ንገረኝ" ነበር ያሉኝ። እኔም የጥያቄውን መልስ ስለማላውቅ መልስ አልሰጠኋቸውም።

እኔ የዛሬ 23 ዓመት አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ከገባሁ ጊዜ ጀምሮ በፖለቲካ ዓለምም ጭምር እነዚህን ሰዎች አውቃቸዋለሁ። ትንሽ ትርፍ የሚገኝ መስሎ ከታያቻው ጥንብ እንዳገኘ ጅብ እያስካኩ ተጠራርተው ሲሮጡ ከማይ በቀር የፖለቲካ አቋማቸው ምን እንደሆነ አላውቅም። እኔ ብቻም አይደለሁም። ብዙ የኦሮሞ ልጆችም የሌንጮ ለታ ቡድን ምን እንደሚፈልግ ሳያውቁ አልቀዋል። ምናልባት ችግራችን ወደነሱ ፀሎት ቤቶች አብረን ስለማንሄድና እውነተኛውን ነገር የሚናገሩት እዚያ መድረክ ላይ ሊሆን ስለሚችል የፖለቲካ ዓላማቸው ምን እንደሆነ፣ በትክክል ምን እንደሚፈልጉና ለኦሮሞ ሕዝብ ምን እንደሚመኙ እንዲነግሩን እንፈልጋለን። ከእንግዲሁ በተድበሰበሰ አቋምና ባለፈ ታሪክ እያሳዘኑ፣ በሕዝብ መካከል የጥላቻ መርዝ እየረጩ፣ የሕዝብ ልጆችን ለመስዋዕትነት የማቅረብ ቴያትር መጋረጃ መዘጋት አለበት።

(ሌሎችን ጉዳዮች በተመለከተ በክፍል 2 እንገናኝ)

## ውድ አንባብያን

ብዙ አንባብያን በስልክና በቃል በጠየቁን መሠረት ይህንን የረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲናን ጽሑፍ የጦቢያ መጽሔትን ላላገኛችሁት በማሰብ አውጥተነዋል።ክፍል ሁለትን በሚቀጥለው እትም እናቀርባለን። በዚሁ አጋጣሚ የጦቢያ መጽሔት ይህን የመሳሰሉ በሳል ሥራዎችን በማውጣት ለምታደርገው ጥረት ከፍተኛ አድናቆታችንን እንገልጻለን።

# አዳም ና ሔዋን

አዳምና ሄዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መካል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ነው። የገጠሙኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ። በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችንም እያቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተያየታችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠሙኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## ዕጣዬ

### ከአብርኸት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብርኸት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነው ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

### ክፍል 12

ከየትም ይምጣ ከየት ለኃይለ አሜሪካን አገር ቀደም ብሎ መምጣት ትልቅ ነገር ነበር ሆኖ የሚታየው። እናም ከእሱ በኋላ መምጣቴ ብዙ ነገር በተለይም የከተማን ነገር እንደማላውቅ አድርጎ ነው የሚወስደው። አዲስ አበባን፣ አስመራን እንኳን ሳያይ ነው ከመንደፈራ ጫካ ገብቶ በሱዳን በኩል ወጥቶ አሜሪካን የመጣው። እና ሰው ሁሉ እንደእሱ ይመስለዋል። እና በቃ ምንም የማላውቅ ጥሬ አድርጎ ነበር የሚያየኝ። የሚገርማችሁ አስመራ ወይም ሌሎች የኤርትራ ከተሞች ተወልደው ያደጉ ከመሐል አገር ያሉትን ወይም የሚመጡትን መናቅ፣ ባላገር አድርጎ መቁጠር የተለመደ ነበር። በተለይም የትግራይ ልጆችንማ ሲንቁ ሌላ ነው። አንዳንዶቹ በጣልያን ስር ተገዝቶ መቆየቱ የሥልጣኔ ቁንጮ ያደረጋቸው ይመስል ጉራቸው አይጣል ነው። እንደጣልያኖቹ ለመሆን ይከጃጀላቸዋል። እና ተከስተም ከመሐል አገር በመጡ ሰዎች ላይ ትልቅ ንቀት እንዳለው ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። እንግዲህ ኃይለ እኔን ለመቅረብ ብሎም ለማውጣት መፈለጉን ብረዳም እኔ ደግሞ ያለመፈለጌን እንዲያውቅልኝ ብዙ ምልክቶች ባሳየው አልገባውም። ሲኒማ ወይም ፓርቲ ልጋብዝሽ ሲለኝ አልችልም ማለቴ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አንዳንድ ወሬዎችን ሲያነሳ አርዕስት ስቀይርበት አልገባው አለ። ፍርጥ አድርጌ አለመፈለጌን ብነግረው ደግሞ ጠብ ያለሽ በዳቦ እንደሚል ከሁኔታው ተረዳሁ። ዝም ብሎ መዝጋቱም፣ ካልሆነም በአራዳነት እሺ የምል መስዬ እንዳልሸውደው እኔ በምሰራበት አካባቢ ትንሽ ኃላፊነት ስላለውና ከእለቆች ስር መርመጥመጥ ስለሚወድ በስንት ጣጣ ካገኘሁት ሥራ እንዳያፈናቅለኝ ፈራሁ። እኔ የምጓጓዘው በባቡር ነበርና አንድ ቀን ወደ ባቡር ጣቢያው መሄጃ መንገድ ላይ ይኸው ተስፋ ያልቆረጠው ኃይለ ከሥራ ስወጣ ጠብቆ እቤት ላድርስሽ ይለኛል። እምቢ የምልበት ሁኔታ አልታይ ስላለኝና ምናልባትም ለማስረዳት አጋጣሚው ይረዳኛል በሚል ከመኪናው ገባሁ። ቤታችንን እንደሚያውቅ፣ ከእህቴም ጋር ጥሩ ወዳጅነት እንዳለው ቀደም ብሎ ነግሮኝ ስለነበር አቅጣጫውን ልነግረው አልተቸገርኩም።

"አንድ ቦታ ላይ ቡና ብንጠጣ ጊዜ ይኖርሻል ወይ?" አለኝ በትግርኛ።

"እቸኩላለሁ። ለማንኛውም አንድ አስራ አምስት ደቂቃ ይኖረኛል" አልኩት በአማርኛ። ምናልባትም ሁኔታዬን ለማስረዳት ዕድል አገኝ ይሆናል።

ወደዚያው እየነዳ "እኔ በትግርኛ ሳናግርሽ ለምንድነው በአማርኛ የምትመልሺልኝ?" አለኝ

"ምነው በአማርኛ ባወራ አይገባህም እንዴ?" አልኩት።

"አአይ! አንቺ ኤርትራዊት ነሽ፣ የመጀመሪያው ቋንቋሽ ትግርኛ ነው ብዬ ነዋ!" አለ በፈገግታ። ሊያስቀይመኝ አልፈለገም።

"ዘመዶቼ ኤርትራዊ ይሁን እንጅ ተወልጄ ያደግሁት አዲስ አበባ ስለሆነ ብዙ ጊዜ የማወራው አማርኛ በመሆኑ እሱ ይቀለኛል። ለዚህ ብዬ ነው።" አልኩት

በዚህ ርዕስ ሊቀጥል አልፈለገም። ክርክርና ጭቅጭቅ ተነስቶ ያሰበውን ዓላማ የሚያጨናግፍበት ስለመሰለው ርዕሱን መቀየር መፈለጉ ነው መሰለኝ።

አንድ የቡናና ኬክ መሸጫ ቤት (ደንከን ዶነት) ገባንና እኔ አንድ ቡናና ኬክ፣ እሱም እንደዚሁ አዞ ቁጭ አልን።

"ልቀርብሽ ስሞክር ሁልጊዜ ለመራቅ ትሞክሪያለሽ?" አለኝ።

"መራቅ ስትል አልገባኝም፤" አልኩት። "ማለቴ ብዙ ጊዜ ልጋብዝሽ ስል እምቢ ትይኛለሽ?" አለኝ።

"ዓላማህ ስላልገባኝ ሊሆን ይችላል" አልኩት።

"ዓላማዬማ ግልፅ ነው። ደስ ስላልሺኝ ነው፤ ይህን መቼም የምታጪው አይመስለኝም።" አለኝና ያንን ደረቅ ፈገግታ አሳየኝ።

"እኔ እኮ ባለትዳር ነኝ" አልኩት።

"ባለ ትዳር?" አለ፣ የመገረም ፊቱን እያሳየኝ

"አዎ፣ ባለትዳር ነኝ። ባለቤቴ ያለው ሱዳን በመሆኑ ነው ያላየኸው በቅርቡ ይመጣል።" አልኩት።

"ለምን እንደማላውቅ አድርገሽ ትነግሪኛለሽ?" አለ

"ባልሽ ሳይሆን አብራችሁ ትወጡ የነበረ ሰው መሆኑን የማላውቅ መሰለሽ?"

"'ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' እኔ ባሌ ነው ስልህ ለምን እኔ የምነግርህን ትተህ ከሰው የምትሰማውን ትቀበላለህ?" አልኩት።

"መቼ ተጋባችሁ? ሁሉንም አውቃለሁ። በዚህ ላይ አንቺ እዚህ ከመጣሽ ጀምሮ ደብዳቤ እንኳ እንዳልፃፈልሽ ነው የምሰማው" አለኝ።

ደነገጥኩ፣ ገረመኝም፤ ለጥቂት ደቂቃ ዝም አልኩ። የሰይፉን ደብዳቤ አለመፃፍ የምናውቀው እኔና እህቴ ብቻ ነን። ከእህቴ ካልሆነ ከሌላ ከየት ይህን ሊሰማ ይችላል?

"ማነው እንደዚያ ብሎ የነገረህ?" አልኩት።

"እሱ ምንቸገረሽ? ሰውዬው እንደማይፅፍልሽ፣ እዚህም ከመጣሽ ጀምሮ በደብዳቤም ይሁን በስልክ እንዳልተገናኛችሁ ሁሉ ያውቃል።" አለና የሚያናድድ ዓይነት ፈገግታ አሳየኝ።

"ደብዳቤ ይፃፍልኝ አይፃፍልኝ፣ ስልክም ይደውል አይደውል ይህ እኔና እሱ ብቻ የምናውቀው የእኛ ጉዳይ ነው። እና እኔ ባለትዳር ነኝ ብዬ ስነግርህ ይኸው የሚበቃ መሰለኝ" አልኩት።

"ምንም ይሁን ምንም ልትኳኳኑ አትችሉም"

"እሱንም የምናውቀውና የምንወስነው እኛው ብቻ ነን።"

"መቼም እህታችን ዓይኗ እያየ ገደል ስትገባ ደግሞ ማየት አንችልም፤ ኃላፊነት አለብን" አለኝ የማግባቢያ ፈገግታ እየሰጠኝ።

ንዴቴ መጣ። "የማደርገውን ነገር የማውቅ፣ በዕድሜ የበሰልኩ ሰው እኮ ነኝ።"

"ፍቅር ዕውር ነው፣ ዕድሜ አይገታውም። በፍቅር አሳውሮሽ የምታደርጊውን የምታውቂ አይመስለኝም" አለኝ ንዴቴ አፍንጫው ላይ እንደሆነ ያስታውቅበታል።

ከዚህ በላይ ሌላ መልስ ልሰጠው አልፈለግሁም። አዝማሚያው ደስ አላለኝም።

"እኔ እወደዋለሁ። ብዙ መከራ አብረን አሳልፈናል። እንግዲህ ምን ማድረግ እችላለሁ" አልኩት። አባባሌን አሳዝኜ።

"በዚህ ላይ ደግሞ አማራ ነው፣ እይደል" አለኝ።

"እና ቢሆንስ?" አልኩ።

"ማለቴ ከአማራ ጋር ያለንን ጥላቻ ታውቂያለሽ"

"እኔ አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር ሰው መሆኑን ብቻ ነው። ኢትዮጵያዊ!" አልኩት፤ ውስጤ እየተቃጠለ ያለውን ንዴቴን ዋጥ እያደረግሁ።

"አባትሽም እንደማይፈቅዱት ሰምቻለሁ።"

"ይህን ደግሞ ማን ነገረህ? ውሸት ነው?" አልኩት።

"አውቃለሁ እባክሽ ይልቅስ ልምክርሽ። እሱ አሁን አንቺ ረድተሽው እዚህ እንድታመጪው ነው እንጂ እዚህ ሲደርስ ያውም መምጣት ከቻለ የራሱን ዘሮች ሲያገኝ ይለወጣል።" አለኝ።

ሰዓቴን አየሁ፣ ወሬው እንዲቀጥል አለመፈለጌን በተለያየ መልክ ብገልፅለት አልገባው ስላለ "በል እባክህ አሁን ቤት መድረስ ስላለብኝ እንሂድ" አልኩት።

"ታዲያ ምን አልሽ?" አለኝ።

"ነገርኩህ እኮ፣ አድርሰኝ እባክህ" አልኩት።

"ገና ለገና ተሳክቶለት ከሱዳን ይመጣል ለምትይው ሰው ጊዜሽን ባታጠፊ፤ ምናለ ምክር ብትሰሚ።"

"ነግሬአለሁ እንግዲህ፤ ከእንግዲህ በኋላ ይህን ነገር ባታነሳብኝ ደስ ይለኛል።" አልኩና ተነሳሁ።

"ቆይ እንጂ ትንሽ ምን አስቸኮለሽ?" አለኝ።

"አላደርስሽም ካልክ በታክሲም ቢሆን እሄዳለሁ። እቸኩላለሁ ብዬ እየነገርኩህ" አልኩት

"ኧረ አድርስሻለሁ፤ ታሳዝኚያለሽ አንቺ ግን" አለና ተነሳ። ወደ ቤት ስንሄድ መንገድ ላይ ብዙም አላወራን። ቤታችን መዳረሻ ጋ ስንደርስ።

"እሺ እሱም እስኪመጣ ብቸኛ ከመሆን ምናለ ከእኔ ጋር አብረን ብንሆን" አለ።

"አንድ ሰው እየወደድክ ከሌላ ጋር መውጣት እንዴት ይቻላል። እኔ እንደነገርኩህ ለእሱ ጠንከር ያለ ፍቅር ስላለኝ ከሌላ ሰው ጋር ለመውጣት ፍፁም ሃሳቡም የለኝም። በፍፁም አይሆንልኝም። እባክህ ተረዳልኝ።" አልኩት ቢገባው።

"ብቸኝነት ጥሩ አይደለም። አየሽ በተለይ እዚህ አሜሪካ ሌሎች በጥሩ ሁኔታ አያዩትም" አለ።

"ሰው ስለሚያወራው ጉዳይ ግድ የለኝም። ለሰው ሳይሆን የምኖረው ለራሴ ነው።"

"እንዳው ልጠይቅሽና ስሜት ብጤ አያስቸግርሽም" አለኝ።

"የምን ስሜት?" አልኩት።

"ምን እንደማታውቂ ትሆኛለሽ?"

"አላውቅም የምትለውን፣ የምን ስሜት?"

"አአይ ማለቴ . አለ አይደለም አያሰኝም።"

"ምን?"

"ለምን እንደማያውቅ ትሆኛለሽ? ሳይገባሽ ቀርቶ እንኳ አይደለም። እንዴት እንደሚለው ለማወቅ ፈለግሁ። ውስጤ በሁኔታው የተናደደ ይምሰል እንጂ ጅልነቱ የበለጠ እያሳቀኝ መምጣቱ ይታወቀኝ ጀመር።

"ምነው አንተ ምን ለማለት እንደፈለግህ ብትናገረው?"

"ምን ብዬ ነው የምናገረው?"

"ማለት የፈለግኸውን። Sex ማለትህ ነው?" አልኩት፣ ይውጣለት

"እህ! . . . አዎ Sex" አለ

"አንድ ነገር ልንገርህ፤ እኛ ሴቶች የምንወደው ወንድ ካለ እሱን ካላየን ሆነ ካላገኘን አያሰኘንም። ይህ ይግባህ? የእኔም እንደዚሁ ነው" አልኩት። ቢገባው የነገርኩት እምነቴንም ጭምር ነበር። ከዚያ በኋላ ደፍሮ ሊቀጥልበት አልፈለገም ጥያቄውን። ዝም አለ። እኔም እቤት ምንግዜ ደርሼ እህቴን በጠየቅሁዋት ነበር ችኮላዬ። እቤቴ አደረሰኝና ሄደ። እየተቻኮልኩ እቤት ገባሁ። ውስጤ ሲቃጠል የዋለውን ንዴት ልነግራችሁ አልችልም። እቤቱን ከፍቼ ስገባ እህቴ ከሥራ ወጥታ መኝታ ቤቷ ልብሷን ስትቀያየር ደረስኩ። መኝታ ቤቷ አልጋው ጫፍ ቁጭ አልኩ። ከልብስ መስቀያው ክሎዜት ውስጥ አንድ ነገር ደበቅ ስታደርግ ያየሁ መሰለኝ። እንደመደንገጥ ማለቷ ጥቂት ሳይገርመኝ አልቀረም። ድንገት ስለገባሁባት ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ቀና ብዬ ሳያት ጥምድ አደረግሁዋት።

"ምነው ትብለፅዬ ምን አደረግሁሽ? የእናቴ ልጅ እህቴ ነሽ" አልኳት እንባ እየተናነቀኝ።

ደንገጥ ብላ ክሎዜቱን ዘግታ ወደ እኔ ጋ መጣች።

"ምን አደረግሁሽ?" አለችኝ።

"ለዛ እኛ ጋ ለሚሰራው ለኃይለ ምን ብለሽ ነው የነገርሽው?"

"ምን ብላ ነገረችኝ አለሽ?" ከድንጋጤዋ መለስ አለች። "ደግሞ እኔ ምን ብየ እነግረዋለሁ" አለች

"ስለ እኔና ስለ ሰይፉ ከየት ሰማ ታዲያ?"

"ከተማው ሁሉ የሚያወራው ነው። ከእሷ ሰማሁ አለሽ እንዴ?"

"ስሚ ትብለፅ ስለእኔና ስለሰይፉ ከተማው ከየት ሰምቶ ነው የሚያወራው?"

"ትብለፅ አወራች ታዲያ! ያው ከሱዳን የመጡ ብዙ ልጆች ከተማውን ሞልተዋል፤ እነሱ አውርተው ሊሆን ይችላል።" አለች

"ሰይፉ ለእኔ ደብዳቤ አለመፃፉን ሆነ ስልክ አለመደወሉን ከእኔና ከአንቺ በስተቀር ማን ያውቃል?" አልኳት፤ እንደ ቁጣም አሰኘኝ።

"እና አንቺ ነሽ ልትይኝ ነዋ?"

"መቼም እኔ አላወራሁ፤ ለምን እንካካዳለን።" አልኳት። ውስጤ እየተቃጠለ የነበረውን ንዴት ልንግራችሁ አልችልም።

አንገቷን ደፍታ ዝም አለች። ልትከድ እንደማትችል አውቀዋለች። መልስም ልትሰጥበት የምትችለው ጉዳይ የሆነላት አልመሰለኝም።

"እኔ እህትሽ ነኝ። የኔ ገበና የአንቺም ገበና ነው። ዝም ብለሽ የሆነውን ያልሆነውን ነገር መናገር ተገቢ አይደለም።" አልኳት።

"ምን አድርጊ ትይኛለሽ! አላስወጣ አላስገባ አለኝና እኮ ነው" አለች።

"ለምን? ምንአድርጊ ብሎ?" አልኳት።

"እህትሽን በጣም እወዳታለሁ ሲለኝ ጊዜ ረጋ በል እሷ የምትወደው ሰው አላት ብለውም አልገባው አለኝ" አለች።

"ከሰይፉ ጋር በደብዳቤም እንደማንገናኝ ትነግሪዋለሽ እንዴ ታዲያ?" አልኳት።

"እባክሽ አብረኸት ምኑንም አላውቀው። ብቻ ተከስተ እኮ ጥሩ ሰው ነው" አለች

"ምኑ ነው ጥሩ?"

"እንዴ አንቺ እሱ እኮ ሁለት ሥራ እየሰራ ያለው ገንዘብ እንዲህ አይምሰልሽ።"

"አይ ትብለፅ ትገርሚኛለሽ። የእሱ ሁለት ሥራ መሥራት፣ የእሱ ገንዘብ መብዛት ለእሱ ነው። ይህ የሰው ጥሩነት መለኪያ አይደለም። ይህም ሆነ ያ ለእሱ ማንነትም ሆነ ምንነት ማወቅ አልፈልግም።" አልኳት ፍርጥም ብዬ።

"ይኸው ከመጣሽ ከአንድ ሰው ጋር እንኳ ስትወጪ አላየሁ። ብቸኛ መሆን ለሴት ልጅ ጥሩ አይደለም በተለይ እዚህ አሜሪካ አገር። ምናለ አንቺ ትንሽ ብታስቢበት። ሰይፉ መጣም አልመጣም ለጊዜውም ቢሆን ጓደኛ መያዙ ክፋት ያለበት አይመስለኝም።" አለች።

"በይ እርሺው፣ እኔ ነግሬሻለሁ። የሰይፉን የመጨረሻ ቁርጥ ሳላውቅ እንኳን ላደርገው ይህን ነገር ላስበውም አልፈልግ። በሰይፉ ላይ ያለኝን እምነት ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። እወደዋለሁ። በቃ። ይህ የማይቀር በውስጤ ያለ ስሜት ነው።

"ተይ አብረኸትዬ ከአንቺ የበለጠ አላውቅም። ወንድን ልጅ ይህን ያህል ማመን ግን ደግ አይደለም። አንቺ ምንቸገረሽ ሞክሪው፤ ለጊዜውም ቢሆን።"

"እንግዲህ ነገርኩሽ። ሁለተኛ ይህን ነገር እንድታነሺብኝ አልፈልግም። በነገርሽ ላይ ዛሬ ደብዳቤ ከፍተሻል?" አልኳት።

"እዎ! ምንም የለም።" አለችኝ።

እቤት ሁልጊዜ ቶሎ መግባት የምፈልገው ለዚህ ነበር። ድንገት የሰይፍዬ ደብዳቤ ከመጣ በሚል ሁሌ እጠይቃታለሁ። የፖስታ ሳጥኑ ቁልፍ እሷ ጋ ስለሆነ የምትከፍተው እሷ ናት።

'የዘመድ ጥል የስጋ ትል" ይባላል። ምንም ብበሽቅባትም፣ ምንም ብታናድደኝ እህቴ ናትና ቂም አልይዝባትም። ለተከስተ የእኔን ምስጢር ዝክዝክ አድርጋ መለፍለፏ ደስ ባይለኝም በየዋህነት ያደረገችው አድርጌ ወሰድኩት። እኔን ከማትወዳቸው እማራዎች ጋር እንዳልሆን በየዋህነት ከምትቃዠው ቅዠት የመነጨ ሴራዋ እንደሆነ ነው የተረዳሁት። በእርግጥ የዋህነት እንጂ፤ እንዲያውም ጅልነት። ዘር፣ ጎሣ፣ ሃይማኖት የማይለየውን የፍቅር ኃያልነት ያለመረዳት ሞኝነቷ እንጂ እስቲ አሁን እኔ እህቷ የእናቴ ልጅ ደስ የሚለኝን ነገር ማድረጌ ምን ከፍቷት? ብዙ ማውራት አልፈለገችም መሰለኝ እኔን መኝታ ቤቷ ትታኝ የምሄድበት ጉዳይ አለ ብላ ወጣች። እኔም ትንሽ ተከዝ ብዬ ለአፍታ በሃሳብ ባህር ውስጥ ከገባሁ በኋላ አንድ ነገር ከነከነኝ። ቅድም እኔ ድንገት ስገባ ከእኔ አንድ ነገር ለመደበቅ መመኮሯ ተሰምቶኝ ስለነበረ ሆድ ሆዴን በላኝ። ምን ይሆን በማለት ተነስቼ ወደ ክሎሴቷ ሄድኩ። ባይ ፊት ለፊት ምንም ነገር የለም። አንደኛውን ፊትለፊት የተሰቀለውን ኮቷን ሳየው አለወትሮው ኪሱ አበጥ አለብኝና ምን እንደሆነ ለማወቅ እጄን ከተትኩና አወጣሁት። በጣም ብዙ ደብዳቤዎች ናቸው። አድራሻውን ስመለከተው ለኔ ነው። የላኪውን ስም ስመለከት ሰውነቴን አንድ ነገር ወረረኝ። ከፍቅረኛዬ ከሰይፉ የተጻፉ ወደ ሰላሳ የሚደርሱ ደብዳቤዎች ናቸው። ከድንጋጤ ብዛት እጄ መንቀጥቀጥ ጀመረ። እየተንገዳገድሁ ደብዳቤዎቹን ይዤ አልጋው ላይ ዘፍ አልኩ። የገባሁበትን ምስቅልቅል ሁኔታ ምን ብዬ ልንገራችሁ። እንዴት ይሆናል?" እየተንቀጠቀጥኩ ደብዳቤዎቹን ሳይ በሙሉ ተከፍተዋል። በተለያዩ ጊዜ የመጡ ናቸው። ደብዳቤዎቹን እቅፍ አድርጌ ከደረቴ ስር በማድረግ ጋደም አልኩ። እንባዬ ኮለል እያለ መፍሰስ ጀመረ። "ለምን? ለምን? ለምን?" በአዕምሮዬ የሚመላለሱት ጥያቄዎች። ጥቂት ቆይቶ መንፈሴ እንደተረጋጋ ሰይፉ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች በእንባዬ ጭጋግ ውስጥ ማንበብ ጀመርኩ።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማሟሟት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል የሚል እምነት አለን። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። አንዱ ከሌላው ልምድ ሊማር ይችላልና። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠሙኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩት መሆኑ ይታወቅልን።

## እንድረስላቸው ! !

አንዋር አህመድ (ዲሲ)

በዛሬው መጣጥፌ ሌሎች ወረቀቶች ላይ ያልተከተቡ ወይንም ለጆሮ አዲስ የሆኑ ነገሮችን ለመተረክ ሳይሆንም ከነበሩና ካሉ ክስተቶች በመነሳት የአሜሪካንን ጀርባውን ለመግለፅ መሞከር ይሆናል። ከዛ በፊት ግን ባለፉት ሁለት ወራት ባለንበት በአሜሪካን አገርና ስም አገራችን ላይ ሰፊውን መድረክ ይዞ የቆየው የአድዋ ድል አከባበር እንደነበር ቢታወቅም ለእኔ ግን ከምንጊዜውም የበለጠ በተለይ እዚህ ዋሽንግተንና አካባቢዋ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ያሳዩት ትብብር ሲያስገርመኝ ከከረመው አንድ ነገር ስለሆነ አብረን ብንመክርበት አይከፋም።

ባለፉት አስር አመታት ምናልባትም ከዛ በላይ ሊሆን ይችላል። የነገር መጠንሰሻው፣ የመቧጨቂያው፣ የመባያውና የሐሜት መደብር የሆነችውና የነበረችው ዋሽንግተን የማን አለብኝ ደንበኞቿን ስታስተናግድ ቆይታለች። የዘፋኙ፣ የአርቲስቱ፣ የዳንሰሪው፣ የእስክስታ ወራጁ ኧረ ስንቱ! ስንቱ ተቆጥሮ የማያውቀው፣ ሙያ ያለውም የሌለውም ዋሽንግተንን ያልረገጠ ያለ አይመስለኝም። ለባላገሩ አዲስ አበባ ብርቅዬ እንደሚሆንበት ሁሉ አሜሪካ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊም ዋሽንግተን ለየት ብላ ትታየዋለች። ከእናት ምድራችን ከተለየን ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ እንዳለው የትም የትም ይሁን እህል ውሃችን ወደሳበን ቦታ ሄደን መኖራችን አይቀርም። ህይወታችን በየቦታው ተዘበራርቆ፣ አንድ መሆን እትትን በረባ ባልረባው በመናቆር የታሪካችንን አኩሪነት በቁልቁላኑነት ብቻ ስንተርከው አሉባልታና የወሬ ሚዛናችን በራሳችን ላይ አድልቶ ቁልቁል ሲሰበን ይታያል። ይህን ሁሉ የዘረዘርኩበት ያው የፈረደበት የአድዋ ጉዳይ ስለሆነ ወደእሱ ልመለስ።

ዝግጅቱ በማን? እንዴት? ለምን? ተዘጋጀ የሚለው ሀተታ ውስጥ መግባቱ አስፈላጊ አይደለም። ዓላማው ኢትዮጵያዊ እስከሆነ ድረስ ዝግጅቱን ያዘጋጁት ሰዎች ብዙ ውጣ ውረድ ቢደርስባቸውም የልብ ቀናዒነታቸው ለስራቸው መሳካት ትልቅ ውጤት አሳይቷል። በቦታው የነበረው ህዝብ ከተጠበቀው በላይ በመምጣቱ እውነትም ዲሲ ያለሁ አልመስል አለኝ። የጃማይካኖቹ በኢትዮጵያ መኩራት፣ ከዚህ በፊት በታሪክ ታይተው የማይታወቁ የጣልያን ፋሺስት የግፍ ጭፍጨፋ ፎቶግራፍና ስዕሎች መታየት፣ እንዲሁም ህዝቡን ሲያስለቅሱት ማየት፣ ልባዊ ደስታን ሰጥቶኛል። በዓሉ በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ማምሸቱ በቦታው የነበረው ህዝብ ከሰጠው ጭብጨባና ጩኸት ማወቅ ይቻላል።

ምናልባትም የዛ አይነት አንድነት፣ መተሳሰርና፣ ፍቅር የሚደገመው ከመቶ አመት በኋላ እንዳይሆን ስጋት ላይ ይጥለኛል። ይህን ያልኩት ያለ ምክንያት አይደለም። ከዚህ በፊት እንደተከሰተውና እንደተለመደው ዲሲ ለሰርግ ወይንም ለሙዚቃ ዝግጅት ሲባል የሚመጣው ህዝብ ጣልያን እንደገና ኢትዮጵያን ቢወራት ከሚመጣው ህዝብ በእጥፍ የሚበልጥ ይሆናል ብዬ ስለገመትኩ እንደዚህ አይነት ልብ የሚነካ ዝግጅት ቢደጋገም ከብዑሉ ባህላችን እየራቁ የሄዱትንም ወጣቶች ሊመልስ ስለሚችል ያላዘጋጁ ወይንም ያላሰቡ ሰዎች ትምህርት ቢወስዱ ጠቃሚ ነው እላለሁ።

በበዓሉ ላይ ተሳትፎ ካደረጉ ሰዎች ውስጥ ሁለት ወጣቶች እዚህ አሜሪካ ያደጉ ይመስሉኛል በዚሁ በእንግሊዝኛው ቋንቋ Rap አዘፋፈን ግጥሞቹን በአማርኛ በማድረግ መድረኩ ላይ እየተቀባበሉ ሲዘፍኑ በመጀመሪያ እኔንም አልሳበኝም ነበር። ነገር ግን ምን እንደሚሉ በጥሞና ሳዳምጥ ቀደም ሲል የገመትኩት ግምት መልሶ ራሴን እንዲያሳፍረኝ አደረገኝ። አቅጣጫው ጠፍቶባቸው፣ ባህላቸው ተዘባርቆባቸው እርዳታ እንደሚጠይቁ ከግጥሙ ስንረዳ ሁሉም ህዝባዊ አድናቆቱን ገለፁላቸው። እውነትም እንደነዚህ ሁለት ወጣቶች በየቦታው ቀኑ ግራ፣ ብርሃኑ ጨለማ የሆነባቸው ብዙ ወጣቶች እንዳሉ አልጠራጠርም። ማን ይሆን ህመማቸውን ታሞ፣ ቁስላቸውን ቆስሎ በእኔ ለእኔ ባይነት ሳይገታ የአገር አንድነትና ህልውና አሳስቦት ከሄዱበት ወይንም እየሄዱ ካሉበት የጭቃ መንገድ ሊያወጣቸው የሚሞክር ሰው ጠፍቷል አልልም። ኢትዮጵያ ያበቀለቻቸው እልፍ አእላፍ ልጆቿ ተፈጥሮና ትምህርት ቤት በለገሳቸው እውቀት ማንንም ከማጡ ሊያወጡ ይችላሉና። የኑሮ ሁኔታ አዳሽቋቸው የዕለት ጉርሳቸውን ለመሙላት የሌላውን ህይወት ለማየት እንገታቸው ቀና ባይልላቸው ነው እንጂ። ይህም ሲባል እዚህ አሜሪካ ያለነው ማድረግ ያለብን ነገር ነው ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም በጥቂቱም ቢሆን ሆዳችንን ስለምንሞላና ልጆቻችንና ወንድሞቻችን በአልኮልና በአደንዛዥ እፅ ሳይበላሹ በፊት ብንደርስላቸው ለማለት ነው።

# እልፍ ሲሉ እልፍ ሲገኝ

ፍገሬል ሰዩሰች (ከአትናትዮስ)

ከአሰገደች ጋር ዝም ብሎ የመውጣቱ ተግባር ለጥቂት ጊዜ ቀጠለ። ከዚያን ቀን ምሽት ጀምሮ የአሰገደችም ሁኔታና ጠባይ እየተለዋወጠብኝ መምጣቱን ስረዳ እኔም መንፈሴን ጠንከር ለማድረግና እሷንም መርሳት መጀመር እንዳለብኝ ተረዳሁ። እኔ በቀረብኳት ቁጥር የምትርቀኝ ከሆነና ስለጋብቻም ደንታ የሌላት፣ በእሷ አባባል "ገና ብዙ የምትሰራው ነገር" ስላላት ጊዜዬን አለማጥፋቱን መረጥኩ። "እልፍ ሲሉ እልፍ" ይገኛል ይሉ የለ። ቢሆንም አሰገደችን ቶሎ ለመርሳት አልቻልኩም። በሁለት ምክንያቶች፤ አንደኛው ይህ ነው የምለው አይደለም። በቃ ፍቅር ቢጤ አስይዛኛለች። ሁለተኛው ደግሞ ከላይ እንዳልኩት ልረሳት ወስኜ እኔ ስልክ መደወሌን ባቆምም እሷ በተመቻት ጊዜ ትደውልና እየረሳ ያለውን መንፈሴን ስለምትረብሸኝ ነበር። በሁለትም ሆነ በሶስት ሳምንት አንዴ ትደውልና "ምነው ጠፋህ? ዛሬ ማታ ምን ትሰራለህ?" ካለችኝ መንፈሴ ይረበሽና "አለሁ" ብዬ ተነትቼ እሄዳለሁ። አጅሪት ሲመቻት ነበር የምትደውለው። ለጥቂት ጊዜ እሷው እንደተመቻት ሄድኩና ኋላ ዕቃነቴ እየተሰማኝ በመምጣቱ ጥሪዎቹን አቆምኩ። ደውላ እንገናኝ ስትለኝ አይመቸኝም፣ ጉዳይ አለኝ ማለት ጀመርኩ። መጀመሪያ ላይ እንደዚያ ስላት እውነት አልመሰላትም። "excuse me!" አለችኝ። እንደማይመቸኝ ደገሜ ነገርኳት። ለጥቂት ጊዜ ዝም አለችና "እሺ" ብላ ስልኩን ዘጋች። ይህንን በተባባልን እንደወትሮው በሳምንቱ ሳይሆን ከሁለት ቀን በኋላ ደወለች። አሁንም እንደማይመቸኝ ነገርኳት። በነጋታውም እንዲሁ። በአራተኛው ቀን ስትደውል ይህንኑ "አይመቸኝም" ስነግራት "ምን ሆነሃል? ያስቀየምኩህ ነገር አለ እንዴ?" አለችኝ። አይገርማችሁም። "ያስቀየምኩህ ነገር!" ብሎ ጥያቄ አይገርማችሁም። እንግዲህ ግልፅ መሆንና የልብን ግልጥልጥ አድርጎ መናገር ችግር ካመጣ ኩራ ብሎ መናገር ሳያዋጣ ይቀራል ብላችሁ ነው። እኔም መልሴ "አአይ ያስቀየምሽኝ ነገር የለም፣ ምነው እንዲህ አልሽ?" አልኳት።

"እንዴ ቢሆን ነው እንጂ! ታዲያ ይኸው ያለፉት አራት ቀናት ደውዬልህ ላገኝህ ስልህ መልስህ 'አይመቸኝም' ብቻ ሆነብኝ።" አለች።

"ሳይመቸኝ የቀረ እንደሁ ታዲያ መልሴ ምን ሊሆን ነው?" አልኳት።

"አነጋገርህ ሁሉ ተለውጦብኛል። ፊት እንደዚህ አልነበርክም።" አለችኝ።

"ምንም አልተለወጠም። ሳይመቸኝ ሲቀር ምን ልልሽ ነው ታዲያ" አልኳት ድርቅ ብዬ።

"እሺ አሁን ምን ትሰራለህ? ትመጣለህ?" አለችኝ፣ ልስልስ ባለ አንጀት በሚበላ አባባል።

"ኖ! እየነገርኩሽ፣ አንድ ቦታ መሄድ አለብኝ።" አልኳት።

"እሺ እኔ ልምጣ!" አለች። እልህ ብጤ በያዘው ቃና።

"ምን ነካሽ አሰገደች፣ እየነገርኩሽ። አንቺም መጣሽ እኔም አንቺ ጋ መጣሁ ሲመቸኝ አይደል። እንዲያውም ሰዓቱ ደርሶብኛል" አልኳት።

"ወይኔ! አትናትዮስ እንደዚህ ተለወጥክ" አለች።

"በይ እንግዲህ ሲመቸኝ እደውልልሻለሁ። አሁን መሄድ አለብኝ" አልኳት።

"እንዴ! እኔ አላምንም! ወይኔ አትናትዮስ፣ ትገርማለህ፤ . . . እሺ ትንሽ አዋራኝ።"

"ምን ነካሽ አሰገደች? understand አድርጊ እንጂ። መሄድ አለብኝ ነው የምልሽ" አልኳት ቆጣ ብዬ።

"ከማን ጋር ነው ቀጠሮ ያለህ?"

"አታውቂም"

"ወንድ ወይስ ሴት! እ . . ህ!" አለች።

"እባክሽ አሰገደች ልቀቂኝ፣ እንቢ ካልሽ መዝጋቴ ነው ስልኩን።

"እስቲ ሞክራታ! ሁለተኛ ዓይኔን አታያትም።"

ንዴትም፣ ብሽቀትም፤ አሸናፊነትም ሁሉም ተሰማኝና ስልኩን ጆሮዋ ላይ ጠረቀምኩት።

"ብልጥ" አልኩ ሙከ ብዬ ስልኩን እንደዘጋሁ። በወኔዬ ተደነቅሁ። በአሰገደች ላይ እንዲህ አደርጋለሁ ብዬ ገምቼም አላውቅ። በሰው ላይ ስልክ መዝጋት አድርጌ የማላውቀው ባህርይ ነበር። በተለይ እሷ ላይ ስልኩን እዘጋለሁ ብዬ ፍፁም አላሰብኩትም። እርር ድብን ቅጥል ያለው ውስጣዊ ስሜቴ ገንፍሎ ያደረገው ነገር መሆኑ ነው መሰለኝ። ትክዝ ብዬ እንዳለሁ ስልኩ በኃይል ሙኾ ለአፍታም ቢሆን ከገባሁበት የሃሳብ ባህር አወጣኝ። "እሷም ትሆናለችና አታንሳ" አለኝ መንፈሴ። ሶስቴ ደውሎ አራተኛው ላይ ወደ ጥሪ መቀበያ ቴፕ (Answering machine) ሄደ።

"አትናትዮስ! ስልኩን አንሣው!" የሚል የአሰገደች ድምፅ ተሰማ። "አለህ፣ አውቃለሁ፣ አንሳው" አለች ደገማ እርር ድብን እንዳለች ከድምጿ ያስታውቃል። እኔስ ቢሆን እርር ብዬ ከርሜ የለ ጭጭ አልኩ።

"ስልክ በጆሮዬ ትዘጋ አትንዬ . . . ግዴለም፣ . . . በል እንዳልክ" የሚል የሚያሳዝን፣ የሚያባብል ድምጿ ተሰምቶ ስልኩ ተዘጋ። "ምን እንዲህ ጨካኝ አደረገኝ?" ብዬ ከራሴ ጋር ሙግት ገጠምኩ። ገና መጀመሪያ አካባቢ ስንገናኝ ታቀላምጠኝ የነበረው "አትንዬ" ዛሬ ከየት መጣ? አልኩ በሆዴ።

ይህን በማደርግበት ጊዜ ሁለንተናዬ በእሷ ላይ እየተለወጠ መምጣቱ እየተሰማኝ ነው። ስፈልጋትና ስለእሷ ስጨነቅ ብዬም እሷን ለትዳር ጓደኝንት ስመኝ የት ነበረች? አሁን በእሷ ላይ ያለኝ

እምነት መንምና ስለእሷ ማሰብና መጨነቅ ባቆምኩባት ጊዜ ከየት መጣች? የሚገርማችሁ ነገር እሷን እንደዚያ ስለምናትና ስለማመጣት የነበርኩት ሰውዬ ዛሬ ተራዋን ልምጣ እያለች ደጋግማ በጠየቀችኝ ቁጥር፣ ደጋግማ በለመነችኝ ቁጥር የበለጠ እየጠላሁዋት መጣሁ። ቀስ በቀስ ከሆዴ እየወጣች ጠፋች እያደርም አውሬ ትመስለኝ ጀመር። በተከታታይ እየደወለች የምትተወውን መልዕክት ሁሉ ላለመስማት ወስኜ እደመስሰው ጀመር።

መለስ ብዬ ላስታውሳችሁና እነኚህን ገጠመኞቼን ላጫውታችሁ ያነሳሳኝ "አላለልኝ ይሆን?" ብላ ትዝታ በተከታታይ ያቀረበችው የራሷ ታሪክ ነው። እኔም የትዝታ "አላለልኝ ይሆን?" ታሪክ ሁለተኛው መሪ ተዋናይ በመሆኔ እሷ ማለትም ትዝታ እኔን ወዳለችበት ቦታ ከመጋበዟም በፊት ሆነ በኋላም ያጋጠማትን ሁሉ በማውራቷ እኔም እንዲሁ ገጠመኞቼን በተከታታይ አጫውቼአችሁዋለሁ። እስካሁን ግን ትዝታን እንዴት ለመተዋወቅ እንደበቃሁና እሷም ጋ በግብዣዋ መሰረት መጥቼ የደረሰብኝን አላጫወትኳችሁም። እዚያ ከመድረሴ በፊት በአጠቃላይ ለጋብቻ የምትሆነኝን ልጅ ለማግኘት ባደረግሁት ዘመቻ የገጠመኝን ሁሉ ባጫውታችሁ ጥሩ ጭብጥ ይሰጣችሁዋል ብዬ በመገመት ነው። እንግዲህ ወደ ትዝታ ታሪክ ከመግባቴ በፊት አንድ ሌላ ገጠመኝ ላጫውታችሁ። የገጠመኝ ታሪኬ ከአሰባችሁበት በላይ ረዝሞ ቢያሰለቻችሁም። አዳምጡኝ።

የአሰገደችና የእኔ ሁኔታ ቀደም ሲል እንደገለፅኩላችሁ በዚሁ አቆመ። ዓይኗን ለማየት አስጠላችኝ። እልህ ብጤ ይዟት ደጋግማ ደጋግማ ደውላ እኔ ፍንክች ባለማለቴ ተስፋ ቆርጣ ብትተውም በእኔ ላይ ዘመቻ ጀመረች። "ጠባዬ ስላልተስማማኝ ዘጋሁት (Dump አደረግሁት) እያለች ታስወራብኝ ጀመር። ስሜት አልሰጠኝም። በቃ ቀረ። እኔም ሐሞተ ቆራጥ ሆንኩ። ትዝታዋም ብን ብሎ ጠፋ። ግን ስሜ በአበሻው አካባቢ ብዙ ተወራበት። ግማሹ እሱ ነው የዘጋት ሲል ግማሹ እሷ ናት የዘጋችው እያለ ሰው በማያገባው እየገባ ወሬ ተንሰራፋ። ይህ በአለሁበት ከተማ የአንድ ሰሞን ወሬ ሆኖ ሰነበተ። ስሜት አልሰጠኝም።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# ከአካባቢያችን

## ከንቲባ ቢል ካምብል የኢትዮጵያውያንን ድጋፍ አገኙ

ቁጥራቸው በርከት ያለ በአትላንታ ከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ጊዜ የአትላንታ ከንቲባ የሆኑት ቢል ካምብል በድጋሚ አሸናፊ ሆነው የከንቲባነት ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ያላቸውን ምኞትና ድጋፍ ገለፁ። March 9, 1996 እሁድ ከሰዓት በኋላ ከ5:00 P.M. ጀምሮ አትላንታ ከተማ በሚገኘው አባይ ምግብ ቤት በተዘጋጀው ሥነሥርዓት ላይ ከንቲባው ቢል ካምብል በመገኘት ይህንኑ የድጋፍ መልዕክት የሰሙና በተጨማሪም እሳቸውም ዕለቱን "የኢትዮጵያውያን ቀን" በማለት የወሰኑ መሆኑን ገልፀው ይህንኑ የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ለኢትዮጵያውያኖቹ አስረክበዋል።

## ካሣ ከበደ ተነፈሡ (ከሰይፉ መኩሪያ)

(አትላንታ March 1996) ለ"የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ" በአምባሳደርነትና በሚኒስቴርነት ያገለግሉ የነበሩት አቶ ካሣ ከበደ በቅርቡ በታተሙ 'ጦቢያ' መጽሔቶች ላይ ስለራሳቸውና ስለኢትዮጵያ የቅርብ ታሪክ የሚያትት ዘገባ አቅርበዋል። ከቀድሞው ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር የቀረበ ግኑኙነት አላቸው እየተባለ የሚወራባቸው አምባሳደር ካሣ ባቀረቡት ትረካ ላይ ከፕሬዚዳንት መንግሥቱ ጋር ምንም ዓይነት የሥጋ ዝምድናም ሆነ ቀደም ያለ ትውውቅ እንደሌላቸውና ከፍተኛ የሥልጣን ርካብ ላይ የወጡት ለፕሬዚዳንቱ የግል አገልጋይ በመሆን ሳይሆን በሙያቸውና በራሳቸው ጥረት መሆኑን ገልፀዋል። ለመንግሥቱ ኃ/ማርያም የሚሆን ግላዊ ሀብት ያሸሹ ነበር እየተባለ የተወራባቸው አቶ ካሣ "የጓድ ፕሬዚዳንት መንግሥቱን ገንዘብ እንዳሥቀምጥና ንብረታውንም እንድጠብቅ የተጠየቅሁበት ወይም የታዘዝኩበት ጊዜ ፈፅሞ አልነበረም፤ (በአምባሳደርነት) የተመደብኩት ሀገሬን እንዳገለግል እንጂ የግለሰብ ሀብት ልጠብቅ አይደለም" በማለት ሰፋ ያለ ማስተባበያ አቅርበዋል። አቶ ካሣ ከበደ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር ውስጥ የዓለም አቀፍ ጥናቶችን የሚመረምር አንድ ማህበር ውስጥ በአማካሪነት ተቀጥረው የሚተዳደሩ መሆናቸውንም ጨምረው ገልፀዋል።

## የኢትዮጵያዊ ያለህ!

(ከሰይፉ መኩሪያ)

(አትላንታ March 23) አትላንታ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አንድ የኮምኒቲ ሬዲዮ ጣቢያ (WRFG) ዛሬ ለአስራ ሁለት ሰዓቶች ባካሄደው 'AFRICAN UNITY DAY' ፕሮግራም ላይ ኢትዮጵያን ወክለው ስለአገራቸው መናገር የሚችሉ ሰዎች ለማግኘት አለመቻሉን የፕሮግራሙ አስተናጋጅ ሸሪፋሣ ገለጡ። ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት የጀመረው ይህ ልዩ ፕሮግራም ከልዩ ልዩ አገሮች የመጡ አፍሪቃውያንን በስቱዲዮው አቅርቦ ስለየአገራቸው አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን ለአትላንታ አድማጮች ለማቅረብና እግረ መንገዱንም ለሬዲዮ ጣቢያው የሚሆን የገንዘብ ዕርዳታ ከአድማጮች ለመሰብሰብ የታቀደ ዝግጅት ነበር። ፕሮግራሙ የጀመረው ምሥራቅ አፍሪቃን

በመቃኘት ሲሆን ሱማሊያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ኬንያና ኢትዮጵያን አጠቃልሎ ያቀፈ አጫጭር ውይይት ካሂዷል። ፊት ከሬዲዮ ጣቢያው ጋር ትውውቅ የነበረው አንድ ኢትዮጵያዊ በስቱዲዮው በመገኘት ለኢትዮጵያ በተዘጋጀው ደቂቃዎች ውስጥ አጠር ያለ የትውውቅ ገለፃ አቅርቧል። የኮምኒቲ ማህበር፣ የእምነት ተቋሞችና ልዩ ልዩ ማህበሮችን አፍልቀዋል የሚባልላቸውትየአትላንታ ኢትዮጵያውያንአገራቸውን ወክለው በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ ሰዎች ለማቅረብ አለመቻላቸው በሬዲዮ ጣቢያው አካባቢ ያሉትን ሰዎች አስገርሟል። ይህ ችግር ባለፈው ዓመት በተካሄደው ተመሳሳይ ፕሮግራም ላይ መከሰቱንም የፕሮግራሙ አስተናጋጅ ገልጠዋል።

## በዴንቨር በግፍ የተባረሩ ክርስትያኖች ተፈረደላቸው

የዜናው አቅራቢ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ማሕበርተኛ (ከዴንቨር ኮሎራዶ)

ትውልዳችን ትግራይ ክፍለ አገር ነን የሚሉ የዴንቨር ነዋሪዎች በዴንቨር የሚገኘውን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የግላችን ነው በማለት አማኞችን በአውሮፓ አቆጣጠር 2-21-96 ከጠዋቱ 9:00 ሰዓት ከሰው ፍርድ ቤት አቀረቧቸው። ተከሳሽ ምዕመናንም "ከአሁን በፊት ቤተክርስቲያኑ የኛ ነው በማለት በግፍ አባረሩን። አሁን ደግሞ ለምን ይከሱናል?" በማለት ሐዘናቸውን አሰሙ። የከሳቸው ፍሬ ሃሳብ እንደሚለው "ቤተክርስቲያኑን ቀድሞ ያቋቋምነው የትግራይ ተወላጆች ብቻ ነን። ለዚሁም ማስረጃ የሆነው አቡነ ማትያስ ዴንቨር ኮሎራዶ መጥተው ይህንኑ ቤተክርስቲያን መርቀው መከፈታቸው ነው፤" የሚል ነበረ። በተጨማሪም "መሰረቱ ከኢትዮጵያየሚገኘውየቤተክርስቲያኖችዋናጽሕፈት ቤት በአቡነ ጳውሎስ ስር የሚተዳደር ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን መጠሪያ ስሙ፣ የእኛ መሆን ይገባዋል" የሚል ነበር። ቀደም ሲል ዘር ሳይለይ ሁሉም በጋራ በአንድ ቤተክርስቲያን ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ዕቃዎች ማለትም የቡና ማፍያ፣ የምንጣፍና የወለል መጥረጊያ እንዲሁም $3000.00 እንዲመልሱ ፍርድ ቤቱ እንዲሰጥበት ክስ አቅርበዋል። ክሱ እውነትን ያዘለ ለማስመሰል በምስክርነት ደንብ አቡነ ማቲያስን ዴንቨር እንዲመጡ አድርገዋል። ነገር ግን የፍርድ ቤቱ ዳኛ አቡነ ማቲያስን ለምስክርነት እንዲቀርቡ አልፈለገም ስላለ እቅዳቸው ሳይሳካ ወደመጡበት ከተማ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ተመልሰዋል። ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች 3 ቀናቶች ሙሉ ሁለቱም ወገኖች ጠበቃ ይዘው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የፍርድ ቤቱ ዳኛ ከዚህ የሚቀጥለውን ፍርድ በውሳኔ መልክ አቅርቧል።

1ኛ) ማንኛውም እቃ ቤተክርስቲያኑን የሚመለከት እንዲሁም $3000.00 ለተከሳሾች እንዲሰጥ፣ 2ኛ.የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን የሚለው መጠሪያ ስም ለተከሳሾች እንዲሰጥ ፈርዷል። ዳኛውም በመጨረሻ "ለ3 ቀናት ተመላልሳችሁ ፍርዱን ስትከታተሉ ለቆያችሁ ሁሉ ላደረጋችሁት ታላቅ ምግባርና ሥነሥርዓት በኔና በፍርድ ቤቱ ስም ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፤" በማለት የፍርዱን ውሳኔ ወደ መዝገብ ቤት አስተላልፈዋል።

## ስፖርታዊ ጨዋነት

ከዮሐንስ ገ.ሚካኤል ገ.ሕይወት (አትላንታ)

ውድ የላንዳፍታ ደንበኞች እንደምን ከረማችሁ? እኔ ደህና ነኝ። የአየሩ ጠባይ ለውጥ እንዴት ያደርጋችኋል? እኔን እያስደሰተኝ ነው። መቸም ስለስፖርት ጉዳይ ሲፃፍ ስፖርትን የምንወድና የምናዘወትር ሁሉ ዓይናችንን ቀና በማድረግና በማተኮር የውድድሩን ውጤት ለማወቅ እንሞክራለን። እንግዲህ ወደዛሬው ጽሑፌ አርእስት በቀጥታ ልግባና ስፖርታዊ ጨዋነት ማለት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ልሞክር። ቃሉም እንደሚያስረዳን አንድ ስፖርተኛ በውድድርም ላይም ሆነ ከውድድር ውጭ የሚያሳየው ጠባይ ሥነሥርዓትና ባህርይ በአጠቃላይ ከቡድኑ አሰልጣኝና ተጫዋቾች ከቡድን መሪዎች ወጌሻዎች፣ ደጋፊዎችና ከስፖርት ክለቡ አስተዳዳሪዎች ጋር ንፁህ መግባባት ያለው ፍቅርና መከባበር ሲሆን በግሉ ደግሞ በልምምድ ወቅት የልምምድ ጊዜውን በሥነሥርዓት መጨረስና በጨዋታም ወቅት ከራሱ ቡድን ተጫዋቾች ጋር በመግባባት ቡድኑን አሸናፊ ለማስገኘት ያሚያደርገው ንፁህ የሆነ ጥረትና ለዳኞችና ለደጋፊዎች እንዲሁም አብረውት ለሚጫወቱት የተቃራኒው ቡድን ተጫዋቾች የሚያሳየውን ፀባይና ስፖርታዊ ወንድማማችነትን ሁሉ ያጠቃልላል።

ከዚህ በተጨማሪ የራሱን ሰውነት የመጠበቅን በጊዜ በሰዓቱ የመመገብን የመተኛትን ዕለት በዕለት ደግሞ ስለአካሉና አእምሮውና ማህበራዊ ሕይወቱ በማሰብ ራሱን ለስፖርታዊ ዓላማው ዝግጁ ማድረጉ ሁሉ በስፖርታዊ ጨዋነት ውስጥ የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው።በአጠቃላይ ስለስፖርታዊ ጨዋነት ይህንን ካልኩ ዛሬ በሚደረገውና የስፖርት እንቅስቃሴ ላይ የስፖርታዊ ጨዋነት ምን እንደሚመስል ላሳይ በአሁኑ ወቅት በተለይ በሐበሻዊ ወገን እየተዘወተረ የሰው ጨዋታ የእግርኳስ ሲሆን ይህ የውድድር ስፖርት እዚህ አሜሪካን አገር ምንም እንኳ እንደአዲስ ስፖርት ይታይ እንጂ በተለይ ባለፈው የዓለም ዋንጫ ሎስ አንጀለስ ላይ በመደረጉና የአሜሪካን የእግር ኳስ ቡድን ግሩም ውጤት ከጥሩ ጨዋታ ጋር ካሳየ በኋላና የአሜሪካ ሕዝብም ጠቅላላ ጨዋታውን በመገናኛ ብዙሃን ከተከታተለ በኋላ ተወዳጅነቱና ተዘውታሪነቱ እያደገ መጥቷል። ታዲያ ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ አንፃር የእኛን ተጫዋቾች ሁኔታ ስመለከተው ምንም እንኳ ያለውን የኑሮ ጫና ተቋቁመው ልምምዱን በማድረግ ወደጨዋታ በሳምንት

ሁለት ጊዜ መሄዱ አስቸጋሪ ቢሆንም ባላቸው ፍቅርና ስፖርታዊ ስሜትየአቅማቸውን ያህል ጥረት እያደረጉ ቢሆንም በሌላው መልኩ በእግር ኳሱ ሜዳ ውስጥ በውድድር ወቅት ያለውን የስፖርታዊ ጨዋነት ሁኔታ ሳየው በጣም የሚያሳዝን ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ተጫዋቾች እርስ በእርሳቸው ሲሰዳደቡ መስማቱና ሲረጋገጡ ሲጎሻሸሙ ማየቱ የሚያሳዝን ነው። እንዲያውም ጨዋና ሥነሥርዓት የነበራቸው ተጫዋቾቻችን ተቃራኒ ቡድን ውስጥ ባሉና ስነምግባር በጎደላቸው ተጫዋቾች አማካኝነት ፀባያቸው ተለውጦ ቢጫና ቀይ ካርድበማየት ከሜዳ የተወገዱ ብዙዎች ሲሆኑ በሌላው ውድድሩን የሚመሩት ዳኞች መከበር ሲገባቸው የስድቡ ተካፋይ ሆነው ማየቴና መስማቴ የስፖርታዊ ጨዋነት የሚባል ነገር የለም እንዴ ብዬ እንዳስብ ሲያስገድደኝ አልፎ አልፎ በዳኞች በኩል የሚታየው ሁኔታ ደግሞ ተሳስተው ነው ወይስ አውቀው እያዳሉ? በማለት ራሴን እንድጠይቅ አስገድዶኛል። በሌላ በኩል እንደሰማችሁት ሁሉ የአትላንታው የእግር ኳስ ቡድን የጆርጅያ ስቴትን ለመወከል ከሚያስችለው ውድድር 2ለ1 በሆነ ውጤት በመሸነፉ ከውድድሩ የወጣ ሲሆን ባለፈው ዓመት በዚህ ውድድር አሸናፊ ሆኖ የዋንጫ ባለቤት በመሆንና ስቴቱን በመወከል ናሽቪል ቴነሲ ላይ በሊጉ ውድድር ለዋንጫ ደርሶ ሁለተኛ መውጣቱና አምስት ምርጥ ተጫዋቾች ለእስቴቱ ማስመረጡ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነበር።

ሌላው በዙሩ ውድድር ላይ ያለው ደረጃና ውጤት ዝቅተኛ ቢሆንም እንኳ ተጫዋቾቹ፣ የቡድን መሪዎቹ፣ የቡድኑ ደጋፊዎችና መስራቾች ከአሰልጣኙ ጋር የሚያደርጉት ጥረት የሚያስመሰግናቸው ሲሆን በተጓዳኝ መልኩ አዳዲስና ወጣት ተጫዋቾችን በብዛትና በጥራት ለማዘጋጀት መሞከሩ ቡድኑ ወደፊት ሊደርስበት የሚችለውን የተተኪ ተጫዋቾች ችግር ይቀርፋልና ቢታሰብበት መልካም ነው። ይህ በወጣት በተስፋ ቡድንና በዋናው የብሔራዊ ቡድን የተገነባ ጠንካራ ቡድን ዘንድሮ ዋሽንግተን ዲሲ ላይ በሚደረገው የእግር ኳስ ውድድር ተአምርን በማሳየት የዋንጫ ባለቤት ለመሆን ከአሁኑ ጥረት ይደረግ ዘንድ ተደጋጋሚ ሃሳቤን በቅድሚያ ለመስጠት እሞክራለሁ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ዛሬ በመላው አሜሪካ ከእግር ኳስ በተጨማሪ የሌሎችም የውድድር ስፖርተኞች እንቅስቃሴ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ እዩታዩ ሲሆን ይህም ዘር ሃይማኖት የፖለቲካ ልዩነት ሳይኖር ስፖርት ለጤንነት ለወንድማማችነት ለሰላምና ለፍቅር በሚለው ሙርሆ መሰረት ሌሎችንም የውድድርና የቤት ውስጥ ስፖርቶች (Indoor Games) ማስፋፋት እንደሚቻል ሁኔታው ያሳየናል።

ስለዚህ ይህንን አጠቃላይ ሁኔታ በማየት በማጠናከርና በማስተባበር ከዚሁም ጋር ስፖርታዊ ጨዋነትን በማስተማር ጠንካራና ብርቱ የሆኑ ወገኖችን መፍጠሩ ተገባና አስፈላጊ መሆኑን እየጠቆምኩ ለዚህም ቅዱስ ሃሳብ መፈፀም ያሉት የኮምኒቲ መሪዎች፣ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች ከስፖርት ባለሙያዎችና ቤተሰቦች ጋር በመግባባትና በመቀራረብ ሁኔታዎችን በቀላሉ ሊያቀናጁትና ሊያስፈጽሙት ይገባል እላለሁ።

# ስፓርታዊ ባህሪ

(ከሰይፉ መኩሪያ) አትላንታ

ባለፈው ወር በአትላንታው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቡድንና 'ዳታ ግራፊክስ' በሚባለው የአሜሪካኖች ቡድን መሀከል በተደረገው ግጥሚያ ላይ የኢትዮጵያው ቡድን ባሳየው የጠባይ ጉድለትና ርግጫ አንድ የቡድኑ ተጨዋች በቀይ ካርድ ከሜዳ ሲባረር ሁለት ሌሎች በቢጫ ካርድ ተከትበዋል። ጨዋታው እንደተጀመረ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የመጀመሪያዋን ጎል ያስገባው ዳታ ግራፊክስ ሌሎች ሁለት ጎሎችን በመደጋገም ሶስት ለባዶ እየመራ የመጀሪያው አጋማሽ አልቆ እረፍት ሆነ። በሁለተኛው አጋማሽ ላይ የኢይጶጵያ ቡድን በተከታታይ የዳታ ግራፊክስን በር ቢደበድብም ጎል የማግባት ዕድል አላገኙም ነበር። ሶስት ያለቀላቸው ግቦች በልፍስፍስ በጥለዛ ሙከራዎች መና ሆነው ቀርተዋል። የጎል እድል በከሸፈ ቁጥር ስፖርታዊ መንፈስ መኮላሸት ጀመረ። ከእረፍት በኋላ ሜዳ ውስጥ ይታይ የነበረው ርግጫና ንጭንጭ በቲፎዞዎችም ላይ በመንፀባረቁ አንድ የቡድናችን ደጋፊ ከሜዳው ዙሪያ እንዲወጣ (በዳኛው) ተደርጓል። ቋሚ መስራች አባል በሆነበት ሊግ ውስጥ የጨዋታው ረቂቅነት የሚደነቅበት የኢት.እግር ኳስ ቡድን ባለፈው ዓመት ሻምፒዮና ሆኖ ዋንጫውን እንደያዘ ቢታወቅም የዘንድሮው አጨዋወት ስልቱ ክብሩን የሚያስጠብቅለት አለመሆኑን ተመልክተናል። ይህ ቡድን የቀይ ካርድ ማከማቻ እየሆነ መምጣቱንና በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ወደፊት ከሊጉ ከነአካቴው ሊባረር እንደሚችል ሊጉ አካባቢ ያሉ ሰዎች ይናገራሉ። ከዳታ ግራፊክስ ጋር በተደረገው ግጥሚያ የኢት. ቡድን ፕሬዚዳንትና አሰልጣኙ ሜዳ ውስጥ የሚያዩት ግጭቶች እንዳሳዘናቸው ከፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር። አሰልጣኙ አቶ እንዳለ ቱፈር ተጨዋቾቹንና ቲፎዞዎችን ለማረጋጋት ጥረት ሲያደርጉ መታየታቸው የሚመሰገን ሲሆን ፕሬዚዳንቱ አቶ ማርቆርዮስ አዳፍሬ ሜዳ ውስጥ እርግጫ መብዛቱ እያበሸቃቸው "ኳስ ጨዋታ መሆኑ ቀረ ማለት እንዴ!?" በማለት የራሳቸውን ቡድን ሲተቹ እንደነበረ ለማየት ችለናል። የሚደነቅለትን የኳስ ጥበብ ለመመልከት ቡድኑን በሄደበት እየተከተሉ ድጋፍ የሚሰጡ ብዙ ቲፎዞዎች መበሳጨታቸውንም ታዝበናል። በአንድ የግጥሚያ ውጤት ላይ አሸናፊውም ተሸናፊውም ስፖርተኞች መሆናቸውን መገንዘብ እርግጫና ስድብን መቀነስ ብቻ ሳይሆን ራስንም ማክበር ነው።

## ውድ አንባብያን

በየአካባቢያችሁ የተደረጉ አበይት ክንዋኔዎችን በዜና መልክ ለማውጣት ቢቻል ከፍቶግራፍ ጋር የዜና አጠናቃሪውን ስምና አድራሻ በማከል ላኩልን። አንዱ ከሌላው መማማር እንዲችል ዜናዎችን ማቅረቡ ተገቢ ነው።

# MRA'G TRAVEL

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*


ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ ,አለንልዎ!

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን



92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305

# RE/MAX®


**today's inc.**
an independent member broker

ቤት መግዛት ለምትፈልጉ
መሬት ገዝታችሁ መሥራትም
ሆነ Subdivision ውስጥ ለማሠራት የምትፈልጉ
ሁሉ ደውሉልኝ እረዳችኋለሁ።

የክሬዲት ሆነ የሥራ ማጣት ችግር
ቢኖርቦትም ጭንቀት የለም ወገኖች
ደወሉልኝ።

ሁልጊዝም ኮሚሽን የምከፈለው
በሚሸጠው ሰው ነው።

WOW!
YO! YO!



*Have Cash?*
*Bad Credit?*
*No Job?*
*No Problem*
*Just Call me.*

- *Residential*
- *Commercial*
- *Business*
- *Relocation*
- *Forclosures*
- *HUD*



*Selamawit "Sammy" Tadesse*
*Realtor*

ሰላማዊት ታደሰ

*Remax Today's Inc*
*1597 Phoenix Blvd. Suit - 5*
*College Park, GA 30349*

*Tel - (404) 907-0525*
*or 907-0183*
*Fax - (404) 907-0524*

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

| | | |
|---|---|---|
| ለ6 ተከታታይ እትሞች (Six Consecutive Issues) | U.S. | $16.00 |
| | Canada | $22.00 |
| | Europe | $30.00 |
| | Asia | $38.00 |
| | Institutions | $40.00 |

**የሚላከሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።**
**በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።**

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ
## LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( _______ ) ______________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( _______ ) ______________

አባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# አባይ ምግብ ቤት
# Abbay Restaurant



ከእሁድ እስከ ሐሙስ ከ 11:30 a.m. እስከ 11:00 p.m.
ዓርብና ቅዳሜ ከ11:00 a.m. እስከ 12:00 midnight (ራት)
የሙዚቃ ፕሮግራም እስከ 2:00 a.m.

ለሠርግ፣ ለቀለበት፤ ለክርስትና፤ ለልደትና
ለመሳሰሉት በልዩ ትዕዛዝ እናዘጋጃለን።



የተለያዩ ባህላዊ ምግቦቻችንን ይወዳሉ።
ብቅ ይበሉና እናስተናግድዎት።

በዕረፍት ቀናት ምሽት
የሙዚቃ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።
ደስ ሲላችሁ እኛንም ደስ ይለናል፤
ስለዚህም በመስተንግዶአችን እናስደስትዎታለን።

## AUTHENTIC ETHIOPIAN RESTAURANT

Have a spicy authentic Ethiopian dinner
and stay for the cultural entertainment on weekends.

3375 Buford Highway # 1050
Atlanta, GA
(404) 321-5808






aster CD $14.00
aster CASS $ 7.00

1. ሰበቡ
2. እትት
3. ትዝታ
4. ጠይም
5. ሰላሌ
6. የሸበሉ
7. ፍቅር አነሠኝ
8. ወለላ
9. ሰኞ




Ebo Poster $10.00
Actual size 18"x24"/Full color




Ebo CD $14.00
Ebo CASS $ 7.00

1. ምኑ ተነካና
2. ኤቦ
3. ያለ ስሜ
4. የኔ ቆንጆ
5. ባለ ጋሪ
6. እስቲ ልኑርበት
7. የዋህ ልቤን
8. አሸወይና




Aster Cap (Black/Red) $10.00

Ebo T-Shirt $15.00
(L, XL) / Full Color




Kabu CD only $14.00

1. የዲ ጎሽ
2. ያሀ
3. ካቡ
4. ከዚራ
5. ባቲ
6. ተጫወታ
7. ኢዮሃ
8. ብቸኛ

Make Check or money order payable to:

## BARKHANNS RECORDS

**163 Amesterdam Ave. No. 316**
**New York, NY 10023-5001**
**Tel: (212)969-8646**

**ባርካንስ ሬከርድስ**
**የቀድሞ የአስቴር ምርጥ ዘፈኖች**
**በዲጂታል ሪማስተርድ**
**ሲዲና ካሴት**
**በቅርብ ጊዜ ያቀርብላችኋል።**
**Digitally Remastered**
**Compilation of**
**Aster's Music**
**COMING SOON**
**On CD/CS**

### ሱቆች
### RETAIL OUTLETS

Atlanta, GA
- *Sweet Auburn Grocery*
- *H & B Shop*

Chicago, IL
- *Ethio Village Restauran*

Dallas, TX
- *Maru Grocery*

L.A., CA
- *Merkato*
- *Chibo Cafe*
- *Demera*

New York, NY
- *Awash Restaurant*
- *Abyssinia Grocery*

Oakland, CA
- *Albo*

Seatle, WA
- *Blue Nile Grocery*

St. Paul, MN
- *Merkato*

Toronto, Canada
- *Ethiopian Spices*

Washington, D.C.
- *Addisu Gebeya*
- *Arada Market (MD)*
- *Ethio Sound*
- *Marhaba Market (VA)*
- *Queen of Sheba (VA)*



Aster Poster $10.00
Actual size 18"x24"/Full col

| Item | Price | Quantity | Total Price |
|---|---|---|---|
| aster CD | US$14.00 | | |
| aster CASS | US$7.00 | | |
| Kabu CD | US$14.00 | | |
| Ebo CD | US$14.00 | | |
| Ebo CASS | US$7.00 | | |
| Ebo T-Shirt (L /XL) | US$15.00 | | |
| Ebo Poster | US$10.00 | | |
| Aster Poster | US$10.00 | | |
| Aster Cap (B/R) | US$10.00 | | |
| Please, add US $2.00/item for shipping & handling. Outside USA, add US$4.00/item | | Subtotal | |
| | | Ship & Hand | |
| | | Grand Total | |

## ORDER FORM

Name: ______________________
Address: ______________________
______________________
______________________
Phone: ______________________
Ship Gift TO:
Name: ______________________
Address: ______________________
______________________
______________________
Phone: ______________________